## ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

# ዓለም ያደነቀው የኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት ሰልፍ

የሶማሊያ ሕዝብ ከእንግሊዝና ከኢጣሊያ ቅኝነት ነፃ ከወጣበት ማግስት ጀምሮ ለአገሪቱን የፖለቲካ ሥልጣን የጨበጠው መንግሥት በኢትዮጵያ መንግሥት ሥልጣን ሥር ያለውን የአስተዳደር ክልል መሬት አንድ አምስተኛውን፤ እንዲሁም የተወሰነ መጠን ከኬንያ መንግሥት መውሰድና መላውን ጂቡቲ አጠቃልሎ የራሱ ግዛት በማድረግ ታላቋን ሶማሊያ ለመፍጠር በመነሳት በአፍሪካ ቀንድ ለመስፋፋት ያለውን ፍላጎት በተመለከተ የኢትዮጵያ መንግሥት በኩል በቂ ግንዛቤ የነበረ ቢሆንም በእነዚህ ሶስት አገሮች ኪሳራ ለመስፋፋት ያለውን ምኞት በጦር ኃይል ለማስፈፀም ያስባል፤ ለዚህም ብቃት ይኖረዋል የሚል ግምት ግን በማንም ዘንድ አልነበረም።

የኢትዮጵያ ፊውዳል ሥርዓትና የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎች የፈጠሯቸውን ችግሮች ለመገንዘብ የሚያስችል ማህበራዊ ንቃት የሌላቸውን በጊዜያዊ የግል ጥቅምና በአካባቢው ጠባብ ብሔርተኝነት ስሜት የተመረዙ ግለሰቦችን በማሰባሰብ ከሐበሻ ኢምፔሪያሊዝም ጋር ለነፃነታቸው የሚታገሉ አርበኞች ናቸው እያለ የአገራችንን ሰላምና ፀጥታ ማደፍረስ ከጀመረ ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በ1969 ዓ.ም የታዩውን ዓይነት የጦር ኃይል ያደራጃል ብሎ የገመተም አልነበረም።

ሆኖም የሶማሊያ ተስፋፊ መንግሥት የተመኘውን ተግባራዊ በማድረግ እጅግ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የታጠቀ ግዙፍ የጦር ኃይል አዘጋጅቶ በአገሮቻችን ድንበር ሲያሰልፍ ነው የአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ከእንቅልፉ ነቅቶ ተመጣጣኝ የጦር መሣሪያ የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊስት መንግሥትን የጠየቀው።

ይህም ሆኖ በቅድመ አብዮት የሶማሊያ መንግሥት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተርና የተባበሩት መንግሥታት ዓለም ዓቀፍ ህጎች በመጣስ ኢትዮጵያን የሚያክል ሃገር ለመውረር አይቃጣም የሚል አስተሳሰብ በኢትዮጵያዊያንም በባዕዳንም ጭንቅላት ውስጥ ሲንቀዋለል እንደነበረ የሚታወቅ ነው።

የሰሜን አሜሪካ መንግሥት የወታደርና የሲቪል ባለሥልጣኖች መሣሪያ በተጠየቁ ጊዜ እንሰጥም ላለማለት ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች አንዱ የሶቭየት ኅብረት መንግሥት ለሶማሊያን የጦርኃይል ያስታጠቀበት ምክንያት የሶማሊያን መንግሥት ከሚፃረሩ ኢትዮጵያ፤ ከኬንያና ጂቡቲን በቅኝነት ከሚያስተዳድረው ከፈረንሳይ መንግሥት ጥቃት ራሱን እንዲከላከል እንጂ እናንተ እንደምታስቡት ኢትዮጵያን ለመውረር አይደለም።

በእኛና በሶቭየት ሕብረት መንግሥት መካከል ባለው የዶ.ታንት ውል በአፍሪካ ቀንድ አገሮች መካከል ያለው ወታደራዊ ኃይል ሚዛን እንዳይዛባ ብቻ ሳይሆን አንዱ ሌላውን ሃገር እንዳያጠቃው ወይም እንዳይወረው የተስማማን ስለሆነ እናንተን የሚያሰጋ ነገር የለም ነበር የሚሉን።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ፍንዳታ በኋላ የአፍሪካ ቀንድ ጠቅላላ ሁኔታ ፍፁም ተለወጠና ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ወሮ መሬት እንዲቆርስ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት እንዲያፈርሱና አብዮቱን እንዲቀለብሱ የሰሜን አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት የሚገፋፉ ዋና ደጋፊ ሆነ። በተቃራኒ ከምንም አንስቶ የሶማሊያን መንግሥት በአፍሪካ ግዙፍ ወታደራዊ ኃይል አድርጎ የገነባው የሶቭየት ሕብረት መንግሥት የሶማሊያን የመስፋፋት ዓላማና ወረራ ዋና ተቃዋሚ ሆነ።

የኢትዮጵያና የሶማሊያ መንግሥታት እሰልቺ የወሰን ጭቅጭቅ ወደ ወታደራዊ ፍጥጫና ብሎም ወደ ጦርነት ሳይሸጋገር ሠላማዊ መፍትሔ ይገኝለት ዘንድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ለረጂም ጊዜ ካደረጋቸው ሙከራዎች በተጨማሪ በሞስኮና በኤደን ከተሞች የተደረጉት የሠላም ጥረቶች የዚሁ የአፍሪካ ቀንድ ጠቅላላ ሁኔታ የመለወጥ ውጤቶች ናቸው።


ኤደን ላይ በተደረገው የመጨረሻ የሠላም ጥረት መድረክ የሶማሊያው መሪ ከመቀመጫው ተነስቶ ጣቱን እኔ ላይ በመቀሰር "አንተ ስለጦርነት የምታውቀው ነገር የለም። የጦርነትን ምንነት ከዚህ እንደተመለስን እንደትማርና እንድታውቅ ስለማደርግ ከእንግዲህ ወዲያ በጦር ሜዳ እንገናኝ" በማለት እቅጩን ነገረኝ።

ከኤደን መልስ ማግሥት የተጀመረው የሕዝባዊ ሠራዊት ዝግጅት በሚካሄድበት ጊዜ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የሚደርሱን ወሬዎችና መረጃዎች ያስረዱን የነበረው ከኤደን የሠላም ጥረት መክሸፍ በኋላ ወረራውን በተመለከተ በሶማሊያ መንግሥት ከፍተኛ የአመራር አካላት መካከል በሃሳብ ልዩነት ላይ የተመሠረተ መከፋፈል እንደተፈጠረ፣ ሠራዊቱ ለወረራ የሚያደርገውን ዝግጅት ያጠናቀቀ ቢሆንም ሶቭየት ሕብረትና የተቀሩትም ሶሻሊስት አገሮች ወረራውን ተቃውመው ባደረጉት ተፅዕኖ የሶማሊያ መንግሥት አመራር የፖለቲካ ውሳኔ ለመስጠት እንደተቸገረ ስለነበረ በዚህ ሁኔታ ምናልባት ውጊያው ከመጀመሩ በፊት የሁለትና የሦስት ወራት ተጨማሪ ጊዜ ማግኘት እንችል ይሆናል በሚል ተስፋ የሕዝባዊ ሠራዊቱን ሥልጠና ጊዜ ለማራዘምና ሠራዊቱን ለማብሰል አቅደን ነበር።

በግንቦት ወር አጋማሽ የሶማሊያ መሪዎች ከኤደን እንደተመለሱ ወረራውን ለመጀመር ወሳኝ የፖለቲካ ውሳኔ ላይ እንደደረሱ፣ ጦርነቱ መቼና እንዴት ይጀመር፡ ጦርነቱን የሚቃወሙት ሶቭየቶች ካገራችን ቢወጡና የእነሱ ወታደራዊ ርዳታ ቢቋረጥ አሜሪካ ስለምትሰጠው ድጋፍ ዓይነትና መጠን ከሶቭየቶች ጀርባ ከአሜሪካኖች ጋር እየደራደሩ መሆናቸውን በሚያብራራ ሁኔታ ካስረዳን በኋላ ቀደም ካሉት መረጃዎች እንደተረዳነው በሶማሊያ መንግሥት ከፍተኛ የአመራር አካላት መካከል በወረራ የሥልት ምርጫ ልዩነትና መከፋፈል እንደተፈጠረ የሚያስረዳ ሌላ መረጃ ከሞስኮ ደረሰን።

ይህ መረጃ በተጨማሪ የሰጠን በጣም ጠቃሚ ነገር ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬና አብዛኛው ከፍተኛ የሲቪል ባለሥልጣኖች የአፍሪካን አንድነት ድርጅት ቻርተር፣ በአባልነት የተቀበልነውን የአርብ ሊግ ቻርተርና የተባበሩት መንግሥታት ማህበርን ዓለምአቀፍ ህጎች ሁሉ ጥሰን በኢትዮጵያ ላይ ግልፅ ወረራ በማድረግ ከዓለም ሕብረተሰብ ከመገለልና ከመወገዝ ባሻገር ምናልባትም አላስፈላጊ መስዋዕት ሊያስከፍለን ይችላል። የተወሰኑ





አነስተኛ ሠራዊት ሠላማዊ ልብስ በማልበስ በኢትዮጵያ ውስጥ በመዋጋት ላይ ያሉትን የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጭንና ሶማሊያ አቦን የኢትዮጵያን አንድነትና አብዮት ከሚፃረሩ ኃይሎችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር አቀናጅተን ህቡዕ የደፈጣ ውጊያ ብናደርግ የአዲስ አበባን ወጣት መኰንኖች መንግሥት በመጣልና ኢትዮጵያን በመነጣጠል በሚፈጠረው ትርምስ የእኛን ፍላጐት ያለመስዋዕትነት ልናሟላ እንችላለን ሲሉ፣ ኡመር ሰመተር የሚባለው የሶማሊያ ምክትል ፕሬዝዳንትና የመከላከያ ሚኒስትር የሚመራው የጦር ኃይሉ ከፍተኛ የአመራር አካላት ቡድንና ጥቂት የሲቪል አክራሪዎች ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ወታደራዊውን መንግሥት በቀላሉ ለመጣል የሚችሉ ተፃራሪ ኃይሎች በብዛት አሉ ተብሎ የሚነገረው የተሳሳተና የተጋነነ ግምት ነው። ከእነኚህ ጋር አነስተኛ የጦር ክፍሎች የህቡዕ ውጊያ ማድረግ የሚባለው የውጊያ ስልት እኛን የሚጠቅም ሳይሆን የአዲስ አበባ መንግሥት ውጊያ እንዲዘጋጅ የሚረዳ ነው። ስለሆነም ሳንዘገይ በሙሉ ኃይላችንና በግልፅ ወረራውን እንጀምር የሚሉ ናቸው።

ስጊዜው በፕሬዝዳንቱ የሚመራው ቡድን ሀሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ግልፅና ጠቅላላ ወረራ ማድረጉ ዘግይቶ ጥሩ የኮማንዶ፣ የደፈጣ ውጊያና መሰሪ የፖለቲካ ሥራ ሥልጠና የተሰጣቸው አራት ኮማንዶ ብርጌዶች በተወሰኑ የእግረኛ የጦር ክፍሎች ተጠናክረው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ሰርገው በመግባት በቅርብ ውጊያ እንዲጀምሩ ተወሰነ።

በህቡዕ የሚንቀሳቀሰው ጦር ግዳጅ በሁለቱ አገሮች ጠረፎች ወይንም ወሰኖች ላይ ሰፍሮ ማስከበርና ለጠረፍ ጥበቃ የተሰማሩት ፖሊሶች፣ ከአንዝ ወይንም ከአናት ክፍላቸው ተገለው በርቀት በጠረፍ አካባቢ የሚገኙ የጦር ክፍሎችን እንዲደመስሱ፣ በደቡብ በመሃል ሰሜን ኦጋዴን ሰፍረው የሚገኙት የኢትዮጵያ የጦር ክፍሎች አንዱ ከሌላው እንዳይገናኝ እንዳይረዳዱና ከመሃል ኢትዮጵያ ቀለብና ሌሎችም እደላዎች እንዳይደርሳቸው መቆራረጥ፣ አንዳው ክልል ወደ ደጋው ክልል በመጥለቅ የኢትዮጵያን አንድነትና አብዮት የሚወጉ ኃይሎችን ማስታጠቅና በውጊያ ማስተባበር፣ [illegible]



መረጃ ማሰባሰብ ናቸው። እነዚህ የውጊያ ስልቶች ወይም አማራጮች አንዱ ከሌላው ይከብድ ወይም ይቀል እንደሆን እንጅ ሁለቱም ለኢትዮጵያ የሚበጁ ሳይሆን፣ ለአገሪቱ አንድነትና ለአብዮቱ ደህንነት ብርቱ አደጋዎች ስለሆኑ በህቡዕ የሚመጣውን አደገኛ ጦር በንቃት እንድትጠባበቁ እናሳስባለን። አሁን በሶማሊያና በአሜሪካ መንግሥት መካከል ከሚታየው ወዳጅነት፣ በሶማሊያ ሕዝብ ውስጥ እያደገና እየጠነከረ ከመጣው ፀር ሶሻሊስትና ፀረ-አብዮት ሁኔታዎች አንፃር የእኛ በሶማሊያ ቁይታ የሚወሰነው ከጠቅላላውና ከግልፅ የሶማሊያ ወረራ ጋር ነው በሚል ከሶሻየት ሕብረት ለመጀመሪያ ጊዜ የደረሰን ትልቅና እጅግ ጠቃሚ መረጃ ስለሆን የሕዝባዊ ሠራዊቱን ሥልጠና ማራዘም የሚባለውን ነገር ትተን የመከላከያ ሠራዊታችንን ወደ ጦር ግምባር ለማስማራት ወሰንን።

እንደሚታወቀው ይህ ሁሉ ጥረትና መሰናዶ የአንድን ታሪካዊ፣ ብሔራዊ፣ የዜግነት የትውልድ ሃላፊነት ለመወጣት ስለሆነም ይህም በታሪክ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አባቶቻችን ያወረሱን የነፃነት፣ የሃገርና የወገን ፍቅር የጀግንነትና አይበገሬነት በአዲሱ ትውልድ ሁሉ እንዲሰርፅና የኢትዮጵያ ሕዝብም በጀግኖች ልጆቹ ያለው እምነትና ኩራት እንዲዳብር ከማድረግ በላይ አገርና አብዮትን ለማዳን ነፃ አውጪው የመከላከያ ሠራዊታችን ወደ ፍልሚያው ግንባር ከመሰማራቱ በፊት የጀግና ሠልፍ ማሳየት የተለመደ ወግና ባህላችን ነው።

ስለሆነም ሰኔ 19 ቀን 1969 ዓ.ም መላው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ በተሰበሰበበት፣ ከተለያዩ አገሮች መንግሥታት በአዲስ አበባ የተወከሉ ዲፕሎማቲክ ልዑካኖች፣ የተለያዩ ባዕዳንና የሃገር ውስጥ እንግዶችን የአገሪቱ የሲቪልና የጦር ባለሥልጣኖች፣ የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር ጋዜጠኞች በተገኙበት በአዲስ አበባ የአብዮት አደባባይ ዓለምን ያስደነቀ ታላቅና እጅግ ደማቅ ሰልፍ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት እስከ ስምንት ሰዓት ታዬ።

በታጠቅ የጦር ሰፈር የሠልፍ ልምምድ በሚደረግበት ጊዜ ለመገንዘብ እንደተቻለው ሦስት መቶ ሺህ ሕዝባዊ ሠራዊት ከሀያ ሺህ በላይ መደበኛ ሠራዊት ለማሰለፍ ቢፈለግ የሚጠይቀው ጊዜ ሰዓቶችን ሳይሆን ቀናቶችን ስለነበረ በአብዮት አደባባይ ለማሰለፍ የቻልነው ወደ አንድ መቶ ሀያ ሺህ የሚሆን የመከላከያ ሠራዊት ነበር።





ሆኖም ጠላቶቻችንን ለማሸበር ስንል አምስት መቶ ሺህ ሠራዊት ነው ያሰለፍነው ብለን የሰጠነውን መግለጫ ዓለም አምኖ ተቀብሎታል። ሠልፉን እንዲመለከቱ ከተጋበዙት ዲፕሎማቶች መካከል ከፊሉ በተለይም የምዕራቡ ዓለም ዲፕሎማቶች በአሜሪካኑ አምባሳደር ተመርተው “አምስት መቶ ሺህ ሠራዊት አሳሰለፋችሁም። የምታሳዩን አንዱን ደጋግሞ ለማሳለፍ በማዞር ነው” ስላሉ ሠራዊቱ ከሚነሳበት ከጥንቱ የአውሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ እየተመመ በአብዮት አደባባይ በማለፍ በአፍሪካ ጎዳና አድርጎ እስከሚከትበት እስከ ሸንግዳ ድረስ በሄሊኮፕተር እያዘዋወርን ስላሳየናቸው አምነው በመቀበል ሰልፉ አልቆ አደባባይ ስናሰናብታቸው “እንኳን ደስ ያላችሁ አስደናቂ ክንውን ነው” በማለት ነው የተለዩን።

ኢትዮጵያ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የሄንን የመሰለ ግማሽ ሚሊዮን ሠራዊት ማደራጀት እንዴት ቻለች? ለምንስ አስፈለጋት? በማለት በዓለም ብዙሀን ማስራጫዎች ግለሰቦች አንደበትም የተለያዩ በርካት አስተያየቶች ተሰጥተዋል። እኔ በእንግሊዝ ማዕከላዊ የብዙሃን ማሰራጫ ወይም ቢቢሲ ተጠይቀው ስለ ኢትዮጵያ እናውቃለን የሚሉ ግለሰቦች የተናገሩትን ብቻ መግለጽ እወዳለሁ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥንታዊነትና የረጅም ጊዜ የትግል ታሪክ በመዳሰስ በዓለማችን የአውሮፓን ሠራዊት ከአንዴም አራት ጊዜ ደጋግመው በጦር ሜዳ በማሳፈር የረቱ ብቸኛ ሃገሮች ናቸው በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነቱ ያለውን ቀናኢነት፣ ብርቱ ተዋጊነትና ጀግንነት አውስተው በተለያዩ ሁኔታ የየግል አስተያየታቸውን ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበዋል።

ስለኢትዮጵያ እናውቃለን ከሚሉት ሁለት ግለሰቦች አንደኛው አፄ ዮሐንስ የመሩትን የጉራእንና የዶጋሊን፣ ምኒልክ የመሩትን የአድዋን ውጊያና ሌሎችንም በኢትዮጵያ የተከሰቱ ክስተቶች አውስቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአፍሪካ ወደር የሌለው ተዋጊ ሲሆን መሪዎቹም የተዋጣላቸው አደራጆች ናቸው ሲል፣ ሌላው ግለሰብ በድህረ ፋሽስት ኢትዮጵያ የሽግግር ጊዜ በነበረው የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳዳር ተሸከርካሪዎችን ይነዱ የነበረው እንደ እንግሊዝና የእንግሊዝ ቅኝ አገሮች በግራ እንደነበረ ገልጦ የእንግሊዝ ወታደራዊ ልዑክ [illegible]



የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት የመራና ያዳነው የደርግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት
ከግራ ወደ ቀኝ - ሻለቃ ተስፋዬ፣ ሻምበል አዲስ፣ ሻምበል ፍቅረሥላሴ፣ እኔ፣ ሻለቃ ፍስሀ፣
ሃምሳ አለቃ ለገሰ እና ሻምበል ብርሃኑ

ይቀጥልና በአፍሪካ የመጀመሪያው የማራቶን ጀግና የሆነውን አበበ ቢቂላን በማስታ[illegible] ማንም የማያውቀው ግለሰብ ተወዳዳሪዎቹን በርቀት ጥሎ ያለጫማ በባዶ እግሩ በር[illegible] የኦሎምፒክ አደባባይ ብቅ አለ ካለ በኋላ፣ ኢትዮጵያዊያን በድንገት ከእነሱ የማይጠበ[illegible] ነገር የማድረግ ችሎታቸው የሚያስገርም ነው ብሏል።

## ምዕራፍ ሠላሳ ሦስት

# የሶማሊያን መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጥቃት ለመከላከል በምሥራቅና በደቡብ ግምባር አብዮታዊ ሠራዊታችን ያደረገው ትግል

አብዮታዊ ሠራዊት ሰኔ 19 ቀን 1969 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አብዮት አደባባይ ላይ የጀግና ሰልፍ ባሳየበት ዕለት የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ሰልፉን ተመልክቶ ሠራዊቱን ወደ ፍልሚያው ሜዳ ሲሸኝ ያሰማው አብዮታዊ መፈክሮች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ።

"ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግምባር!"

"አብዮታዊት እናት ሃገር ወይንም ሞት!" የተሰኙ ነበሩ።

ፈታኝና ወሳኝ በነበረው የአብዮታችን ሂደት መነሻ ወይንም እፍላ የሽግግር ጊዜ ጠላቶቻችን ባወጁብን ጦርነት የተወጠርነው በአራት የአገሪቱ ማዕዘናትና እንዲሁም በመሃል ሀገር ቢሆንም የአገሪቱን አንድነትና የአብዮቱን ደሕንነት ዕድል ይወስናሉ ብለው ዋናውን ትኩረት የሰጧቸው ለአገሪቱ ሰሜንና ምሥራቅ ክልሎች ስለነበረ በእኛም በኩል መከላከያ ሠራዊታችንን ለፍልሚያው ልናሰማራ የወሰነው ወደእነዚሁ ክልሎች ነበር።

ሠራዊታችንን ለፍልሚያው በምናሰማራባቸው ሥልትና ስትራቴጂዎች በደርግ ሸንጎ ላይ ስንወያይ ሁለት አከራካሪ ምርጫዎች ከፈሉን። የተከፋፈልነው በአፍራሽ ሁኔታ ላይ በተመሠረተ ቅራኔ ሳይሆን ገንቢ በሆኑ የሃሳብ ልዩነቶች ብቻ ነበር። ታሪኩም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

አንዱና የመጀመሪያው ልዩነታችን የስትራቴጂ ምርጫ ልዩነት ነበር። በእነዚህ ዙሪያ በላይ በገለጥኳቸው የአገሪቱ ሰሜንና ምሥራቅ ክልሎች ውስጥ የሚወጉን የውስጥና የውጭ ጠላቶቻችንን ዓላማ፣ ፍላጎት፣ ማንነታቸውንና ባህሪያቸውን ከማንፃፀር ባሻገር ስለ አቅማቸውና ብሎም ድርጊታቸው ባገኘነው አስተማማኝ የውጊያ መረጃ ላይ በመመሥረት የውጊያ ስትራቴጂያችን በሰሜን መከላከል በምሥራቅ ማጥቃት እንዲሆን ለደርጉ ጉባዔ ሃሳብ አቀረብኩ።

ይህንን የውጊያ ስትራቴጂ እስካቀረብኩበት ጊዜ ድረስ ከምሥራቁ ክልል በበለጠ ከፍ ያለ ምታት የሆነብን የሰሜኑ ችግር ስለነበር ሁኔታውን በቅርብ ለመከታተል ስንል የደርጉን ሁለት ልዑካን በየጊዜው ስለምንልክ የኤርትራ ሁኔታ የአብዛኛውን የደርግ አባላት ቀልብ ሰልቦ ነበር ወይንም ስቧል። የእኔን የስትራቴጂ ሃሳብ ከማቅረቤ ሁለት ሳምንት በፊትም የደርጉ ምክትል ሊቀመንበር ጓድ ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ኤርትራን ጎብኝቷል።

የተመለከተውና የሰማውን የገንጣዮች የጥፋት ተግባርና ከዚህም አንፃር የሠራዊታችን ሁኔታ እሱ ይገምት ከነበረው በላይ ሆኖ እንዳገኘውና በእጅጉ እንዳሳሰበው ከተመለሰ በኋላ ለኔም ለደርጉ ጉባዔም በመግለጥ አስቸኳይ መፍትሔ እንዲፈለግ አሳሰቧል።

የእኔን የስትራቴጂ ሃሳብ ሲሰማ "የሶማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ላለው የመስፋፋት ዓላማ ተግባራዊነት ኃይልን በመጠቀም የጦርኃይሉን በከፍተኛ ደረጃ ያዘጋጀ ቢሆንም ከእኛ ጋር ውጊያ አልጀመረም። በኤርትራ የክፍለ ሃገሩን ርዕስ ከተማ በመከላከል ላይ ያለው ሠራዊታችን ከዓመት በላይ በአስር ኪ/ሜትር እርቀት በሽፍታ ተከብቦ ይገኛል። ቀለብ፣ ጥይት ወዘተ ሁሉም ነገር ከመሃል ሃገር የሚላክለት በአየር መጓጓዣ ነው። ድረሱልኝ፣ ከዚህ ከበባ አውጡኝ እያለ ማመልከቱን ከእኛ መካከል የማያውቅ የለም። በላካችሁኝ ጊዜ ሠራዊቱን እየተዘዋወርኩ ስጎበኝ ሠራዊቱ ደግሞ ላቀረበልኝ 'ከዚህ ከበባ አውጡን' ጥያቄ፣ በወከለኝ በዚህ ጉባዔ ስም 'ኤርትራን የሚያጥለቀልቅ ሠራዊት በቅርቡ ይደርስላችኋል' ብዬ የገባሁት ቃል ነው።

በሊቀመንበር መንግሥቱ ስትራቴጂ ፍፁም አልስማማም። ይህ ጉባዔ በዚህ ስትራቴጂ ቢስማማ ለዚህ ታላቅ የሃገር ኃላፊነት በመረጠንና በሚያምነን ሠራዊት ፊት ቃል አባይ ከመሆናችን በላይ ኤርትራን ለአረብ ምንደኞች አሳልፈን እንደምናስረክብ መታወቅ አለበት። መሆን ያለበት ሊቀመንበር ካቀረበው ተቃራኒው ነው ማለትም በሰሜን ማጥቃት በምሥራቅ መከላከልና ወንበዴውን ከመታን በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ ፊታችንን ወደ ምሥራቅ ማዞር በማለት ቆሞ በስሜት የኔን ሃሳብ ተቃወመ።

የአጥናፉን ሃሳብ በመደገፍ ከሱ ንግግር በኋላ በደርጉ ውስጥ የሰሜን ኢትዮጵያ መለዮለባሽ ተወካይ የሆኑት አባላት በተለያየ ቋንቋ ጉባዔውን ያሳምንልናል ብለው ያመኑባቸውን ሃሳቦች በማስረጃ እያስደገፉ በማቅረብ ከአጥናፉም በጠነከረና በስሜት ተቃውሟቸውን ስለገለጡ ጉባዔው በደጋፊና በተቃዋሚ የተከፋፈለበት ሁኔታ ተፈጠረ።

ተቃዋሚዎቼ እስኪረኩ ሃሳባቸውን ከገለጡ በኋላ እኔም በበኩሌ ሃሳቤ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ከዚህ ግርጌ በተመለከተው ሁኔታ መከላከያየን አጠናክሬ አቀረብኩ።

በቅድሚያ የሰሜኑን ክፍለሃገራችንን በአጠቃላይና ሠራዊታችን ያለበትን አሳዛኝ ሁኔታ በተለይ በተመለከተ በተቃዋሚው ቡድን የተነገረውን ተካፋይ መሆን ብቻ ሳይሆን ከማንም በላይ ኃላፊነት እንዳለብኝ እረዳለሁ።

በሰሜን መከላከል ብልም አሁን በአስር ኪ/ሜትር ርቀት ውስጥ በጠላት ተከቦ በመከላከል ላይ የሚገኘው ሠራዊታችን የሚቆጣጠረውን የመሬት መጠን በጣም እናሰፋና ከምሥራቁ ድል በኋላ ሠራዊታችን ፊቱን ወደ ሰሜን እስኪያዞር ድረስ ኤርትራን ለመከላከል ይችል ዘንድ በሁለት ክፍለጦር ሕዝባዊ ሠራዊትና በአንድ የታንክ ሻለቃና በተለያዩ ከባድ መሥሪያዎች ድጋፍ የምናጠናክረው መሆናችንን ገለጥኩና የተቃዋሚዎቼን የሥጋት ትኩሳት አበረድኩ።

የማጥቃቱን ቅድሚያ ለምሥራቅ ያደረግሁበት ምክንያት ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ከኤደኑ የሠላም ጥረት መክሸፍ በኋላ ግልጥና ጠቅላላ ወረራ ለማድረግ የፖለቲካ ውሳኔ ላይ ከመድረሱ ባሻገር ለወራሪው ሠራዊት መንገድ የሚጠርግ፣ በጠረፍ ላይ ያሉትን ፖሊሶቻችንንና የጦር ክፍሎቻችንን በቅድሚያ የሚደመስስና ሠራዊታችን አንዱ ክፍል ከሌላው ጋር እንዳይረዳዳ በማድረግ የሚቆርጥና የእደላ መንገዶችን የሚዘጋ መደበኛ ሠራዊት ጨርቅ አልብሶ በማስገባት የደፈጣ ውጊያ መጀመሩን በጠረፎችን ላይ



ጠቅላላ ወረራ አስፍስፎ የሚጠብቀውን የጠላት ኃይል በዓይነትና በመጠን እስከታጠቃቸው መሣሪያዎች ዝርዝር አስረዳሁ።

ይህ ለወረራ የተዘጋጀ ሠራዊት በኃይል ከአገራችን ቆርሶ ለመውሰድ የሚፈልገው ግዛት ለም፣ ሃብታም፣ ሰፊና ብዙ ሕዝብ ያለባቸውን ክፍላተ ሃገር ወይንም የአገራችንን አንድ አምስተኛ ሲሆን፡ የኤርትራ ገንጣዮች ሊያደርጉት አይችሉም እንጅ ቢችሉ የሚገነጥሉት አንድ ክፍለ ሃገር ብቻ ነው።

ከዚህ ሁሉ በላይ በጠላትነትና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሊያደርሱ በሚችሉት ጉዳትና ውርደት መጠን የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት ከኤርትራ ገንጣዮች ጋር እኩል ማስተያየት ስህተት መሆኑን ስላስረዳሁ ኮሎኔል አጥናፉን ጨምሮ በመላ የቢቱን ድጋፍ ስለአገኘሁ በሰሜን መከላከል በምሥራቅ ማጥቃት ስትራቴጂ ተግባራዊ እንዲሆን ተወሰነ።

ሁለተኛው ልዩነት ወይም ክፍፍል ምክንያት የስትራቴጂ ሳይሆን የሥልት ወይንም የታክቲክ ጥያቄ ነበር።

ጠላት ካቀደው ከዋናው ጠቅላላ ወረራ በፊት ለዋናው ወራሪ ሠራዊት መንገድ መጥረግና የውጊያ መረጃ ለማሰባሰብ በህቡዕ ያስማራቸው ጦሮች ቀደሚ ተግባር በጠረፍ ክልል ላይ ያሉትን ፖሊሶችና የጦር ክፍሎች መደምሰስ ነበር። እኛ በደርግ አዳራሽ ስለሥልትና ስትራቴጂ በምንወያይበት ጊዜ ዶሎ፣ ብርሆሽና ጎዶሬ በሚባሉ ሦስት የጠረፍ ክልል ሥፍራ ወይንም የፖሊስ ጣቢያ ላይ የሚገኙ ፖሊሶች በጠላት መደምሰሳቸው ተነገረኝ እነዚህ ራሳቸውን ለመከላከል የማይችሉና እኛም የማንረዳቸው ምስኪን ኢትዮጵያዊያን አሁን ባሉበት ሁኔታ ከጠላት ታንኮችና ብረትለበሶች ጋር ተፋጠው በከንቱ እንዳያልቁ ቁጥራቸው ወደ 29 ከሆኑት የጠረፍ ጣቢያዎች ላይ ያሉትን ፖሊሶች ዶሎ፣ ፊላ፣ ገላዲን፣ ብርኩር፣ ሙስተሂልና ሸላቦ ያሉ የጦር ክፍሎችን ወደ ኋላ መልስን ማጥቃት ወደፊት በመሮጥ ላይ ያለውን ጠላት እርምጃ ለማዘግየትና ጊዜ ለመግዛት ጅጅጋ፣ በቀብሪደሐር፣ በደገሐቡር፣ በጎባና በነገሌ አሰባስበን በአዲሱ ሕዝባዊ ሠራዊታችን እንጠናከራቸው የሚል ሃሳብ አቀረብኩ።

ይህ የውጊያ ሥልት በወታደራዊ ባህሪው በኔ በሠራዊቱ፣ ጠቅላይ እዛዥ መወሰን ያለበት ሲሆን ለደርጉ ጉባዔ ያቀረብኩበት ምክንያት ከጊዜው ሁኔታና ከፖለቲካ ባህሪው አንፃር ተመልክቼ ነው። ይህንን ሥልት የተቃወሙት የደርግ አባላት ቁጥር በጣም ጥቂት የሆነ የተቃውሞአቸውንም ምክንያትና ለአያሌ ዓመታት ሲጠበቅ ከነበረው ጠረፋችን ላይ ወታደሮቻችን ፊት ጦራችንና ፖሊሶቻችን የጥበቃ ሥፍራቸውን ጥለው መሸሽ እንዴት የውጊያ ሥልት ወይንም ታክቲክ ይባላል? ይህንን ማድረግ ጠላታችን ወሰናችንን ጥሶ እንዲገባ መጋበዝና የልብልብ እንዲሰማው ማበረታታ አይደለም ወይ በሚል ጥያቄ ላይ የተመሠረተ ተቃውሞ ነው።

ከሞራል ጥያቄና በኢትዮጵያዊነታችን ካለን ኩራት አንፃር ካየነው የምናደርገው ወታደራዊ ማፈግፈግ የሚያኮራ ወይንም በጀግንነት የሚተረጎም ስላይደለ ስሜትን ከመጉዳቱ አኳያ የጓዶቼ ጥያቄ እውነትነት አለው ለማለት ይቻል ይሆናል። ታዲያ ለዚህ ጥያቄ መልሱ ምንድነው ቢባል ራሳቸውን መከላከል የማይችሉና እኛም ከጥቃት ልናድናቸው የማንችልበት ሁኔታ እያለን ያለአንዳች ፋይዳ ወይንም ጥቅም ወገኖቻችንን በጠላት ማስገደል ሞራል አልባ ከመሆኑና ስሜትን እጅግ ከመጉዳቱ በላይ ወንጀልም መሆኑን ብዙኛው የደርግ አባላት ግንዛቤ ስለነበራቸው ያለብዙ ክርክር በቀላሉ ተወሰነ።

በዚህ ውሳኔ መሠረት መታዬት ከነበረባቸው በጠረፍ ላይ ከነበሩ የጦር ክፍሎች ዋርዴርና አይሻ በሚባሉት የኦጋዴን አውራጃ ከተሞች ላይ ሰፍረው የሚገኙት 40ኛውና 22ኛው እግረኛ ሻለቆችም ነበሩ።

እነዚህ በኦጋዴን ማዕከላዊ ክልል የሚገኙ ሁለት ከተሞች ደቡብና ሰሜኑን ኦጋዴን በሚያገናኝ ዋና አውራ የመገናኛ መንገድ ላይ ከመገኘታቸው በላይ በኦጋዴን ደረጃ ትልቅ ከተማዎች ስለሆኑና ብዙ ሕዝብ የሚኖርባቸው ስለሆኑ የጠላትን እርምጃ አይተን ውሳኔ ለመስጠት በይደር አቆይተናቸዋል።

በደርግ ጉባዔ ላይ በተወሰነውና በብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ በታቀደው መሠረት ከዚህ በሚከተለው ቅድመ ተከተል መከላከያ ሠራዊቱን ወደ የግምባሩ ማሰማራት ጀመርን።

በታጠቅ የጦር ሰፈር በቅድሚያ ከሰለጠኑትና መሣሪያ ከታጠቁት ሁለት መቶ ሺህ ሕዝባዊ ሠራዊቶች መካከል በቅድሚያ በኤርትራ ክፍለ ሃገር ከገንጣዮች ጋር በመታገል ላይ ያለውን ሁለተኛውን ዋሊያ እግረኛ ክፍለጦር ቀደም ሲል ከደረብንለት የጦር ክፍሎች ሌላ በተጨማሪ በሁለት ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለጦሮችና በአንድ የታንክ ሻለቃ አጠናከርነው። ሻለቃው የታጠቃቸው ታንኮች ከሰላሣ በላይ ናቸው።

በሁለተኛ ደረጃ ከመሃል ሃገር በጣም እርቆ በጎዴ አውራጃ ይገኝ የነበረውን አንድ እግረኛ ብርጌድ በተጨማሪ በሌላ የሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ አጠናከረነው። ጎዴ በኦጋዴን ብቸኛውና ዘመናዊው የአይሮፕላን ማረፊያና የአየር ኃይል መደብ ስለሆነ ብርጌዱ በአንድ ባለ 40 ሚ/ሜትር አየር መቃወሚያ ባትሪ መድፎች የተደገፈ ነበር። መድፎቹ አንድ መትረየስ በአውቶማቲክ ተኩስ በደቂቃ በርካታ ጥይቶችን ለመተኮስ ስለሚችሉ የጠላትን አውሮፕላኖች ብቻ ሳይሆን እግረኛ ጦሩም በጥሩ ሁኔታ ሊቋቋሙ የሚችሉ ናቸው። በቀብሪድሐር አውራጃ ከተማ የሚገኙ የዘጠነኛ እግረኛ ብርጌድ መምሪያ፤ የብርጌዱ ድጋፍ ሰጪ ከባድ መሣሪያ 4.2 ኢንች አዳፍኔ ባትሪ፤ አንድ የታንክሻለቃ፤ አንድ 13ኛው እግረኛ ሻለቃ አንድ የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ሻለቃ በመኖራቸውና በእነዚህ ላይ በተጨማሪ ከጠረፍ ጥበቃ እንዲመለሱ የሚደረጉት የጦር ክፍሎችና ፖሊሶች ስለሚያጠናክሯቸው ሌላ ጦር መጨመር አላስፈለገንም።

በሦስተኛ ደረጃ ዋርዴር የነበረው 22ኛው እግረኛ ሻለቃ የሚጠብቀው ከተማ መሃከላዊው ሰፊ የኦጋዴን ክልል ለመቆጣጠርና እንዲሁም በመገናኛነቱ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ስላለው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በአንድ ነበልባል እግረኛ ሻለቃ፤ በአንድ ብረት ለበስ ሻምበልና በአንድ ፈጥኖ ደራሽ የፖሊስ ሻለቃ አጠናከርነው።

መላው ኦጋዴን የጨርቅ ልብስ በለበሰው የሶማሊያ ጦር የተወረረ በመሆኑ የጦር ጦር ያለውጊያ መንቀሳቀስ ስለማይችል ከፍብዬ የጠቃቀስኳቸውን የጦርክፍሎች ያጓጓዝነው በየብስ ሳይሆን በአየር ነበር። አራተኛ የደገሐቡር አውራጃና ከተማው ያሉበት ሥፍራ ስትራቴጂያዊ ባህሪ ስለአለው ክልሉን ይጠብቅ የነበረውን አንድ መደበኛ እግረኛ ብርጌድ በተጨማሪ በአንድ ተጨማሪ ሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ አጠናከርነው። ይታወስ እንደሆነ በኦጋዴን ክልል አማካኝ ሥፍራ ላይ በመገኘቱና መገናኛም በመሆኑ የፋሽስትን ወረራ ለመመከት በ1928 ዓ.ም ኦጋዴን የዘመተው የኢትዮጵያ ጦር ዋና የስንቅ ማከማቻና ማዘዣ ነበር። ለጅጅጋም በጣም ቅርብ ነው።





ስለሶማሊያ ጦርነት መግለጫ ስንሰጥ

በአምስተኛ ደረጃ ጅጅጋ ለኦጋዴን ክልል ወደር የሌለው ስትራቴጂካዊ ሥፍራ ሆን ለሐረርጌም በር ነው። በዚህ ሥፍራ የሚገኘውን አንድና ብቸኛ ሜካናይዝድ እግረኛ ብርጌድ በአንድ ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለጦርና በሁለት የመድፍ ሻለቆች አጠናከርነው።

በስድስተኛ ደረጃ እስከ አሁን ከገለጥኳቸው ግምባር ቀደም የኦጋዴን የጦር ክፍሎች በኋላ ለሚገኙትና የጠላት ዋና ትኩረትና እንዲሁም ግብ ለሆኑት የሐረርጌ ደጋማ አውራጃዎችና ለድሬዳዋ መከላከል አራት የሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦሮችና አንድ ነበልባል በሚል የሚታወቅ እግረኛ ክፍለጦር፤ አንድ መድፈኛ ሻለቃ፤ አንድ ቢኤም 23 ሮኬት ባትሪና አንድ የታንክ ብርጌድ ደለደልን።

እነዚህ እስከአሁን በቆላውና በደጋው ሐረርጌ ተሠማሩ በማለት የዘረዘርኳቸው የጦር ክፍሎች በሙሉ በአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት እዝ ወይንም መምሪያ የሚመሩ ናቸው።

በሰባተኛ ደረጃ ለባሌ ክፍለሃገር አንድ የሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለጦር መምሪያውን በክፍለሃገሩ ርዕሰ ከተማ ጎባ ላይ አድርጎ ክልሉን እንዲከላከል፤ ነገሌ ቦረና ያለውን ገነኛውን ...ተኛ እግረኛ ብርጌድ በአንድ ሕዝባዊ ሠራዊት ብርጌድ፤ በአንድ ፈጥኖ ደራሽ የፖሊስ ብርጌድና በአንድ 105 ሚ/ሜ ሐዊትዘር መድፍ ሻለቃ አጠናከረን የባሌውንና የሲዳሞውን ክልል ጦር የሚመራ አንድ ንዑስ እዝ አዋሳ ከተማ ላይ አቋቋምን።

በዚህ ሁኔታ በምሥራቅና በደቡብ የጦር ግምባር ያሉትን የጦር ክፍሎች ካጠናከርን በኋላ ነው ከመሃል ሃገርና ከእናት የጦር ክፍላቸው በርቀት ተነጥለው በጠረፍ ጥበቃ ላይ የነበሩትን ፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶችና የጦር ክፍሎች ወደኋላ የመለስነው።

ጠረፍ ጥበቃ ላይ የነበሩትን ፖሊሶችና የጦር ክፍሎች ወደ ኋላ ስናገልል በጠቅላላው ኦጋዴን ክልል የነበሩትን የጦሩንና የፖሊስ ሠራዊቱን ቤተሰቦች ደግሞ በአየር ወደ ሐረር ለማገለል በተሞከረበት ጊዜ አይሻ የነበረው የ40ኛው እግረኛ ሻለቃ ጦር በታዬበት የሞራል ድቀትና ከፍያለ የሥነሥርዓት ጉድለት ምክንያት በዚሁ ጊዜ ውስጥ ከውጊያው በፊት ወደ ኋላ እንዲገለል ተደርጓል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ለመከላከል በኢትዮጵያ ምሥራቅና ደቡብ ክልሎች የጦር ሜዳዎች የየዘቻውን የመከላከያ

ሥፍራዎች የሠራዊቱን እዝና ምንዝር ካስረዳሁ ዘንድ ከኢትዮጵያ ተከላካይ ሠራዊት እንዲ ለማጥቃት የተዘጋጀውን የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊትን ትጥቆች በተለይም ብረትለበሶችን፣ ታንኮችን፣ የተለያዩ ከባድ መሣሪያዎችን፣ ተዋጊ አውሮፕላኖችንና የሠራዊቱን ዕዞች አደረጃጀት ከዚህ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

በኢትዮጵያ ምሥራቅና ደቡባዊ ክልሎች የሚኙትን ሦስቱን ክፍለሃገሮች ማለትም፣ ሐረርጌን፣ ሲዳሞንና ባሌን ለመውረር በሚያመቻቸው ሁኔታ ሦስት የግምባር ዕዞችን ማለትም፣ አንደኛውን ዕዝ አሻ ባይዶዋ፣ ሁለተኛውን ዕዝ ገልካዩ፣ ሦስተኛውን ዕዝ ሐርጌሳ፣ የእነዚህ የበላይ የሆነውን ዋናውን ዕዝ በሶማሊያ ርዕሰከተማ በሞቃዲሾ አድርጎ ነው ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወረራውን የመራው።

ሦስቱም ግምባር ቀደም ዕዞች በተቋቋሙባቸው ከተሞች ዘመናዊ የአየር ማረፊያዎች ለወረራው ሲባል የተዘጋጁ ስለእሉ ሦስቱም ዕዞች የአየር ኃይል መደቦች ከተሟሉ የአየር መቃወሚያ ተቋማት ጋር የተደራጁ ነበሩ።

ከዚህ በኋላ ሦስቱም እዞች ወረራውን ሲጀመሩ በአጠቃላይ የነበራቸውን ጠቅላ ኃይል ከወገን አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት ኃይል ጋር ለማመዛዘን እንዲችል የተዘጋጀውን ሰንጠረዥ (ሀ እና ለ) ይመለከቷል።

ሰንጠረዥ (ሀ)፡ በጦር ክፍል ተቋም የኃይል ማነጻፀሪያ

| ተ.ቁ | የክፍሎች ዓይነት | የሶማሊያ | የኢትዮጵያ |
|---|---|---|---|
| 1 | እግረኛ ክፍለ ጦር | 8 | 10 |
| 2 | ኮማንዶ ብርጌድ | 4 | የለም |
| 3 | ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር | 4 | የለም |
| 4 | ታንከኛ ብርጌድ | 4 | 1 |
| 5 | መድፈኛ ብርጌድ | 4 | 1 |
| 6 | ቢኤም 22 ሮኬት ሻለቃ (ቢኤም-23) | 7 | 1 |
| 7 | በሰጋ ሚሳኤል አየር መቃወሚያ ሻለቃ | 5 | የለም |

ሰንጠረዥ (ለ)፡ የመሣሪያ ዓይነት መጠን ማነፃፀሪያ

| ተ.ቁ | የመሣሪያዎች ዓይነት | የሶማሊያ | የኢትዮጵያ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተለያዩ ዓይነት ብረትለበሶች | 253 | 51 |
| 2 | ታንኮች | 608 | 132 |
| 3 | መድፎች | 260 | 48 |
| 4 | ቢኤም ሮኬቶች | 125 | 1 |
| 5 | አየር መቃወሚያ ሚሳኤሎች | 75 | የለም |
| 6 | ተዋጊ አይሮፕላኖች | 65 | 8 |

የሶማሊያ መሪዎች ታላቋ ሶማሊያ የሚሏትን ሃገር ለመፍጠር ያላቸውን ምኞት ተግባራዊ ለማድረግ በይፋ ጦርነት አውጀው ጠቅላላ ወታደራዊ ወረራ ከማድረግና በዓለም ሕብረተሰብ ዘንድ ህገ ወጥና ወራሪ ተብለው ላለመጋለጥና ላለመወገዝ ነፃ አውጭ የተሰኘ



ም በሰጧቸው ፀረ-አንድነትና ፀረ-አብዮት ኢትዮጵያዊያን በመረዳት ስውር ይም ህቡዕ ጦራቸውን ተጠቅመው ረራውን የጀመሩት በሰኔ ወር 1969 ም ነው።



የሶማሊያው ወራሪ ሠራዊት

የሶማሊያው መሪ ጄነራል ያድ ባሬ ወራሪውን ሠራዊት በስውር ሰናበት እንዲህ ብሎ ነበር፤ "አያት ድመ አያቶቻችሁ ሲታገሉ ኖረው ሊተሳካላቸውን ታላቋን ሶማሊያ መፍጠር ዓላማ ዛሬ ተግባራዊ ምታደርጉ እናንተ የአዲሲቱ ሶማሊያ ጆች እጅግ እድለኞች ናችሁ። ታላቋን ማሊያን በመፍጠራችሁ እድሜ ዘችሁን ራሳችሁን ከማስደሰታችሁና ጃኖችሁን ከማኩራታችሁ ባሻገር በዚች ር ታሪክና በመጪዎች ተከታታይ ውልዶች ለዘለዓለም ስትታሰቡና ትወደሱ ትኖራላችሁ። ዛሬ በኢትዮጵያ ም የለም። መላው ሐበሻ ከአማራው ቅና ለመላቀቅ በትግል ላይ ይገኛል። ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ስትገቡ የምታዩትና የምታገኙት ናንተን የሚጋተር ኢትዮጵያዊ ወታደር ሳይሆን እናንተን በጉጉት ሲጠብቅ የቆየ ፀረ-መንግሥት ኃይል ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ ከእናንተ ፊት የሚቆም ወታደር የለም። ኢትዮጵያ ገባ ስለምግብ ፍፁም አትቸገሩም አታስቡም። ኢትዮጵያ ፓፓዬው፣ ሙዝና ብርቱካን ተትረፈረፈበት ውብና የጥጋብ ሃገር ናት ሂዱና ያዟት።"

ዚያድ ባሬ እንዳለው ሳይሆን እንደ ሶማሊያ መንግሥት ሠራዊት የ15 ዓመታት ታደራዊ ሥልጠና ባያገኝም ከፍያለ አብዮታዊ ወኔ የመደብና የፖለቲካ ንቃት ያለውና ናት አገሩ ፍቅር ልቡ የነደደ ጀግና ሠራዊት ነበር፡ ምሽጉን በሚገባ ገንብቶና መሣሪያውን ቃታ ጨብጦ የሚጠብቃቸው።

የሶማሊያ ሠራዊት ወረራውን የጀመረው በእኛም በእነሱም ደቡባዊ በሆኑት ቀጠናዎች ዶሎ፣ በባሬና በጎዴ ላይ ነበር። ሰኔ 25 ቀን 1969 ዓ.ም በዶሎ የጀመረውን ጥቃት ከታተልና በማስፋፋት፣ ሰኔ 26 ቀን ባሬን ሰኔ 29 ቀን ጎዴን አጠቃ። በመሪው ጄነራል ዚያድ እንደተነገረው ከፊቱ የሚቆም አንድም የኢትዮጵያ ወታደር እንደሌለ ማመን ያለሥጋት ሙዝና ብርቱካን ለመብላት ነበር የሚንቀሳቀሰው።

ለጠረፍ ጥበቃ አነስተኛ ቁጥር ተበታትነው በመሥፈራቸው በቀላሉ ለጠላት ጥቃት ጋለጡ የሚችሉትን ፖሊሶቻችንንና የጦር ክፍሎቻችን ወደኋላ ለመመለስ ባቀድነው መሠረት ዶሎ፣ ባሬ፣ ኢሚ፣ መስሎ፣ ብርኩር፣ ሙስተሂል፣ ሸላቦና ገላዲን ወዘተ የነበሩትን ሎቻችንን አንስተን ስለነበር ጠላት ዶሎንና ባሬን የተቆጣጠረው ያለውጊያ ነው።

ከዚያድ ባሬ ንግግር በተጨማሪ የእነዚህ ሥፍራዎች መለቀቅ ያዝናናው ይመስላል ዜን አጥቅቶ ለመቆጣጠር ሲመጣ የገጠመው ሁኔታ ፍፁም ያልጠበቀው አደጋ ነው።

የጎዴን ዘመናዊ የአውሮፕላን ማረፊያ፣ ከተማውንና ራሱን ለመከላከል በሚገባ መሽጎና ጣቱን መሣሪያው ምላጭ ላይ አድርጎ የሚጠብቀው የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት እንደ መንጋ እየተንጋጋ የመጣውን የጠላት እግረኛ ሠራዊት በአየር መቃወሚያው አውቶማቲክ መድፍ፣ መትረየስና አውቶማቲክ ጠብመንጃ እንደልቡ ማጨድ ብቻ ሳይሆን ጠላት ነፍሱን ለማዳን ፊቱን አዙሮ ሲፈረጥጥ የወገን ሠራዊት ከምሽጉ እየወጣ በማሳደድ ከጠላት ለወሬ ነጋሪም እንዳይቀር ሞከረ። ከአንድ እግረኛ ክፍለጦር የጠላት ሠራዊት አብዛኛው ሲሞትና ሲቆስል እንዲሁም ሲማረክ ሕይወቱን አድኖ ለማምለጥ የቻለው ጥቂት ነበር።

እቅድ አንድ የተባለው የሶማሊያዎች የመጀመሪያው ወረራ ለዓለም ብቻ ሳይሆን ለሶማሊያ ሕዝብና ለሠራዊቱም ምስጢር ስለነበረ ይመስለኛል በአንዱ ክፍለሠራዊት ላይ የደረሰውን አደጋ ወይንም ውድቀት ሌላው ስለማያውቅ ሰኔ 27 ቀን በተመሳሳይ ጊዜና ሁኔታ የቀብሪደሐርንና የዋርዴን ከተማ አጠቁ።

ቀብሪደሐር ላይ የነበረው የኛ አንድ ሻለቃ ታንከኛ ጦርና ዋርዴር ላይ የነበረው አንድ ሻምበል ብረት ለበስ ጦር ከተቀረው እግረኛ ጦርና ከአየር ኃይላችን ጋር በሕብረት የመልሶ ማጥቃት ውጊያ እያሳደዱ በጠላት ላይ ያደረሱት ጉዳት ከጎዴውም የከፋ ነበር።

ይህንን ጦር የመሩትና ይህንን የመሰለ ፍፁም ያልጠበቁት እልቂት የደረሰባቸው የሶማሊያ የጦር መኮንኖች "የአዲስ አበባው መንግሥት ፀር የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአበባ ይቀበላችኋል። በፊታችሁ የሚቆም አንድም ኢትዮጵያዊ ወታደር የለም ብሎ 'አፈወይን' አስፈጀን በማለት በፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ ላይ ከፍ ያለ ጥላቻ ስለአደረባቸው የደረሰባቸውን እልቂት በያዟቸው ወታደራዊ ሬዲዮኖች ለመላው የሶማሊያ ሠራዊት በማዳረስ ፀረ-ዚያድ አመፅና ቅስቀሳ ጀመሩ። ለበላይ እዛቸውም እንታዘዝም በማለት ከቁጥጥር ውጭ ሆኑ። ለፕሬዚዳንት ዚያድ 'አፈወይን' የተሰኘ ስም የሰጡትም በዚህ ጊዜ ነው። 'አፈወይን' ማለት በሶማሊኛ አፈሰፊ ወይንም ክፍት አፍ ማለት ነው።

ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ዕቅድ አንድ ባለው የወረራ ዕቅድ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ እምርጎ ያስገባው የሶማሊያ ወራሪ እግረኛ ሠራዊት ላይ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ባደረሰበት ከባድ ጉዳት አብዛኛው ከውጊያ ውጭ ሆኖ ሳለ በደቡብ ሶማሊያ ክልል ባይዶዋ ላይ የሚገኘው አንደኛው ዕዝ በሥሩ ያሉትን ተዋጊ የጦርክፍሎች ባሌንና ሲዳሞን ወርረው በቁጥጥራቸው ውስጥ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ በመስጠቱ በሲዳሞ በኩል የዘመተውን መጠን ሰፊ እግረኛ ሠራዊት በግምባር ቀደምትነት ይመራ የነበረው አንድ እግረኛ ብርጌድ ነገሌ ቦረና ሲደርስ የአየርኃይላችን ያሉትን ተዋጊ አውሮፕላኖች አንስቶ በመትረየስ፣ በሮኬትና በቦንብ በመቀጥቀጥ በጥቂት ሰዓት ውስጥ በሠራዊታችን የተቆጠሩ 300 ሦስት መቶ የጠላት ወታደሮች ተሰውተውና ከዚህ በላይ ቆስለው የብርጌዱ ሠራዊት ከውጊያ ውጭ በመሆኑ ከኋላ ይጓዝ የነበረው ዋናው እጥቂ ሠራዊት በሙሉ ፊቱን አዙሮ ወደ መጣበት በመፈርጠጥ ተመለሰ።

የዚህ ሙሉ በሙሉ የተደመሰሰ ብርጌድ አዛዥ የነበረው ግለሰብ ጦርነቱ በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ድል አድራጊነት ከተደመደመ በኋላ የዚያድ ባሬ መንግሥት ተቃዋሚ በመሆን ወደኢትዮጵያ መጥቶ የሶማሊያ ነፃ አውጭ ዲሞክራቲክ ግምባር የተባለውን ድርጅት ያቋቋመውና ዛሬ እኔ ይህንን ታሪክ በምጽፍበት ጊዜ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና በወያኔ ጥምር ርዳታ የሶማሊያ ጊዜያዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት የተባለው ኮሎኔል አብዱላሂ ዮሱፍ ነው።



በደረሰባቸው ያልተጠበቀ ከባድ አደጋዎች የተደናገጡት የሶማሊያ የጦር ኃይል አመራር ከፍተኛ አካላት ብቻ ሳይሆኑ የመንግሥት ከፍተኛ የአመራር አካላትም ጭምር ሞቃዲሾ ላይ ያለውና በፕሬዚዳንቱ የሚመራውና 'ከፍተኛ አብዮታዊ የዕዝ ማዕከል' የተባለው የዕዝ አካላት ሰኔ 28 ቀን 1969 ዓ.ም ተሰብስቦ ኢትዮጵያን የመውረር ዕቅድ ሁለት ያለውን ጠቅላላና ግልፅ ወታደራዊ የወረራ ዕቅድ አፅድቆ ጦርነቱን ይፋ በማወጅ ሠራዊቱን ክፍላተ ሃገሮቻችንን ማለትም፣ ሐረርጌን፣ ባሌንና ሲዳሞን በእግረኛና በሜካናይዝድ ሠራዊት አጥለቀለቃቸው።

በእንባቢ ዘንድ ይታወስ እንደሆን በታጠቀው መሣሪያ ዓይነትና መጠን ከወገን ሠራዊት በእጅጉ የሚልቀውን የጠላት ሜካናይዝድ ወይንም ብረት ለበስ ሠራዊት ለማጥቃት የኦጋዴን በረሃማ መሬት ላይ ቀላልመሣሪያ በታጠቀ እግረኛ ሠራዊት ለመቋቋም መሞከር አስፈላጊ ያልሆነ መስዋዕትነትን የሚያስከፍለን ብቻ ሳይሆን ወራሪውን ሠራዊት በአጭር ጊዜ መልሶ ለማጥቃት እማይቻልበት ውድቀት ላይ እንደሚያደርሰን በመታወቁ የአገራችንን ምሥራቃዊና ደቡባዊ ጠረፎች ያለውጊያ በመልቀቅ ከፊሉንና ወደደጋው ተቃረቢያ የሆኑትን ስትራቴጂካዊ ቆላማ ሥፍራዎች ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በእንስተኛ እግረኛ ሠራዊት እየተከላከልን ለጠላት ታንኮችና ብረትለበስ ተሽከርካሪዎች በማይመቹት ደጋማ ሥራጃዎች ላይ ዋናውንና ሰፊውን ኃይላችንን አሠማርተን እስከመጨረሻው የምንቆይበትን የመከላከያ ሥፍራ ያስያዝነው፣ በግምባር ቆላማዎቹን አውራጃዎች የሚከላከለው ሠራዊት እስከመጨረሻው በመከላከል እንዲሰዋ ሳይሆን የጠላትን ግስጋሴ በመምታት ኃይሉን ለመቀናነስና ለማዘግየት ነበር።

በዚህ የውጊያ ሥልት መሠረት ጠላት የወረራ ዕቅድ አንድ ባለው ማጥቃት ወደ አገራችን እምርጎ ያስገባውን እግረኛ ሠራዊት በደቡብና በምሥራቅ ድባቅ እየመታ የደመሰሰው አብዮታዊ ሠራዊታችን በጠላት ሁለተኛ የወረራ ዕቅድ የመጣውን በአያሌ ከባድ መሣሪያዎች ድጋፍ የተገነባ ሜካናይዝድ ወይንም ብረትለበስ ሠራዊት ለመመከት ባለመቻሉ ቆላማውን የአገራችንን ዳርቻ መሬት በአጠቃላይ፣ ጎዴ፣ ቀብሪደሐርና ዋርዴር፣ ደገሐቡርና ጅጅጋ በተለይ ከሐምሌ 2 እስከ 11 ድረስ ባሉት ቀናቶች ውስጥ ጠላት እጅ ወደቁ።

አብዮታዊ ሠራዊታችን ጎዴን፣ ቀብሪደሐርንና ዋርዴርን የለቀቀው በበላይ አካል ትዕዛዝ ሲሆን ሦስቱም ክፍሎች ቀደም ብሎ እንደገለፅኩት በጠላት እግረኛ ሠራዊት ላይ ከፍ ያለ እልቂት አድርሰው በሥልታዊ ማፈግፈግ ነው። ከያሉበት ወደ ሐረር በአድካሚ ረጅም ጉዞ ተመልሰው በመግባት እንደገና ወደ ድሬዳዋና ጅጅጋ በመሔድ ሁለቱን የጦር ግንባሮች በከፍተኛ ደረጃ ሊያጠናክሩ ቻሉ።

ጠላት ለደጋማው ክልል መቃረቢያና እስትራቴጂካዊ ይዞት ያላቸውን ደገሐቡርንና ጅጅጋን ያጠቃውና ጎዴን፣ ቀብሪደሐርንና ዋርዴርን ከያዘ በኋላ ለሳምንት ያህል ዘግይቶ ነው።

ደገሐቡርንና ጅጅጋን ከማጥቃቱ በፊት ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ከሶቪየትሕብረት መንግሥት ጋር የተዋዋለውን ሁለገብ ውለታዎች ጥሶ የሶቪየትሕብረት መንግሥት ወታደራዊ አማካሪዎችና ሲቪል ዲፕሎማቶች ከሐምሌ 1 ቀን 1969 ዓ.ም ጀምሮ በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ ከአገሩ እንዲወጡ አዘዘ።

ይህ የሶማሊያ መንግሥት ውሳኔ ለኛ ሁለት ጠቃሚ መልዕክቶችን አስተላልፏል። አንደኛው መልዕክት ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት የወረራ ዕቅድ ሁለት ያለውን ጠቅላላና ግልፅ ወታደራዊ ወረራ ለማወጅ መዘጋጀቱን ያስገነዘበን ሲሆን፣ ሁለተኛው መልዕክት

ሶቭየቶች በዚያ ሁኔታ ተገድደውና ተዋርደው ከሶማሊያ በመውጣታቸው ምክንያት በእኛ እጅ ሶማሊያዎችን ለመበቀል ሲሉ የምንፈልገውን መሣሪያ በምንፈልገው መጠን በገፍና በለጋሥነት ወዲያው እንደሚያቀርቡልን አስገንዝበን ነበር።

ከዚህ በላይ በገለፅኳቸው ሁለት በወታደራዊ አመለካከት ስትራቴጂያዊ ይዞታ ባላቸው በደገሐቡርና በጅጅጋ ከተሞች መሽገው ጠላታቸውን ይጠባበቁ በነበሩት በወገን የጦር ክፍሎች ላይ ጠላት የወረራ ዕቅድ አንድ በማለት ያሠማራው እግረኛ ሠራዊት ጥቃት ስላልሠነዘረባቸው የመጀመሪያ ከባድ የውጊያ እጣቸው በጠላት ሁለተኛ የወረራ ዕቅድ መሠረት ከወራሪው ሠራዊት ብረት ለባሾች፣ ታንኮች፣ ሮኬት ወንጫፊ ከባድ መሣሪያዎችና ከአያሌ የተለያዩ መድፎችና ከጠላት ተዋጊ አይሮፕላኖች ጋር መጋፈጥ ስለሆን እጅግ የከፋ መራራ ውጊያ ነበር።

የደገሐቡርን ከተማ ይከላከል የነበረው አብዮታዊ ሠራዊታችን የደገሐቡርን ከተማ በሚገዛው ከፍተኛ መሬት ላይ ጠንካራ ምሽግ ከመመሸጉ በላይ 4.2 ኢንች ከባድ አዳፍኔውን፣ 106 ሚ/ሜትር 75 ሚ/ሜትርና 57 ሚ/ሜትርና 3.5 ኢንች ባዙቃውን ከዋርሶ ሥሪት ፀረ-ታንክ መሣሪያዎች ጋር አቀናጅቶ በሚገባና በቆራጥነት እየተጠቀመ የጠላትን ብረት ለበስ ተዋጊ ተሽከርካሪዎችና ታንኮች በርቀት እያጋየ ለጠላት ጥቃት ሳይበገር ለሳምንታት ያህል ጊዜ ብርቱ ተጋድሎ ካደረገ በኋላ ነው የሰው ኃይሉ እየተመናመነ ሲሔድ የጠየቀውን ረዳት ጦር ልንልክለት ባለመቻላችን የጠላትን ከበባ በሌሊት ሠብሮ በመውጣት ሥልታዊ ማፈግፈግ አድርጎ የጅጅጋን ከተማ ከሚከላከለው ሠራዊት ጋር እንዲቀላቀል በተሰጠው የበላይ ትዕዛዝ ነው ደገሐቡርን የለቀቀው።

በደቡብ ግምባር ማለትም በባሌና በሲዳሞ ክፍለ ሃገሮች ጠላት ዋና አላማው ወይንም ግቡ ያደረጋቸውን ጎባ የሚባለውን የባሌ ክፍለ ሃገር ርዕሰ ከተማና የነገሌ ቦረናን ከተማ ይከላከሉት የነበሩትን የወገንን አብዮታዊ የጦር ክፍሎች የገጠሟቸው የጠላት ብረት ለበስና ታንከኛ ክፍሎች ሳይሆኑ በመድፎች የተደገፈ እግረኛ ሠራዊትና አገራቸውን ከድተው የጠላት ምንደኛ የሆኑ ጠባብ ብሔርተኛ ኢትዮጵያዊ ገንጣይና አስገንጣይ ድርጅቶች ስለነበሩ እነኝህ በሕብረት ደጋግመው የሠነዘሩባቸውን ጥቃቶች እየመከቱ በመመለስ አንደኛው አብዮታዊ የኢትዮጵያ ሠራዊት በሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት ላይ መልሶ ማጥቃቱን እስከሠነዘረበት ጊዜ ድረስ ለጠላት ሳይበገሩ ሁለቱንም ከተሞች ከጥቃት ለማዳን ችለዋል።

የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት በወረራ ዕቅዶቹ አንድና ሁለት በምሥራቅ ኢትዮጵያ ቆላማ አውራጃዎች ማለትም በቀላፎ፣ በሙስተሂል፣ በጎዴ በቀብሪደሐር፣ በገላዲን በዋርዴርና በደገሐቡር ላይ በተለይም በአንደኛው ዕቅድ በግልፅና በሙሉ ኃይሉ የሰነዘረው ጥቃት እንደአሰበው በቀላሉ ግቦቹን ያስጨበጠው ሳይሆን ከፍ ያለ መስዋዕት ያስከፈለው ቢሆንም በነበረው የመሣሪያ የበላይነት ወረራው ስኬታማ ከሆነለት በኋላ የቆላው ክልል አካል በሆነው በጅጅጋ ከተማና አካባቢው ላይ ጥቃት የሠነዘረው ጥቂት ዘግይቶ በመጨረሻ ነበር።

ጅጅጋ ለሰሜን ሶማሊያ ርዕሰከተማ ለሃርጌሣ ትይዩ የሆነ፣ ሃርጌሳ ላለው ሦስተኛው ወታደራዊ ዕዝና እንዲሁም በዚህ ዕዝ ሥር ለሚመራው በመጠኑም ሆነ በዓይነቱ ከተቀሩት የሶማሊያ ክፍለ ሠራዊቶች ሁሉ በጣም ለሚልቀው ሠፊ ሠራዊት ከተቀሩት አውራጃዎች ሁሉ በጣም ቅርብ ከመሆኑ ባሻገር በአየርንብረቱ ነፋሻነት ከተቀሩት ቆላማ አውራጃዎች ሁሉ የሚሻል፣ መልካምድሩ ምንምዓይነት የተፈጥሮ መሰናክል የሌለበት ቅልጥፍ ያለ ሜዳማ መሬት በመሆኑ ተዋጊ ብረትለበስ ተሽከርካሪዎችንና ታንኮችን በገፍ ለታጠቀው ወራሪ የሶማሊያ ጦር ንቅናቄ በጣም አመቺ ነው።



በጠቅላላው ከስልሳ የማይበልጡ እሮጌ ብረት ለበሶችና ታንኮች ለታጠቀውና በቂ ከባድ መሣሪያ ድጋፍ ለሌለው የወገን ጦር መከላከል የተፈጥሮ ከለላና መከታ የሌለው ብቻ ሳይሆን ወራሪው የሶማሊያ ሠራዊት ለሚመጣበት መሬት የጅጅጋ ከተማና የወገን ጦር የመከላከያ ሥፍራ ተዳፋት ስለሆነ ጠላትን በሩቅ ለመመልከት ባለመቻሉም ውጊያውን አስቸጋሪ አድርጎት ነበር።

ጠላት መቼ፣ እንዴትና በየትኛው አቅጣጫ ሊመጣ እንደሚችል ለመተንበይ አስቸጋሪ ከመሆኑም ሌላ እኔ ከጓዶቼ ጋር እቦታው ላይ እስከንገናኝ ድረስ ጦሩን ይመራ የነበረው የሜካናይዝዱ ብርጌድ አዛዥ የነበረው ታንከኛ መኮንን በመሆኑም ይመስለኛል አብዮታዊ ሠራዊታችን ጠንካራና ቋሚ መከላከያ ምሽግ አልነበረውም።

የወገን ጦር የያዘው የመከላከያ ወረዳ ሜዳማና እጅግ ሰፊ በመሆኑ እግረኛውን ጦር በፈለገ ጊዜ ጠላት ወደመጣበት አቅጣጫ ለማንቀሳቀስ በ10ኛው ሜካናይዝድ ብርጌድ ጠቅላይ ሠፈር አካባቢና በካራመራ ተራራ ግርጌ ተከማችቶ ጊዜያዊ የመከላከያ ሥፍራ በመያዝ የጠላትን መምጫ አቅጣጫ ለመቆጣጠር ይሞክር የነበረው መትረየሶችንና ፀረ-ታንክ መሣሪያዎችን በጠመዱ ጂፕ ተሽከርካሪዎችና፣ በሠራዊት ማጓጓዣ ብረትለበስ ተሽከርካሪዎችና በታንኮች ቅኝት ነበር።

በቆላዎቹ የአጋዴን አውራጃዎች እንደወሰን ሆኖ ከደጋዎቹ አውራጃዎች በመነጠል የሚከልላቸው፣ ለሐረርጌ በር ነው የምንለው፣ ለመከላከል ውጊያ በእጅጉ የሚያመቸውና ካራመራ በመባል የሚጠራው እጅግ ረጅም የተራራ ሠንሰለት የሚገኘው የጠላትን ጥቃት እንከላከልበታለን ከምንለውና የሕዝቡ መኖሪያ ከሆነው የጅጅጋ ከተማ ወደኋላ ከአምስት ኪ/ሜትር በላይ እርቆ ነው።

በዚህ የመከላከል ውጊያ የካራመራ ሰንሠለታማ ተራራ የሰጠን አገልግሎት ቢኖር ጠላትን እግረኛና ብረትለበስ የጦር ክፍሎች በቀን ብርሃን ንቅናቄ በመስክ መነፅር፣ የተዋጊ አይሮፕላኖችን ንቅናቄ በራዳር ከሩቅለመቆጣጠር ማስቻሉ ብቻ ነበር።

የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት በአገራችን ደቡብና ምሥራቅ ዳር ሃገር ቆላማ አውራጃዎች ላይ ከተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር በአጠቃላይ ካደረጋቸው ውጊያዎች ሁሉ የጅጅጋ ውጊያ የተለየና አያሌ የመሣሪያ ዓይነቶችና የሁለቱም አገራት የአየርኃይል ሠራዊቶች የተሳተፉበት መጠነ ሰፊና ከባድ ውጊያ ነበር።

የጅጅጋን ውጊያ ልዩና ከባድ ያደረጉት ምክንያቶች ሁለት ናቸው። አንደኛው፣ ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት አንድ አምስተኛውን የኢትዮጵያ መሬት ወይንም ሦስቱን የደቡባዊና ምሥራቃዊ ክፍለሃገሮች አለኝታዎቼ ናቸው ቢልም በሠራዊት ሥምሪት ረገድ ዋናውን ትኩረት በመስጠት ከጠቅላላው የምድርጦሩ ሰባ በመቶውንና መላ አየር ኃይሉን ያሰለፈው በምሥራቅ ግምባር ማለትም በሐረርጌ ክፍለሃገር ላይ ስለነበረ፣ ሁለተኛው፡ እኛም በኩል የጠላትን ፍላጎትና ትኩረት ከውጊያው በፊት ቀደም ብለን የተገነዘብን በመሆናችንና ጅጅጋ በሐረርጌ ክፍለሃገር በርና በወታደራዊ አመለካከት ስትራቴጂያዊ አቀማመጥ ያለው በመሆኑ ጅጅጋ ወይንም ሞት ብለን ያለአግባብ ሠራዊታችንን ልንሰዋ ባንፈልግም በተቻለ መጠን ብርቱ ተጋድሎ ለማድረግ መወሰናችንን ጠላትም ከሠራዊታችን እኩል የተገነዘበው ስለሆነ ነው።

የጠላትንና የወገንን ኃይል፣ ዓይነትና መጠን ለማመዛዘን ይቻለው ዘንድ የወራሪውን ሠራዊት የውጊያ አደረጃጀት፣ ሠራዊቱ በየዕዙ ለወረራ የተከፋፈላቸውን የውጊያ ቀጠናዎችና የተጠቀመባቸውን የውጊያ ሥልቶች ከዚህ እንደሚከተለው አቅርባለሁ፡-

ጠላት ሠራዊቱን ለወረራ ያደራጀውና ያዘጋጀው በሦስት ከፍተኛ ወታደራዊ የዕዝ ተቋማት በመከፋፈል ሲሆን ከእነዚህም ሦስተኛው ዕዝ በሰሜን ሶማሊያ ርዕሰ ከተማ ሐርጌሳ ላይ በጅጅጋ ከተማ ትይዩ ተቋቁሞ በሥሩ ከዚህ የሚከተሉትን የጦር ክፍሎች አካቷል።

1ኛ/ 4 እግረኛ ክፍለጦሮች
2ኛ/ 2 ኮማንዶ ብርጌዶችን
3ኛ/ 1 ሜካናይዝድ ክፍለጦርን
4ኛ/ 2 የታንክ ብርጌዶችን
5ኛ/ 2 የመድፍ ብርጌዶችን
6ኛ/ 2 አየር መቃወሚያ የቦልጋ ሚሳይል ሻለቆችን

ሁለተኛው ዕዝ በማዕከላዊው ሶማሊያ፣ በማዕከላዊው ኦጋዴን አቅጣጫ ገልካዩ ከተማ ላይ ተቋቁሞ በሥሩ ከዚህ የሚከተሉትን የጦር ክፍሎች አካቷል።

1ኛ/ 2 እግረኛ ክፍለጦሮችን
2ኛ/ 1 ኮማንዶ ብርጌድን
3ኛ/ 1 ሜካናይዝድ ክፍለጦር
4ኛ/ 1 የታንክ ብርጌድ
5ኛ/ 1 መድፈኛ ብርጌድን
6ኛ/ 1 አየር መቃወሚያ ቮልጋ ሚሳኤል ሻለቃ

አንደኛው ዕዝ በደቡብ ሶማሊያ በደቡብ ኦጋዴን፣ በባሌና በሲዳሞ አቅጣጫ ባይዶዋ በሚባለው ከተማ ላይ ተቋቁሞ በሥሩ ከዚህ የሚከተሉትን የጦር ክፍሎች አካቷል።

1ኛ/ 2 እግረኛ ክፍለጦሮችን
2ኛ/ 1 ኮማንዶ ብብጌድን
3ኛ/ 1 የታንክ ብርጌድን
4ኛ/ 1 የመድፍ ብርጌድን
5ኛ/ 1 አየር መቃወሚያ ቮልጋ ሚሳኤል ሻለቃ።

ከዚህ በላይ ካለው የኃይል ዝርዝር በተጨማሪ እያንዳንዱ እግረኛ ክፍለ ጦር በውስጡ አንድ የመድፍ ሻለቃና አንድ የታንክ ሻለቃ በአካልነት ይዟል።

በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት አደረጃጀት አንድ መድፈኛ ሻለቃ የሚኖሩት መድፎች 12 ሲሆኑ የሶማሊያዎች 18 ናቸው።


ሩሲያዊያን ከጥንት ጀምሮ በመድፍ ውጊያ የታወቁ ባለሞያዎች ብቻ ሳይሆኑ ሠራዊታቸው በመድፍ ያመልካል ለማለት ይቻላል። ይህ እውነታ በተለያዩ ጊዜያትና የጦር ሜዳዎች ታይቷል።

ሶቭየቶች ለሶማሊያ ሠራዊት ከሚያስፈልገው በላይ በለጋስነት በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ መድፎችን ከመስጠታቸው ሌላ አጠቃቀማቸውን በሚገባ አስተምረዋቸዋል።

የሶማሊያ መድፈኞች ያሏቸውን መድፎች ሁሉ በማሰባሰብ በተከላካዩ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ላይ የጥይት ዝናብ ከማዝነብ ባሻገር ኢላማቸውንም በሚገባ ነበር የሚመቱት።

ያላንዳች አጋዥ ከባድ መሣሪያ ድጋፍ በነፍስ ወከፍ መሣሪያው ብቻ በኦጋዴን በርሃ አገሩንና አብዮቱን ለማዳን በከፍተኛ አብዮታዊ ወኔና ጀግንነት የተዋጋው የኢትዮጵያ






የጦር ክፍሎችን ማንነት የሚገልጹ ወታደራዊ ምልክቶች

ዮታዊ ሠራዊት ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ዕቅድ ሁለት ባለው ሁለተኛና ጠቅላላ ታደራዊ ወረራ አብዛኛው ከጠላቱ ጋር የእጅ በእጅ ውጊያ ሲያደርግ ቀርቶ የጠላቱን ፈኛ ሠራዊት በዓይኑ አላየም ማለት ይቻላል። መከላከያ ምሽጉን እየለቀቀ ለማፈግፈግ ገደደው በጠላቱ የመድፍ ድብደባ ብቻ ነው። የሶማሊያ አየር ኃይል እንደ መድፈኛው ቢሆን ኖሮ የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት በሰባት ወር ካገራችን ለማስወጣት ስለመቻላችን ጠራጠራለሁ።

የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት በኢትዮጵያ አብዮታዊ ተከላካይ ራዊት ላይ በአጠቃላይ የሠነዘረውን ጥቃት ይዘትና ጥልቀት ለመረዳት በኢትዮጵያ ለቲካ ካርታ ላይ የተቀመጠውን ሥዕላዊ መግለጫ ይመለከቷል።

ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ግልፅና ጠቅላላ ወታደራዊ ወረራ እንዳያደርግ ሲከላከል የነበረውን የሶቭየት ሕብረት መንግሥትን የቆየ ወዳጅነትና የተራድኦ ውለታ ጥሶ ወታደራዊ አማካሪዎችንና ሲቪል ዲፕሎማቶችን ከአገሩ ማስወጣቱ ለጠቅላላ ወረራ መዘጋጀቱን የሚገልፅ መልዕክት ነበር ማለቱ ይታወሳል።

ከሐምሌ 5 እስከ ነሐሴ 11 ቀን ድረስ በተደረጉት ውጊያዎች በሲዳሞ፣ ዶሎና ባሬ፣ በባሌና ኤልከሬ፣ በመስሎና ጊኒር፣ በሐረርጌ ቀላፎና ሙስታሂል፣ ጎዴ ቀብሪደሐር፣ ገላዲን፣ ዋርዴርና የደገሐቡር አውራጃዎች በጠላት እጅ በመውደቃቸው ከእነዚህ በኋላ የመጨረሻው የቆላው ምድር ወይንም የኦጋዴን ክልል ውጊያ የሚደረገው በጅጅጋ እንደሆነ በጠላትም በወገንም ዘንድ የታወቀ ነበር።

በተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት የወረራ ዕቅድ አንድ መሠረት ያለከባድ መሣሪያና ብረትለበሶች ድጋፍ ጥሩ የደፈጣ ውጊያ ሥልጠና ያላቸውን ኮማንዶ ብርጌዶቹንና ከፊሉን እግረኛ ሠራዊት በሁለተኛው የወረራ ዕቅድ መሠረት ለሚዘምትብን ዋናው ሠራዊት መንገድ ለመጥረግና ለድል በማመቻቸት ቀደም ካለው የቆላውን ምድር በመሻገር በመላው የሐረርጌ ደጋማ አውራጃዎች ውስጥ በመሰግሰግ ድምፃቸውን አጥፍተው ስለመቀመጣቸው በአስተማማኝ መረጃ ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ በእኛ በኩል አልነበረም።

ከሃያ ሺህ የማያንስ የጠላት ሠራዊት በሐረርጌ ደጋማ ክልሎች ውስጥ ሠርጎ ማድፈጥ ብቻ ሳይሆን የወራሪው ሠራዊት የአየር ኃይልና መድፍ አስተኳሽ ግምባር ቀደም ተመልካቾችና ወታደራዊ ሰላዮች እመሀላችን ተገኝተው እንጀት ጉበታችንን ገላልጠው ሲመለከቱ ልንነቃባቸውና ልናውቃቸው ያልቻልነውኦሮምኛ ቋንቋ የሚናገሩት ገንጣይና አስገንጣዮች፤ በተለይም ኦሮሞ እስላሚያ የተባለው የሶማሊያ መንግሥት ምንደኛ ኦሮምኛና ሶማሊኛ ተናጋሪውን ኢትዮጵያዊ ሕዝብ "የሶማሊያ መንግሥት ሠራዊት የመጣው ከሐበሻ ኢምፔሪያሊዝም እናንተን ነፃ ለማውጣት ነው" ብለው በግድም በውድም በማስተባበር ከጠላት ጋር ስላሰለፉት ነው።

በጠቅላላው የሶማሊያ መንግሥት የጦር ኃይል ሰባ በመቶው የሚሆነውና ሃርጌሳ ከተማ በሚገኘው ወታደራዊ ዕዝ ሥር በጅጅጋ ግምባር ለማጥቃት ትዕዘዝ ሲጠባበቅ፣ እግረኛውና ሜካናይዝድ እግረኛው፣ ታንከኛውና መድፈኛው ሠራዊት በሁለቱ አገሮች የጋራ ድንበር አካባቢ በሚገኙትና ቆልጆት፣ ቶጎጫሌ፣ በሮማና ገቢሌ የሚባሉና የተቀራረቡ ሥፍራዎች ላይ በመካበት ለወረራ እንዳሰፈሰፈ እናውቅ ነበር።

ከኢትዮጵያ ወገን የሶማሊያን መንግሥት በአያሌ ከባድ መሣሪያዎች የሚረዳ ብረትለበስ ሠራዊት በጅጅጋ ሜዳ ላይ ለመመከት የሚመጥን ጦር የሌለን በመሆኑ ውጊያው ለኛ በእጅጉ አዳጋች ቢሆንም፤ እግረኛ ሠራዊታችንን በጅጅጋ ከተማ ዙሪያ ከሃያ እስከ ሰላሳ ኪ/ሜትር ርቀት ላይ ባሉ ወታደራዊ መሬቶች ከፊሉን በአስፈለገ ጊዜ ወደሚፈለገው ሥፍራ ለማንቀሳቀስ በሚያስችል ሁኔታ በደጀን ወይንም በተጠባባቂነት በማስቀመጥ ያሉንን ታንኮችና ብረትለበሶች በሦስት አቅጣጫ ከዚህ እንደሚከተለው አሠለፍናቸው።

አንደኛውን ክፍል ወራሪው ጠላት በተካበተበት አቅጣጫ ከቶጎጫሌ ከተማ በስተኋላ አሮሬሳ ኮረብታ ሥር በጅጅጋ ከተማ ሰሜን ሁለተኛውን ክፍል ከጅጅጋ ከተማ በስተምዕራብ በጭናክሰን በስተምሥራቅ በተፈሪ በር አቅጣጫ፤ ሦስተኛውን ክፍል ከጅጅጋ ከተማ በስተምሥራቅ በሃያ ኪ/ሜትር ርቀት ቀብሪቢያን በምትባል መንደር አካባቢ።

ወቅቱ የሰብል ወቅት በመሆኑና እነዚህ የገለጥኳቸው ሥፍራዎች በሙሉ በማሽላ አዝርዕት የተሸፈኑ ስለነበሩ የእኛ ታንኮችና ብረት ለበሶች የጠላትን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩት



በማሽላ ተክሎች ውስጥ ተከልለው ሲሆን የወገን ጦር አይመለከታቸው እንጅ የጠላት እግረኛ ሰላዮችና የመድፍ ተመልካቾችም በማሽላ ተክሎች ተከልለው የእኛን እንቅስቃሴ ይቆጣጠሩ የነበሩ ከመሆናቸው ሌላ በአካባቢው የሚኖሩት ሶማሊኛ ተናጋሪ ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች ዘላኖች በሙሉ የጠላት ሰላዮች ነበሩ።

የወገን ጦር እነዚህን ከዚህ በላይ የገለጥኳቸውን የመከላከያ ሥፍራዎች ይዞ ጠላትን መጠባበቅ የጀመረው ከሐምሌ 11 ቀን ጀምሮ ሲሆንና ጠላት በበኩሉ ሐምሌ 11 ቀንን የሚጠብቀው በሚገባ ሲመዘግብ የቆየ ይመስላል፡ ሐምሌ 12 ቀን ጎህ ሲቀድ በሦስቱ የወገን መከላከይ ክፍሎች ላይ የጠላት የመድፍ ብርጌዶችና ቢኤም 23 ሮኬት ወንጫፊ ሻለቆች የእሳት ዝናብ ማዝነብ ጀመሩ።

ጠላት የመድፍና የሮኬት ጥይቶችን የሚያዘንበው ጅጅጋን በሚከላከለው ሠራዊታችን ላይ ብቻ ሳይሆን ጎባንና ነገሌን በሚከላከሉት ጦሮቻችንም ላይ ስለነበረ ስምንት ተዋጊ ጄቶች የነበረው አየርኃይላችን ያለእረፍት ከአንዱ ክፍለ ሃገር ወደሌላው እየተዘዋወረ እንደ የብሱ ሠራዊት እንደ አየር ኃይል ብቻ ሳይሆን እንደወገን መድፈኛም ሆኖ የጠላትን እግረኛ ጦር ብረትለበሱን መድፈኛውን ክፍል በመደብደብ ከፍ ያለ ጉዳት ቢያደርስም በተለይ በጅጅጋ ግምባር ጥይት እንደዝናብ ያለማቋረጥ የሚያዘንቡትን የጠላት መድፈኞች ሊገታ አልቻለም።

በመድፍ በሮኬት ድብዳባ ብቻ በግምባር የሚከላከሉት የወገን ጦሮችና ብረት ለበስና ታንኮች በብዛት ጉዳት ስለደረሰባቸው ከጠላት መድፎች እርቀት ውጭ ወደ ኋላ አፈግፍገው ሁለተኛውን አማራጭ የመከላከያ ስፍራ እንዲይዙ ትዕዛዝ ከበላይ አካል ተሰጥቷቸው ሐምሌ 15 ቀን ሥልታዊ ማፈግፈግ ሲያደርጉ በዋናው ግምባር በቶጎጫሌ የተሰለፈውን ጦር ይመራ የነበረው ሻለቃ አስፋ ተሰማ የሚባል መኮንን ጂፕ ተሽከርካሪ ላይ ሆኖ በማሽላ ተክሉ ውስጥ ታንኮችን በመምራት ላይ እንዳለ የታንክ አሽከርካሪዎችን እይት የሚሸፍነው የማሽላ ርዝመት አውኮ ስለነበር የወገን ከባድ ታንክ ከነጂፕ ተሽከርካሪው ደፍጥጦ ስለገደለው ማፈግፈግ ላይ ያለው ጦር አዛዡ ላይ በደረሰው አደጋ እጅግ ከማዘኑና ከመረበሹ ሌላ ዕዝና ቁጥጥርም ለጥቂት ጊዜ ወይንም ሰዓት ተበላሽቶ ነበር ለማለት ይቻላል።

ከጅጅጋ በስተምዕራብ በጭናክሰን፣ በጎግቲና በተፈሪ በር አቅጣጫ ይከላከል የነበረውን ክፍል አዛዥ ሻለቃ ጠና ጋሻው የሚባለው መኮንን በሥልታዊ ማፈግፈግ ጦሩን ወደ ሁለተኛው ተለዋጭ መከላከያ ወረዳ ጂፕ ተሽከርካሪ ላይ ሆኖ በመምራት ላይ እንዳለ የጠላት የመድፍ ስብስብ ተኩስ ድብደባ ከነተሽከርካሪው በመደምሰሱ በሚመራው ክፍል ላይ የቶጎጫሌውን ግምባር የመሰለ ችግር ተፈጥሮ ነበር።

ሦስተኛውና በደቡብ ኦጋዴን አቅጣጫ በቀብሪቢያን አካባቢ የሚከላከለውም የወገን ጦር ሁኔታ አዛዥ አይሰዋ እንጅ በወረደበት የመድፍ ጥይት ዝናብ፤ ሰውም መሣሪያው ተጎድቶ ከጠላት የመድፍ እርቀት ውጭ ወደ ሁለተኛው ተለዋጭ የመከላከያ ወረዳ ሥልታዊ ማፈግፈግ እንዲያደርግ ከሌሎች ጋር ተመሳሳይ ትዕዛዝ ተሰጥቶታል።

የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ከጅጅጋ ከተማ መከላከያ ሦስቱ ግምባር ቀደምና የመጀመሪያ መከላከያ ወረዳ ለቆ ወደኋላ ማፈግፈጉን ያስተዋለውና በቶጎጫሌ ግምባር የተሰለፈው የጠላት የታንክ ብርጌድ ከበላይ አካል በተሰጠው ትዕዛዝ ይሁን ወይንም በራሱ ተነሳሽነት በእግረኛ ወይም በሜካናይዝድ እግረኛና እንዲሁም በአየር መቃወሚያ ሳይጠበቅ ጊዜም ሳይታጀብ የወገን ጦሮች የመጀመሪያውን የመከላከያ ወረዳ ለቀው ሁለተኛውን መከላከያ ወረዳ በያዙ የሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ በጅጅጋ ከተማ ሰሜን በወገን መካከለኛ

የመከላከያ አቅጣጫ ታንኮቹን በረድፍ አሰልፎ ወደወገን ሁለተኛ የመከላከያ ወረዳ በመገስገስ ላይ መሆኑን የተመለከቱት የወገን ቃኚዎች ለጅጅጋ ግምባር እዝ ያመለክታሉ።

የጅጅጋ ግምባር እዝ ለአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት እዝ ሲያመለክት እኛ በያዝነው ወታደራዊ ሬዲዮ በመስማታችን ጣልቃ ገብተን በጓድ ሻለቃ አዲስ ተድላ አማካኝነት ድሬዳዋ ያለው አየርኃይላችን በቅፅበት ተነስቶ ወደ ጅጅጋ ከተማ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉትን የጠላት ታንኮች እንዲደበድቡ ትዕዛዝ ከሰጠበት ደቂቃ ጀምሮው በዚያ ግልፅ ሜዳ ላይ ያለአንዳች ችግር እያሉ ታንኮችን ሲያጋዩ የወገን ታንከኞችም እንዲሁ ብዙዎቹን ከጥቅም ውጭ ቢያደርጉም ከታንኮቹ ብዛት የተነሳ ማቆም ስላልተቻለ የወገን ብረት ለበስ ጦር ወደ ሦስተኛውና ወደ መጨረሻው የመከላከያ ወረዳ ሲያፈገፍግ ጠላት የወገንን እንቅስቃሴ እየተቆጣጠረና እግር በእግር እየተከታተለ ወደ ጅጅጋ ከተማ ይገሰግስ ጀመር።

በዚህ ጊዜ የጠላት የመድፍ ድብደባ ጋብ ብሏል። ከታንከኞቻችን ሌላ አየርኃይሎቻችን ድሬዳዋ ለጅጅጋ በጣም ቅርብና የደቂቃዎች በረራ በመሆኑ በምብና ሮኬት እየተመላለሱ በመጫን ስለሚቀጠቅጡት የጠላት ታንከኞች የኛ አየርኃይል የሚያደርስባቸውን ጉዳት ለማቃለል ይመስላል በመጨረሻ ፍጥነታቸው እየሮጡ ሲመጡ፣ ከጅጅጋ ከተማ ሰሜን ምዕራብ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ባለ ዘብጣማ ወይንም በጣም ሰፊ ግን ጎድጓዳ ስፍራ ላይ በክረምት ውሃ እያቆረ ሀይቅ የሚሰራና መሬቱ መጠጥ ሲል ውሀው የፈጠረው ጥልቅ ደለል በሩቅ ለተመለከተው ደረቅና አቧራማ መሬት ስለሚመስል የሶማሊያ ታንኮች ከፊሉን ታንኮቻቸውን እዚያ ደለል ውስጥ እየጨመሩ መውጣት አልተቻላቸውም። አየር ኃይላችን ከታንኮቻቸው ጋር እንዳያጋዩአቸው ከታንኮቻቸው እየወጡ ወደመጡባት አቅጣጫ ተመልሰው የሚሸሹትን ታንክ አሽከርካሪዎች የተመለከተው የጠላት ታንከኛ ጦር ምን እንደ ተፈጠረ ባለማወቅ በመደናገጥ ታንኮቹን እያዞረ ሲሸሽ አየር ኃይላችን እየተከታተለ ብዙዎቹን እየጋየ አስቀረ።

በቶጎጫሌ ግምባር የተሰለፈው 6ኛው የጠላት የታንክ ብርጌድ በዚያ ሁኔታ በእግረኛ ወይንም በሜካናይዝድ እግረኛ ሳይታጀብ ብቻውን እየሮጠ ለምን እንደመጣና በኋላም ከሰላሳ የማያንሱ ታንኮች እደለል ውስጥ ቢሰምጡበትም ያንኑ ያህል ቁጥር በወገን ታንከኛና አየር ኃይል ቢወድሙበትም የተረፉ በርካታ ታንኮች እያሉት ጅጅጋ ከተማ ውስጥ ከገባ በኋላ በሚያስገርም ሽሽት ተመልሶ የወጣበት ምክንያት ለኔ እስከዛሬም ሳይገባኝ ይኖራል።

ሶማሊያ ውስጥ በአማካሪነት ሲሰሩ የነበሩት የሶቭየት ሕብረት የጦር መኮንኖች ከፊሉ ወደ አገራቸው ሳይመለሱ በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ በመሆናቸው ባቀረቡልን ወታደራዊ መረጃ ስለተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት አደረጃጀት፣ ብዛትና ዓይነት፣ ኢትዮጵያን ለመውረር ስላዘጋጁት ስልትና ስትራቴጂ በቂ እውቀት ስለነበረን በዚያን ጊዜ ከሁሉም የጦር ግምባር ይበልጥና በብርቱ ያሳሰበን የጅጅጋ ግምባር ነበር።

ስለሆነም እኔና ለሥራው አግባብና ሃላፊነት ያላቸው ጓዶች ሐምሌ 11 ቀን 1969 ዓ.ም በአየር መጓጓዣ ድሬዳዋ ከተማ አርፈን ወደ ሐረር በየብስ መጓጓዣ ስናመራ የወራሪው የሶማሊያ መንግሥት ሰርጎገብ ወታደሮችና ኢትዮጵያዊ ምንደኞቻቸው በመንገዳችን ግራና ቀኝ በሚገኙ ዛፎችና ጢሻዎች ውስጥ እድፍጠው ተኩስ በመክፈት ጉዞአችንን ለማወክ ብቻ ሳይሆን ቢቻላቸው ጉዳትም ለማድረስ የሞከሩት ከአደሌ እስከ ሐረር ከተማ ድረስ ነበር።

ወደ ጅጅጋ ለመሄድ ቸኩለን ስለነበር ጊዜ ለመቆጠብ ስንል የክፍለ ሃገሩ አስተዳዳሪና የክፍለ ሃገሩ ደህንነት ጥበቃ ሃላፊ፣ የክፍለ ሃገሩ ፖሊስ አዛዥ የአንደኛ አብዮታዊ ሠራዊት



አዛዥና እንዲሁም የዘመቻ የመረጃ መኮንኖች ስለክልሉ ወቅታዊ የፀጥታ፣ የፖለቲካ ወታደራዊ ሁኔታዎች ገለፃ እንዲያደረጉልን ያደረግነው በአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት ዘመቻ መምሪያ አዳራሽ ውስጥ ነበር።

በዚህ ጊዜ ነበር ጓድ አብዱላሂ የሐረርጌ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪ የነበረው ሶማሊኛ ቋንቋ መምህር ገለጣውን ሲያጠቃልል ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት "አሁን ካልሆነ መቼም" በማለት አለኝታዬ ነው የሚለውን አንድ አምስተኛ የኢትዮጵያን ግዛት በኃይል ለመውሰድ ጦርነት ስላወጀ ሐረር በሶማሊያ ሠራዊት ተከብባለች ብሎ የነገረን።

በብዙ ሰዎች የተደረገልን አስፈላጊ፣ ሰፊና ዝርዝር ገለፃ ከማዳመጥ ባሻገር ከቆላዎቹ በጋዴ አውራጃዎች የጦር ግምባሮች በትዕዛዝ ስልታዊ ማፈግፈግ አድርገው ወደ ሐረር የተመለሱት የጦር ክፍል አዛዦችና እንዲሁም ጦሩን ሳነጋግር በአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ ቅጥር ግቢ ውስጥ እስከ አምስት ሰዓት ድረስ ለመቆየት ተገድደን ነበር። ወደ ጅጅጋ ከማምራታችን በፊት አብረውን የነበሩትን የጦር ኃይሎቻችን ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ሜ/ጀነራል ግዛው በላይነህ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ስለሚያከናውኗቸው አንዳንድ አስቸኳይ ወታደራዊ ጉዳዮች ለመነጋገር በአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ ጽሕፈት ቤት ውስጥ ተቀምጠን ስንነጋገር ስልክ ተደወለና ጀነራል ግዛው አነሱት። የተደወለው ከጅጅጋ ከተማ ከ10ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ ጠቅላይ ሠፈር ነው።

የብርጌዱ ዘመቻ መኮንን የነበረው ሻለቃ ይልማ ግዛው የተባለ መኮንን ለጀነራል ግዛው "የሶማሊያ ታንከኛ ሠራዊት በታንክ እጥለቀለቀን ብሎ ሲነግራቸው እስቲ ቆይ በማለት የስልኩን ማዳመጫ በእጃቸው አፍነው መኮንኑ የነገራቸውን ሲነግሩኝ ስልኩን ተቀበልኳቸው።

የደወለው መኮንን መስመር ላይ እንዳለ ካረጋገጥሁ በኋላ ሻለቃ ይልማ በርጋታና ዝርዝር በጅጅጋ እየሆነ ያለውን ሁኔታ አስረዳኝ ስለው፣ በዚህ ቦታ ብዙ ለመቆየት አልችልም አንድ የሶማሊያ ታንክ እየሮጠ መጥቶ ይሔውና ሰንደቅ ዓላማችንን ጨፍልቆ ጥሎው እየተመለከትኩ ነው። ከኔ የሚርቀው አምስት ሜትር ያህል ብቻ ነው። ደሕና ሁኑ ለአገሬ ለኢትዮጵያ መልካሙን ሁሉ እመኛለሁ ብሎኝ ስልኩን ዘጋው።

ይህ መኮንን በወታደራዊ ችሎታውና በመኮንንነት ምግባሩ የተመሰገነ እውቅ መኮንን ከመሆኑ ሌላ የሕግ ባለሞያም ነው። በሕይወት መቆየቱን በመጠራጠር ለአገሩ ያለውን ፍቅርና መልካም ምኞት ገልጾ ቢሰናበተኝም አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት በምሥራቅ ግምባር አኩሪ ድል ከተቀዳጀ በኋላ ፊቱን ወደ ሰሜን ባዞረበት ጊዜ በመጀመሪያው አፍላ ወረራ በጎንደር በኩል በኮሎኔል ረጋሳ ጂማ እየታዘዘ ወደ ኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ የዘመተው ሠራዊት አንድ ንዑስ ግብረኃይል አዛዥ ሆኖ በሌ/ኮሎኔልነት ማዕረግ በከረን ግምባር ሲዋጋ ነው የተሰዋው።

ሻለቃ ይልማ ደህና ሁን ብሎ ከተሰናበተኝ በኋላ ከጅጅጋ ግምባር ዕዝ ጋር የነበረን ስልክ ብቻ ሳይሆን የወታደራዊ ራዲዮ ግንኙነትም ስለተቋረጠ ከዚያ በኋላ ከጅጅጋ ጋር ያገናኘን የነበረው በልዩ ራዲዮ በጅጅጋ ሰማይ ላይ ያለማቋረጥ ከሚዋጉት አየርኃይሎቻችን ጋር ነበር።

ከዚህ በኋላ ከቀኑ ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ አንደኛ እኔ፣ ሁለተኛ የደርግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የመከላከያ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ገብረኪዳንና ሦስተኛ የደርግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የመከላከያ ኮሚቴ አባል ሻለቃ አዲስ ተድላ፣ አራተኛ የደርግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የጦር ኃይሎች የፖለቲካ ኮሚሳር የመቶ

አለቃ ለገሰ አስፋውና አምስተኛ የጦር ኃይሎች የዘመቻ መኮንን ኮሎኔል ኃይለጊዮርጊስ ኃብተማርያም፣ ስድስተኛ የደገሐቡር ከተማን ከጠላት ሲከላከል የነበረው ግብረ ኃይል አዛዥ ኮሎኔል እሸቱ መኮንን፣ ሰባተኛ የአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት የዘመቻ መኮንን ሌ/ኮሎኔል መሥፍን ገብረቃል ሆነን ከአጋዴን ከተመለሱት የጦር ክፍሎች ከፊሉን ጅጅጋ ለሚዋጋው ሠራዊት ስንቅ፣ ጥይትና ነዳጅ ቅባትና እንዲሁም ሠራዊት የሚኑ ቁጥራቸው ወደ ዘጠና የሚደርስ የየብስ ተሽከርካሪዎችን ይዘን ወደ ጅጅጋ አመራን።

ከሐረር ከተማ የጅጅጋ ከተማ ርቀት 105 ኪ/ሜትር ብቻ ስለሆነ ከባድ የየብስ ተሽከርካሪዎች በአዝጋሚ ጉዞ ከሦስት እስከ አራት ሰዓት ስለሚወስድባቸው እነሳለን ከቀትር በኋላ ከአስር እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ጅጅጋ እንደርሳለን በሚል ግምት ነበር። ሆኖም ከድሬዳዋ ወደ ሐረር ስንጓዝ ከገጠሙን አድፋጭ የጠላት ወታደሮችና ምንደኛ ከሐዲዎች በዓይነትም በመጠንም የላቀ ዳግም ስለገጠሙንና መዋጋት ስለነበረብን ፋፊም ለማደር ተገደድን።

ጠላት በልዩ ልዩ ጠማርና ፈሳሽ ጭንቶች ሌላ ጥይትና ነዳጅም የሚኑ እና ተሽከርካሪዎች መያዛችንን በመመልከቱ ለማጋየት ከያለበት እየተጠራራ መሰባሰብ ስለአሳሰበን ንብረቱን ለማዳን በግድ ለማደር ተገደድን እንጂ የያዝነው ደረቅ ጭነት ብቻ ቢሆን ኖሮ እንደገመትነው በጊዜ ጅጅጋ መግባት በቻልን ነበር።

ቀን እስኪመሽ በአደረግነው ጉዞ ቅልፈቱን የሚመራ አንድ መሣሪያ የጠመደ የወታደር ፖሊስ ጂፕ ተሽከርካሪ ጠላት በቀበረው ፈንጂ ላይ ወጥቶ በመጓዝ በተሽከርካሪው ላይ የነበሩት አሽከርካሪውና መትረየስ ተኳሹ ሲጎዱብን ሌሊት ጨለማውን ሽፋን አድርጎ ጠላት እየተጠጋ በሞከረው ማጥቃት ጥቂት ወታደሮችና ሲቪል አሽከርካሪዎች ተገደሉብን።

ጎህ ሲቀድ በመነሳት ጉዞአችንን በወታደራዊ ሥልት ቀጥለን ያለብዙ ችግር በመጓዝ ከካራመራ ሰንሠለታማ ተራራ በስተጀርባ ወይንም ማርዳፓስ ከሚባለው ከተራራው ጀርባ ወደ ኋላ በአለው ሸለቆ ከመንገዱ ግራና ቀኝ ባሉት ቁጥቋጦዎች ውስጥ መድፋቸውን ከደገኑት ሁለት የመድፍ ሻለቆች በስተጀርባ ቤት ንብረቱን እየጣለ የሸሸው የጅጅጋ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ ሲርመሰመስና ሕጻናት ሲያለቅሱ በማየታችን ታላቅ ሃዘን ስለተሰማን ከተሽከርካሪ ወርደን አይዟችሁ ደርሰንላችኋል በማለት ማፅናናት ነበረብን። ሕዝቡ ያን ያህል ቅልፈትና እንዲሁም በርካታ ሠራዊት ከማስተዋሉም እኛን ሲመለከት የተሰማውን ደስታ ለማግለፅ ያስቸግራል። በሸለቆው እልልታ፣ ፉከራና መፈክር አስተጋባ።

እንባቢ እንደሚያስታውሰው የሶማሊያ 6ኛው የታንክ ብርጌድ በጅጅጋ ከተማ ላይ ሐምሌ 12 ቀን ከቀትር በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ማጥቃት ሠንዝሮ በርካታ ታንኮች ደለል ውስጥ በመግባት ስለሰመጡበት፣ እንዲሁ ሌሎች በርካታ ታንኮች በወገን ታንኮችና በተለይም በጀግናው አየርኃይላችን ስለጋዩበት በሽሽት ወደመጣበት ተመልሷል።

ሐምሌ 13 ቀን ከጧቱ አራት ሰዓት ገደማ ጅጅጋ ከተማ ስንገባ የሚታየውና የሚሰማው የጠላት መድፎች ተኩስ ብቻ ነበር፡ ጠላት ሦስተኛውን አማራጭ የወገን መከላከያና በፈረንሳይ መሐንዲሶች የተሠራውን ከከተማው ሰሜን ወጣ ብሎ የሚገኘውን የሜካናይዝዱን ብርጌድ ዘመናዊ የጦር ሠፈር ሲደበድብ የተወሰኑ ጥይቶች አልፎ አልፎ ከተማው ላይ ይወድቁ ነበር።

ወደ ከተማው ስንቀርብ ከከተማው ወጣ ብሎ ለከተማው ደቡብ በሚገኘው የአጋዴን እንበሳ በመባል በሚታወቀው ዘመናዊ ሆቴል በራፍ ላይ በወገን አየርኃይል ተመትቶ የቆመ ቲ-55 የተባለውን የሶቭየት ሕብረት ሥሪት ታንክ ተመለከትን። አስረኛው ሜካናይዝድ



ብርጌድ መምሪያ ጽሕፈት ቤት ስንደርስ ሻለቃ ይልማ የነገረን የጠላት ቲ-55 ታንክ ቢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ረግጦ በመጣል ላዩ ላይ እንደቆመ ከጽሕፈት ቤት በራፍ ላይ አየነው።

እነዚህ ያየናቸው ሁለት የጠላት ታንኮች ሁኔታ ያስገነዘበን፣ ተዋጊ ፓይለቶቻችን ምን ያህል እንደተራቀቁና ምን ያህል ብቃት ያላቸው ተዋጊዎች መሆናቸውን ነበር። ምክንያቱም፡ የታንኮቹን ከባድ መትረየስና መድፍ ተሸክሞ ወደተፈላጊው አቅጣጫ የመተኮስ የሚያሽከረክረውን ለአሽከርካሪው፣ ለተኳሹና ለታንኩ አዛዥ፣ መግቢያና መውጫ የሆነውን ወይንም በጠቅላላ እንጋገር ታንኩን ታንክ የሚያሰኘው ቱሬት በሮኬት በመምታት ታንኮቹን ጃርት የበላው ዱባ አስመስለዋቸዋል።

በአስረኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ መምሪያ ጽሕፈት ቤት በዘመቻ እዳራሽ ውስጥ ተቀምጠን ሐምሌ 12 ቀን ስለተካሄደው ውጊያ በተለይና ስለወገንና ስለጠላት ሁኔታ በጠቃላይ የተደረገልንን ገለፃ አዳመጥን። ከተደረገልን ገለፃ ይዘት ለመረዳት የቻልነው አብዛኛው የጦር አዛዦችና ለብዙ ጊዜ በታላቅ ስጋት ሲጠበቅ የነበረውን የሶማሊያ ወረራ መክተው በመመለስ የተሟላ ድል እንደተቀዳጁ የሚሰማቸው መሆኑን ነበር። እኔ ቀደም ብዬ ሳውቅ የዘጠነኛው ሜካናይዝድ እግረኛ ሻለቃ ጥብቅ የመረጃ መኮንን የነበረ አሥራት የሚባል ወጣት የመቶ አለቃ በነበረብን የመኮንኖች እጥረት ምክንያት ይመስላል የጅጅጋ ግንባር የመረጃ መኮንን ሆኖ ነው ስለጠላት ገለፃ ያደረገልን።

ትናትና ሶማሊያዎች በአንድ የታንክ ብርጌድ የሰነዘሩት ጥቃት ዋና ዋና የመጨረሻው ጥቃት ነው ብለህ ታምናለህ? ብዬ ስጠይቀው "በሚገባና በትክክል ነው የማምነው። የትናንቱ የጠላት ጥቃት የመጨረሻው ጥቃት ነው" የሚል መልስ ሰጠኝ። ጥቂት መኮንኖች በሹክታ አጉረመረሙ። በትጥቁ ጥራትና ብዛት በጥቁር አፍሪካ ወደር የሌለውን ወራሪ ሠራዊት ለ15 ዓመታት አደራጅቶና አዘጋጅቶ ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ከእኛ ጋር የሚያደርገው ውጊያ በትናንቱ በአንድ የታንክ ብርጌድ ጥቃት ብቻ አብቅቷል ለማለት ያስቻለህ ምክንያት ምንድነው ብዬ ስጠይቀው፣ "የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ባለፈው አንድ ወር በዚህ በሐረርጌ፣ በባሌና በሲዳሞ ክፍለአገሮች ቆላማ አውራጃዎች ባደረገው ወረራ የኢትዮጵያ አየርኃይል ሰማንያ በመቶ የሚሆኑትን ብረት ለበሶችና ታንኮች፣ መድፎችና እግረኛ ሠራዊቱን ያወደመበት ስለሆነ ነው" የሚል ነበር የመጨረሻ መልሱ።

አዛዦችንና የተቀሩትንም መኮንኖች "በመቶ አለቃ አሥራት የመረጃ ግምት ትስማማላችሁ" ብዬ ስጠይቃቸው ሁሉም የመረጃ መኮንኑን ግምት ሙሉ በሙሉ ለመቀበል እንደሚሳናቸው አልሸሸጉም ነበር። የወጣት መኮንኑን ስሜት ላለመጉዳት አየር ኃይላችን በጠላት ላይ ያደረሰው ጉዳት የሚያኮራ ስለመሆኑ ከመቶ አለቃ አሥራት ጋር እስማማለሁ። ነገር ግን ትናንት ያደረጋችሁት ውጊያ የተሟላ ድል ያቀዳጀንና የመጨረሻ ነው ብላችሁ እንዳትሳሳቱ ከተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ጋር የምናደርገው ውጊያ ገና አልተጀመረም። ከባዱንና ዋናውን የጠላት ወረራ ነቅተን መጠበቅ አለብን በሚለው አስተያየቱ ተግባብተን ከአዳራሹ በመውጣት ውጊያው የተካሄደባቸውን መስኮች ወደ መጎብኘቱ አመራን።

በመጀመሪያ ከጅጅጋ ከተማ በስተምዕራብ ያለውን የመከላከያ ወረዳ ነበር የጎበኘነው። ከዚህ ቀጠና ነበር የጠላት ታንኮች በደለል ተውጠው በብዛት የሚታዩት። ከጅጅጋ ከተማ ሰሜን በመካከላዊው የመከላከያ ወረዳና ለጅጅጋ ከተማ ምሥራቅ የመከላከያ ወረዳ ውስጥ



በጦር ሜዳ ጀብዱ ለፈጸሙ የጦር አባሎች የማዕረግ ዕድገት ሲንሰጥ

ከጥቅም ውጭ ሆነው የቆሙ የጠላት ታንኮች ተመልክተናል። አብዛኛዎቹ በወገን አየርኃይል የተመቱ ሲሆን ቀደም ብለን በኦጋዴን አንበሳ ሆቴል በራፍና በአስረኛው ሜካናይዝድ ብርጌድ ግቢ ውስጥ እንደተመለከትናቸው የጠላት ታንኮች በማያዳግም ሁኔታ ተመትተው የጋዩ ናቸው።

ግምባር ቀደም የመከላከያ ወረዳዎችን ከተመለከትን በኋላ ያመራነው ከጅጅጋ ከተማ በስተደቡብ ከካራማራ ተራራ ግርጌ በኋላ ደጀንነት የመከላከያ ስፍራ የያዘውን መደበኛና ሕዝባዊ ሠርዊት ለመጎብኘት ነበር።

ወደዚህ ተጠባባቂ ሠራዊትና ወደ የመከላከያ ቀጣና ስናመራ መንገዳችን ላይ ርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽንን ሲያገለግል ተበላሽቶ ከጅጅጋ አየር ሜዳ ጠርዝ ላይ የቆመ አንድ አሮጌ ዳኮታ የጭነት አይሮፕላን በጠላት አየር ኃይል ተመትቶ አየነው።

እኔ እስከማውቀው ወይም እስከማስታውሰው የሶማሊያ አየር ኃይል መምታት የቻለው ይህንን ተበላሽቶ የቆመ ዳኮታ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ አልፎ አልፎ በአየር ክልላችን ላይ ለመብረር ቢሞክሩም አየር ኃይላችንን ሲመለከቱ ወዲያው እየሸሹ ከመመለስ በስተቀር ያደረሱብን አንዳችም ጉዳት አልነበረም።

በተቃራኒው ከሐምሌ 12 ቀን ጀምሮና ከዚያም በፊት የኢትዮጵያ አየርኃይል የሶማሊያን የአየር ክልል በመድፈር በአጠቃላይና በሰሜን ሶማሊያ ርዕሰ ከተማ በሃርጌሳ በተለይ የሲቪልና ወታደራዊ ዒላማዎችን በመደብደብ የጠላትን የመከላከያ ኃይል ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚውንም ያዳክም ነበር። የጠላት የመከላከያ ሠራዊት ባልጠበቀው ጊዜና ቦታ በድንገት እየደረሰ እንደመብረቅ የሚመታውን የኢትዮጵያን አየር ኃይል ሰይጣን በማለት ነበር የሚጠራው።



ወደ ተንሳሁበት ርዕሰ ልመለስና የጅጅጋን ከተማ ከጠላት ወረራ በመከላከል ላይ ያለውን የጅጅጋን ግምባር ሠራዊት በማጠናከር በደጀንነት የተሰለፈው አብዛኛው መደበኛ ሠራዊት ከጎዴና ከቀብሪደሐር፣ ከዋርዴርና ከደገሐቡር ወዘተ በትዕዛዝ አፈግፍጎ የተመለሰው ሲሆን ከዚያ ከፊት ቀደም ብሎ ለ10ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ የተደረበው አንድ ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦር ጥሩ ስልጠና አግኝተዋል ከሚባሉት ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለጦሮች አንዱ ሲሆን በትቅጥም ረገድ ከነፍስ ወከፍና ከቡድን መሣሪያዎች በተጨማሪ ዘመናት ፀረ-ታንክ መሣሪያዎች የታጠቀና በአመራርም ረገድ የተሻለ የመኮንን ቁጥር ያለው በሌ/ኮሎኔል ደሳለኝ አበበ የሚታዘዝ ነበር።

በብርጌዱ የዘመቻ መምሪያ አዳራሽ ውስጥ በተደረገልን ገለፃ እንደተረዳነው ሰፊው ሠራዊትም እንደመሪዎቹ የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጥቃት ለአንዴና ለመጨረሻ መልሰናል ብሎ በማመን ራሱን እንዳያታልልና እንዳይዝናና በማስጠንቀቅ የጅጅጋን ግምባር መከላከል በእኛ መልሶ ማጥቃትና ብሎም በጠላታችን ላይ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ለምንቀዳጀው የተሟላ ድል የሚኖረውን አስተዋፆና ታሪካዊነት አስረድተን ስናበቃ ጊዜው መሽቶ ስለነበር እዚያው አደርን።

ጠላት በማናቸውም ሰዓት ምንም ዓይነት የተፈጥሮ እንቅፋት በሌለበት የጅጅጋ ሜዳ ላይ በታንክ ባውዛዎች ብርሃን እየተረዳ የሌሊት ማጥቃት ሊሰነዝር ስለሚችልና የዚህ ዓይነት የሶቭየት ሕብረት ሠራዊት ግርፍም ስለሆነ የግንባሩ የወገን ሠራዊት በጠቅላላ መሣሪያውን ደግኖ በንቃት በመጠባበቅ ላይ ስለነበር በማንም ዘንድ እንቅልፍ ብሎ ነገር የሚታሰብ አልነበረም።

በቀን ውሏችንና በሌሊቱ አዳራችን ባየነውና በሰማነው ሁሉ የሜካናይዝድ ብርጌዱ ምክትል አዛዥ የነበረው ሌ/ኮሎኔል ኃይሌ ተስፋሚካኤል በሚያዘው ሠራዊት ዘንድ ተቀባይነት ስላልነበረው ለብርጌዱ የአዛዥ ለውጥ አደርገንና ለግንባሩም እንደዚሁ ብቃት ያለው ሁነኛ አዛዥ በመሾም የእዙን አካል አጠናክረን ለተሰጣቸው ጅጅጋን የመከላከል ተግባር አስፈላጊውን መመሪያ ሰጥተን ከጠዋቱ ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ በሄሊኮፕተር ወደ ሐረር ተመለስን።

ሐረር ያለውን የአንደኛ አብዮታዊ ሠራዊት እዝንም እንደተመለከትነው የመኮንኖች እጥረት እንዳለበት ስለተገነዘብን በወረራው ምክንያት ለጊዜው ሥራውን አቁሞ ከነበረው የሐረር ጦር አካዳሚ መኮንኖች በከፊል ደርበን እዙን ከማጠናከር ባሻገር በዚህ ግምባር ሀገርንና አብዮትን ለማዳን በሚደረገው ትግል ሕዝቡንና ሠራዊቱን ለማስተባበር እንዲቻል የደርጉ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና የመከላከያ ኮሚቴ ሊቀመንበር ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ገብረኪዳን የአንደኛ አብዮታዊ ሠራዊት፣ የክልሉ የፖሊስ ሠራዊት፣ የክልሉ አባት ጦርና የክልሉ ሚሊሽያ የበላይ አዛዥ፣ የደርግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ጓድ ሌ/ኮሎኔል ዘለቀ በየነን ለሠራዊቱና ለክልሉ የበላይ የፖለቲካ ኮሚሳር አድርገን ሐምሌ 14 ቀን ወደ አዲስ አበባ ተመለስን።

ሐምሌ 15 ቀን ጎህ ሲቀድ የጠላት የመድፍ ብርጌዶችና ቢኤም 23 ሮኬት ሻለቆች ከተሟሉ ግምባር ወደ ጅጅጋ ከተማ ተጠግተው በወገን ሠራዊት የመከላከያ ይዞታ ላይ ብቻ ሳይሆን በጅጅጋ ከተማና በአካባቢው ላይ እንደተጠበቀው ጠቅላላ ጥቃት ለመሰንዘር በባድ መሣሪያ ጥይት ዝናባቸውን ማዝነብ ጀመሩ።

የጠላት አቀራረብ እጅግ ከባድና አሳሳቢ ስለነበረ የግምባሩን እዝ ዳግም በማጠናከርና ሠራዊቱን በማትጋት የተቻላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ የሠራዊቱን የበላይ ጠቅላይ አዛዥ

ያደረግነውን ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ገብረኪዳንና የሠራዊቱን የዘመቻ መኮንን ጓድ ሌ/ ኮሎኔል መሥፍን ገብረቃልን ወደ ጅጅጋ እንዲሄዱ አደረግን። ሐምሌ 15 ቀን ጠዋት ነጋ ሲቀድ ጠላት የጀመረውን የመድፍ ድብደባ ያለተቃውሞ ማለትም፣ የወገን አፀፋ የመድፍ ተኩስ መልስ የወገን ጦር ከመቀበሉ ሌላ የጠላትን እግረኛና ብረት ለበስ ጦር ጥቃት ከአየር ኃይላችን ጋር በሕብረት መክቶ ዋለ።

የጠላት 122 ሚ/ሜትር፣ 130 ሚ/ሜትር መድፎችና 122 ሚ/ሜትር ሮኬት ወንጫፊዎች በ30 ኪ/ሜትር እርቀት የወገንን ጦር መደብደብ ሲችሉና የእኛ የአሜሪካን ስሪት 105 ሚ/ሜትር ሐዊትዘር መድፎች የውጤት እርቀት 12 ኪ/ሜትር ብቻ በመሆኑ መድፎቻችንን ፍፁም አልተጠቀምንባቸውም ማለት ይቻላል።

የጠላት እግረኛ፣ ሜካናይዝድ እግረኛና ታንከኛ ጦሮች በሕብረት የወገንን የመከላከያ ይዞታ የሚያጠቁት በቮልጋና በስትሬላ የአየር መቃዎሚያ ሚሳኤሎች እየተረዱ ስለነበረ በሁለተኛውና በጠቅላላው የጠላት ጥቃት ክፉኛ የተቸገረው እግረኛ ሠራዊታችን ብቻ ሳይሆን አየር ኃይላችንም ነበር።

የኢትዮጵያን የመከላከያ ኃይል ለመበታተን ብቻ ሳይሆን የአመራሩንም ትኩረት ለማዛባት ጠላት ጅጅጋን በመጠን ሰፊ ከባድ መሣሪያና ብረት ለበስ ጦር ሲያጠቃ በዚያው ጊዜ ውስጥ የተቀረው የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት በባሌና በሲዳሞ ግምባርም እንዲሁ ከባድ የማጥቃት ውጊያ በማካሄድ ላይ ነበር።

በዚህ ጊዜ ውስጥ ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ፍላጎት እንዲሟላና በሚፈጠረውም አጋጣሚ የእነሱም ኢትዮጵያን የመገንጣጠል ዓላማ ይሳካ ዘንድ የሰሜኖቹ ገንጣዮች ማለትም፣ ጀብሃና ሻዕቢያ በየበኩላቸውና በየክልላቸው በሰሜኑ ሠራዊታችን ላይ እንዲሁ ከባድ ጥቃት ሰንዝረው ስለነበረ የጦር ግንባሮቹ ሁሉ በአንዴ ወይም በተመሳሳይ ጊዜ የአየር ኃይልን እርዳታ ስለሚጠይቁ ድጋፍ ለመስጠት በራሪ ተዋጊዎቻችን ያለ እረፍት የፀሐይ ብርሃን በጨለማ እስኪጋረድ ድረስ ከደቡብ ወደ ምሥራቅ፣ ከምሥራቅ ወደ ሰሜን ወዘተ ቀኑን በሙሉ ሲከንፉ ከመዋላቸው በላይ በዚሁ ቀን አንዱ በደቡብ ግምባር በነገሌ፣ ሌላው በምሥራቅ ግምባር ጭናክሰል ላይ በጠላት የአየር መቃወሚያ ሚሳኤል ተመትተው በቀላሉ የማይተኩ ሁለት ጀግና በራሪዎች ወደቁብን።

ከጅጅጋ መልካምድራዊ ገፅታና ከከተማው አቀማመጥ፣ የጠላት ሠራዊት ሜካናይዝድ ወይም ተንቃናቂ በመሆኑ ጅጅጋን የሚከላከለው የወገን ጦር በአጠቃላይ ቋሚና ጠንካራ መከላከያ ምሽግ ያልነበረው ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን የመሰለ የውጊያ ልምድ የሌለው ሕዝባዊ ሠራዊታችን የሚዘንብበት የመድፍና የሮኬት ጥይት ዝናብ የሰው ኃይሉን ክፉኛ ያመነመነው ከመሆኑም ሌላ ጀግና መሪዎች በዚያ ሜዳ ላይ ያለመከታና ከለላ እየተንቀሳቀሱ ጦራቸውን ለውጊያ ሲያጋፉ ብዙዎች በመሰዋታቸው ከሠራዊቱ አቅምና ቁጥጥር በላይ እየሆነ መሄድ ጀመረ።

የወገን ጦር ሐምሌ 12 ቀን የያዘውን የመጨረሻውን ሦስተኛ የመከላከያ ስፍራ እንዲለቅ በመገደዱ የጅጅጋን ከተማ ወደኋላ ትቶ በካራማራ ሰንሠለታማ ተራራ ግርጌ ያለውን ወታደራው መሬት ለመያዝ ማፈግፈግ መጀመሩን ያስተዋለው ጠላትም በወገን ብርቱ መከላከልና በአየር ኃይላችን ተፅዕኖ ከተገታበት ስፍራ ወደፊት ለመንቀሳቀስ ቻለ። የጠላት የፊት ተመልካቾች ወይም መድፍ አስተኳሾችም ወደ ዒላማቸው ስለቀረቡ በተሻለ ሁኔታ ዒላማቸውን እየተመለከቱና እየመረጡ በማስደብደብ የተኩስ ኃይላቸውን ከጨመሩት ሌላ የጠላት ታንኮች በገፍና በፍጥነት እየተንቀሳቀሱ የ10ኛውን የወገን ሜካናይዝድ ብርጌድ የጥገና አገልግሎት መስጫ ተቋም ወይንም ጋራዥና በተለያዩ ምክንያቶች ተበላሽተው የቆሙ



የተለያዩ ተሽከርካሪዎችንና አርጅተው ከጥቅም ውጭ በመሆናቸው ወደ ማደሻ ኢንዱስትሪ ለመላክ በብዛት የተካበቱ የተሽከርካሪ ጎማዎችን የጥይት፣ የፈንጂ፣ የነዳጅ፣ የቅባት፣ የዘንቅና የትጥቅ ማከማቻ ዴፖዎችን በቅርበትና በቀጥታ ተኩስ መምታት ሲያጋዩአቸው የተነሳው ቃጠሎ የፈጠረው ከፍተኛ ጭስ የጅጅጋን ከተማና የአካባቢውን ብርሃን ጋረደው።

በወገን የእዝ አካሎችና በሠራዊቱ መካከል ያለው ግንኙነትና በአጠቃላይ ዕዝና ቁጥጥር ተቃውሶ መሪና ምንዝሩ ስለተለያዩ በመጨረሻውም ወደማታ ጀንበር ስትጠልቅ ሠራዊቱ ስልትና ሥርዓት በጎደለው ሁኔታ በማርዳፖስ በር እየተጋፋ በማፈግፈግ ከካራማራ ተራራ ጀርባ በመዞሩ የጅጅጋ ከተማና አካባቢው በጠላት እጅ ወደቁ።

እስከዚህ ጊዜ ድረስ ማርዳፖስ በሚባለው የካራማራ ተራራ በር በስተቀኝ ባለው ጋር ኮረብታ ላይ ሆነው የጠላትን ተዋጊ አይሮፕላኖች እንቅስቃሴ በራዳር ሲቆጣጠሩ የነበሩ የአየርኃይል የቴክኒክ ባለሙያዎችና ከእነሱ ጎን ማዘዣቸውን አቋቁመው ውጊያውን ሲመሩ የነበሩት ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ገብረኪዳንና ጓድ ሌ/ኮሎኔል መሥፍን ገብረቃል ከሠራዊቱ ተቆርጠው በተራራው ላይ ስለቀሩ ለጠላት ሰለባ ከመሆናቸው በፊት በአስቸኳይ በሄሊኮፕተር ማንሳት ነበረብን።

ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬና መሥፍን ከተራራው በሄሊኮፕተር ከመነሳታቸው በፊት የሠራዊቱ አዛዦች የሚያፈገፍገውን ጦር አቁመው ሌላ የመከላከያ ስፍራ ለማስያዝ ቢሞክሩ ሰዓቱ ጨለማ በመሆኑ ሰው ከሰው ለመተያየት አስቸጋሪ በመሆኑና መደጋመጥም ያልነበር በመሆኑም ባሻገር መኮንኖች ስለተጓደሉ ሠራዊቱን ያቆም ዘንድ ሐረር የነበረው ጓድ ሌ/ ኮሎኔል ዘለቀ በየነን ከብዙ ወታደራዊ ካድሬዎች ጋር ወደ ጦሩ መላክ ነበረብን።

የጠላት እግረኛና ብረት ለበስ ጦሮች ብቻ ሳይሆን መድፈኛው ጭምር የወገንን ጦር እግር በእግር እየተከተሉ ማርዳፖስን በማለፍ የመድፍ ድብደባቸውን ስለቀጠሉና ከዚህ በኋላ የወገንን ሠራዊት የሚመሩት አዛዦች ሳይሆን የሶማሊያ መድፍ ነበር ለማለት ይቻላል። ጓድ ዘለቀ በወታደራዊ ራድዮ ከኔ ጋር ተገናኝቶ "ሠራዊት ጎርፍ ነው፣ ማቆም አልተቻለም። የጠላት የመድፍ ጥይት በወደቀ ቁጥር በኃይል ጥሶን ስለሚሄድ የሚገታ ሌላ ኃይል አስፈልጎናል" ስለአለኝ ከድሬዳዋ ግምባር ከየመን የመጣልን አንድ የቲ55 ታንክ ሻለቃ በአጣዳፊ ልከን ጦሩን ቆሬ በሚባል ከጅጅጋ በግምት 40 ኪ/ሜትር ያህል በሚርቅና ፋፋም በሚባል ወንዝ ዳርቻ ባለና ለአካባቢው ገዥ በሆነ ወታደራዊ መሬት ላይ ለማቆም ተቻለ። ቆሬ የኢትዮጵያ አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት መልሶ ጠላትን እስካጠቃበት ጊዜ ድረስ ዋናና ትልቁ የመከላከያ ግምባር ሆኖ አገልግሏል።

በብዙ ጥረትና ትግል ሠራዊቱን ቆሬ ላይ አቁመን ቋሚና ጠንካራ የመከላከያ ምሽግ ከማስያዛችን በፊት በነበረው ውጊያና እንዲሁም ጉዞ የገጠመን የሥነ-ሥርዓት ችግር የመጣው ከሶማሊያ መድፍ ተፅዕኖ ብቻ ሳይሆን ራሱን ኢሕአፓ ብሎ የሚጠራው የመጀመሪያ ሥርዓተ አልበኛ ቀጥሎ ፀረ-አብዮተኛ ብሎም አምስተኛ ረድፍ የሆነው ድርጅት ወኪሎች ለጊዜው ለኛ ባልተከሰተልን ሁኔታ በሠራዊታችን ውስጥ ሰርገው በመግባት የአገራቸው በሶማሊያ ሠራዊት መወረር ለእነሱ በጎ ነገርና የእነሱ ጥቅም አድርገው በመመልከት ባደረጉት ቅስቀሳ ነበር።

ኢሕአፓ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ሠራዊቱ ተረጋግቶ በቆሬ ሰፊና ጠንካራ መከላከያ ምሽጉን ገንብቶ የጠላቱን ጥቃት በሚከላከልበት ጊዜም ሥርዓተ አልበኝነት እንዲሰፍንና ጠንካራ የመከላከያ ምሽጉን ጥሎ እንዲሸሽ ወይም ሠራዊቱ እንዲፈርስ ስላደረገው ያልተሳካ

ጥረት ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የመጽሐፍ ክፍል አብራርቼ ለማቅረብ ለአንባቢ ቃል በመግባት ወደ ርዕሴ እመራለሁ።

እጋዴን የምንለውን የሐረርጌ ቆላማ ክልል አውራጃዎች አንዱና የመጨረሻው አውራጃ በጠላት እጅ ወድቆ በደጋው በሐረር አውራጃ በባቢሌ ወረዳ ውስጥና በፋፌም ወንዝ ዳርቻ የሚገኘውን የቆሬን መከላከያ እስከንይዝ ድረስ ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት የጠየቅናቸው የጦር መሣሪያዎች አልተላኩልንም።

የኢትዮጵያን መሬት የረገጠው የሶማሊያ መንግሥት ወታደር ድንኳን ሳይተክል ረግጠን እንደምናስወጣው ፍፁም እምነት የነበረን ቢሆንም በጅጅጋ መያዝ የተሰማንን ስሜት የተረዳ ዛሬ ስሙን የዘነጋሁት ከሶማሊያ በቀጥታ ወደኛ በመምጣት ጠቃሚ ወታደራዊ መረጃ ያቀረበልን ሩሲያዊ ጄነራል መኮንን በተገናኘን ጊዜ በመጠኑ ከሶማሊያ ሠራዊት በጣም የላቀ ጦር እያላችሁ የእጋዴን ክልል እንዴት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለቀቃችሁ? ብሎ ላቀረበልኝ ጥያቄ ከሠራዊታችን ሦስት አራተኛው የሦስት ወር ሥልጠና ያገኘ ገበሬ ከመሆኑም ባሻገር የተዋጋው ያላጋዥ መሣሪያዎች ድጋፍ በነፍስ ወከፍ መሣሪያው ብቻ ስለሆነ፣ እጋዴን የሚያመቸው ለእግረኛ ሠራዊት ሳይሆን ለብረት ለበስ ሠራዊት በመሆኑና በጠላት የመሣሪያ የበላይነት ነው ጦራችን አፈግፍጎ ለእግረኛ ውጊያ የሚያመቸውን የአገራችንን ደጋማ ክልል እንዲከላከል ያደረግነው ስለአልኩት የነገሩኝን ለበላዮቼ እመለከታለሁ ብሎኝ አሰናበተኝ።

በበነጋታው የመከላከያ ሚኒስትራችንን ለመገናኘት ጠይቆ ከተገናኘ በኋላ መሣሪያ የጫኑ የሶቭየት ሕብረት መንግሥት መርከቦች ኢትዮጵያ እስከሚደርሱ ድረስ የቆሬን መከላከያ ምሽግ የሚያጠናክሩ አንድ የ122 ሚ/ሜትር የመድፍ ሻለቃና አንድ 122 ሚ/ሜትር የቢኤም 23 ሮኬት ሻለቆች ከየመን በዛሬው ቀን አሰብ ስለሚገቡ በአስቸኳይ ተረከባችሁ ወደቆሬ እንድትወስዷቸው አሳስባለሁ በማለቱ እንዳለው የተላኩልን ሁለት ሻለቆች የቆሬን መከላከያ ስለአጠናከሩልን የቆሬ ግምባር ሠራዊት ከመረጋጋቱ ባሻገር የቢኤም 23 ሮኬትን የተኩስ ኃይል በመመልከት ተደስቶ ሮኬቱን "በቀለ ገላገሌ" የሚል ስም ስለሰጠው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይህ መሣሪያ በመላው አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊታችን "በቀለ ገላገሌ" በመባል ነበር የሚጠራው።

## ምዕራፍ ሠላሳ አራት

# በሐረርጌ፣ በባሌና በሲዳሞ ክፍላተሃገር ደጋማ አውራጃዎች ለሰባት ወራት የተደረገ የመከላከል ትግል

ጠላት ሐምሌ 15 ቀን 1969 ዓ.ም የጅጅጋን ከተማና አካባቢውን አስለቅቆ ከተቆጣጠረ በኋላ ሳይቆም የሚያፈገፍገውን የወገን ጦር እግር በእግር እየተከታተለ በማሳደድ ቢቻለው ...ሐረር ከተማ ለመዝለቅ ያደረገው ሙከራ በአብዮታዊ ሠራዊታችን ከፍተኛ ተጋድሎ ...ፋ ላይ ቢገታም ሐርጌሳ ከሚገኘው ሦስተኛው እዝ ተጨማሪ የሰውና የመሣሪያ ኃይል ...ስለት የቆሬን የመከላከያ ግምባር ለመስበር ሐምሌ 16 እና 17 ቀኖች በተከታታይ ...ቀ ማጥቃት ሰንዝሮ ባይሳካለትም ተስፋ አልቆረጠም ነበር። ከማጥቃት የተገታውና ...ደ ዝናብ የሚያዘንበው የመድፍ ድብደባ ረገብ ያደረገው ከየመን የተላኩልን የመድፍና ...ሮኬት ሻለቆች ቆሬ ደርሰው ለመጀመሪያ ጊዜ አፀፋውን የመድፍና የሮኬት የተኩስ መልስ ...ሰጡ በኋላ ነው።

ሁለት ጊዜ በመደጋገም ባደረገው ማጥቃት በወገን ፀጥ መከላከል ከፍተኛ ጉዳት ...ርሶበት ሬሳውን ብቻ ሳይሆን ቁስለኞቹንም እየጣለ እንዲመለስ በመገደዱ የቆሬን ...ላከያ ደምስሶ ወደ ሐረር ለመሄድ የማይቻል መሆኑን ስለተረዳ አንደኛውን ወይም ...ምሥራቁን የወገን ሠራዊት በጠቅላላ ከመሃል ሃገር ድሬዳዋ ላይ በመቁረጥ በተፈጥሮ ...ት ለመግደልና መላውን ሐረርጌ ለመቆጣጠር ሐምሌ 19 ቀን በአያሌ ከባድ መሣሪያዎች ...ተደገፈ ሜካናይዝድ እግረኛና ታንከኛ ሠራዊት በድሬዳዋ ከተማ ላይ ጥቃት ሰነዘረ።

ከዚህ በፊት በሲዳሞ፣ በባሌና እንዲሁም በዚሁ በሐረርጌ ቆላማ ክልሎች ስለተደረጉ ...ጊያዎች ጠላት ራሱ እንጂ በኛ በኩል ብዙ ስለማንናገር ጠላት በሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያን ወታደሮች ገደልን፣ በመቶ የሚቆጠሩ ታንኮችን አወደምን፣ ይህንን ያህል ...ሚ አውሮፕላኖች ጣልን እያለ ቢያወራም ባዕዳንም ሆኑ ኢትዮጵያዊያን እምነው ...ቀበሉት ብዙ አልነበሩም።

ሶማሊያ ኢትዮጵያን ወረረች ተብሎ የታመነው ሐምሌ 19 ቀን ድሬዳዋ ከተማ ላይ ...ራው ሠራዊት አደገኛ የሆነ የብረት ለበስ ጦር ጥቃት በሰነዘረ ጊዜ ነው። ድሬዳዋ ትንሽ ...ን ከአገራችን ከተሞች ሁሉ ዘመናዊና ውብ ከመሆኗ ባሻገር የብቸኛው የምድር ባቡር ...ግዣ አገልግሎት ማዕከልና የባሕር በራችን ከሆነው የጂቡቲ ሪፑብሊክ ጋር አገናኝ ነች።

ከሶማሊያ ሪፖብሊክ ጋር የሚያዋስነንን በመጠኑ ከአገሪቱ ክፍለ አገራት ሁሉ ...ዳ ስፋቱ የላቀ ብቻ ሳይሆን የወተት፣ የቅቤ፣ የሥጋ፣ የእሕል...

ሃገር የሆነው፣ የተፈጥሮ ጋዝና የነዳጅ ዘይት ቅምጥ ሀብት ያለውን ሀብታሙን ክፍለሃገር ሐረርጌን ከመሀሉ ሃገር ጋር በየብስ፣ በባቡር መጓጓዣ በጎማ ተሽከርካሪና በአየር የምታገናኝ ከተማ ነች።

የዓለም ማያ የግብርና ዩኒቨርስቲ፣ የአገሪቱ የጦር አካዳሚ፣ የመምህራን ማሰልጠኛ የመሳሰሉ የከፍተኛ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ተቋማት ያሉት ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚ እስተዋፆም ሐረርጌ ግምባር ቀደም ከሆኑት ጥቂት ክፍለ አገሮች አንዷ ከመሆን ሌላ ከታሪክም አንፃር ከፍ ያለ ስፍራ የላት ክፍለ ሃገር ነች። በድሬዳዋ ከተማ ላይ ጠላት የሰነዘረው ወረራ ለኢትዮጵያዊያን ሁሉ ሊዋጥ ቀርቶ የማይቀመስ ሬት ነበር የሆነብን።

ሐረርጌንና ጂቡቲን ከመሃል ኢትዮጵያ የምታገናኘዋን ድሬዳዋ ከተማ ከወረራ የመከላከል ጉዳይ ከማንኛውም ግምባር የበለጠ ትኩረት የሰጠነው ቢሆንም ሐምሌ 19 ቀን ጠላት የሰነዘረው ጥቃት ያልጠበቅነው ዱብ እዳ ነው የሆነው።

ምናልባትም ጠላት እኛን ለማሳሳትና ለማዘናጋት ያቀደውን ጥቃት ሰውር ድንገተኛነትን ለማግኘት ያስወራው ወሬና የሰጠን የሀሰት መረጃ ሳያገለግለው አልቀረም ለማለት እደፍራለሁ። ምክንያቱም ሐርጌሳ የሚገኘው የጠላት ሦስተኛው ወታደራዊ እዝ ያለውን ኃይል በሙሉ አግበስብቦ በመምጣት የቆሬን ግምባር ለሦስተኛ ጊዜ በማጥቃት ለመደምሰስ ታላቅ ዝግጅትና እቅድ አለው የሚል መረጃ ስለደረሰን ዋና ጥረታችን የቆሬ ግምባር በማጠናከር ላይ እንጅ  በድሬዳዋ ግምባር ላይ ያተኮረ አልነበረም።

በቆሬ የመከላከያ ይዞታችን ላይ ያለማሰለስ ሌትና ቀን የሚያደርገው የመድፍ ድብደባ መቆምና ጠላት ድምፁን ማጥፋቱ ቆሬን የማጥቃት መሰናዶ ምልክት አድርገንም ወስደን ነበር። በሰሜን ሶማሊያ ማለትም በሃርጌሣ ክፍለ ሃገር፣ በጂቡቲ ሪፐብሊክና በእኛ በድሬዳዋ ከተማ መካከል ያለው መልካምድር በጠቅላላ አልፎ አልፎ ዝናብ ከሸረሸረው አርድ መሬት፣ ምስጥ ከሰራው ኩይሳና የተሽከርካሪዎች ንቅናቄ የማያውኩ ትንንሽ ቁጥቋጦች በስተቀር ክልሉ ለጥ ያለ ሜዳና አፈር የቀላቀለ አሸዋማ ምድር ነው።

ሃርጌሣ ባለው የሶማሊያ ሦስተኛው ወታደራዊ እዝ ስር ቀልጅትና ቦሮማ በሚባሉ ሁለት የጠረፍ ወረዳዎች ላይ ተሰባስበው ለወረራ ያሰፈሰፉት የሶማሊያ እግረኛ፣ ሜካናይዝድ እግረኛ መድፈኛና ታንከኛ ቅምር መጠነ ሰፊ ጦር የሶማሊያን ሪፓብሊክ በሚያዋስነው በእኛ አዳልና ኢሳ አውራጃ አሳብሮ ወደ ድሬዳዋ ከተማ ለመምጣት ርቀቱ በግምት 200 እስከ 250 ኪ/ሜትር ወይም በሜካናይዝድ ጦር ጉዞ ፍጥነት ከ10 እስከ 15 ሰዓት የሚወስድ ጉዞ ነው።

ድሬዳዋን በድንገት ያጠቃው የጠላት ጦር ከቀልጂትና ከቦሮማ ተነስቶ የሁለቱን አገሮች የጋራ ድንበር በመጣስ በአራቢና በብዩሀ የእኛ የጠረፍ ወረዳዎች አድርጎ ጅቡቲንና ድሬዳዋን የሚያገናኘውን አውራ የተሽከርካሪ መንገድ ጀልዴሳ ላይ በማግኘት ያለችግር ነው ወደ ድሬዳዋ የገሰገሰው።

ጀልዴሳ ከድሬዳዋ ከተማ የሚርቀው በግምት ከ60 እስከ 70 ኪ/ሜትር ብቻ ነው። በእኛ በኩል የድሬዳዋ ከተማ ለጠላት ብረት ለበስ ጦር ጥቃት የተመቸ በመሆኑና ታንክን ለመከላከል የሚቻለው በታንክ ብቻ በመሆኑ ከዩጎዝላቪያ የመጡልንን ሰባ ታንኮችና ከየመን የመጡልንን ሰላሳ ሶስት ታንኮች በድምሩ አንድ መቶ ሦስት ታንኮች ወይም አንድ ታንከኛ ብርጌድ ያሰለፍነው በድሬዳዋ ግምባር ነበር።



እንባቢ እንደሚያስታውሰው ጅጅጋ በጠላት እጅ ወድቆ የወገን ጦር ወደ ሐረር አቅጣጫ ሲያፈገፍግ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ሥነ ሥርዓት ለማስከበር ከየመን የመጡልንን ቲ55 የሶቭየት ስሪት ታንኮች ከድሬዳዋ ወደ ቆሬ ስለላክን የድሬዳዋን ግምባር ከጠላት ብረትለበስ ጦር ለመከላከል የነበሩን ጠቅላላ ታንኮች ሰባ ብቻ ሲሆኑ በእግረኛ ሠራዊት ረገድ ደግሞ ያሰለፍነው ሦስት ሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦሮችና አንድ መደበኛ ነበልባል ብርጌድ ነበር።

የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት ወረራ ለመከላከልና ብሎም መልሶ ለማጥቃት የአየር ኃይላችን የሥራ ድርሻና የድሬዳዋ አውሮፕላን ሜዳ ወሳኝነት ስለነበራቸው የድሬዳዋን ከተማ ምዕራባዊ ዳርቻ የአየር ኃይላችንን ጦር ሰፈርና የአውሮፕላን ማረፊያውን ከጠላት ጥቃት እንዲከላከሉ የተደረጉት፣ ታንኮቻችን በጠቅላላው መደበኛው የነበልባል ብርጌድና አንድ የሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦር ነበሩ።

ከአውሮፕላን ማረፊያው በተዋሳኝ በጂቡቲ አቅጣጫ ከከተማው ሰሜን ምዕራብ ዳርቻ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪውን ፊት ለፊትና አካባቢውን ለመከላከል ሁለት የሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦሮች በስፋትና በጥልቀት ሰፊና ጠንካራ ምሽጎችን መሽገው የጠላትን ንቅናቄ በንቃት ሲጠባበቁ ከወዝአደሩ መደብ መሃል የተመለመለ አንድ ሌላ የሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦር ለሐረርና ለድሬዳዋ ግምባር ደጀን ወይንም ተጠባባቂ ከመሆን ሌላ የድሬዳዋን ከተማ ውስጣዊ ፀጥታ የሚያስከብር ነው።

ጠላት ጀልዴሳ ከደረሰ በኋላ ታንኮቹን ወደ ኋላ አስቀርቶ መድፎቹንና እግረኛ ሠራዊቱን ወደ ድሬዳዋ ከተማ ዳርቻ ከከተማው ሰሜን ምዕራብ አስጠግቶ እግረኛውን ሠራዊት ለጨበጣ ውጊያ ካዘጋጀ በኋላ ለሐምሌ 19 አጥቢያ ከሌሊቱ አሰር ሰዓት ጀምሮ በከተማውን ሰሜን ምዕራብ በሚከላከሉት ሁለት የሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለ ጦሮች የመከላከያ ይዞታን፣ የአየር ኃይሉን ሰፈር፣ የአውሮፕላን ሜዳውን፣ ኢንኮድ በመባል የሚጠራውን የምግብ ፋብሪካ፣ የስሚንቶ ፋብሪካውን፣ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካውን፣ የቴሌኮሚንኬሽን ማሠሪያ ቤት ሕንፃ የምድር ባቡሩን ጠቅላላ ይዞት ወዘተ በመድፍ ለሁለት ሰዓት ያህል ከደበደበ በኋላ ጎህ ሲቀድ የጨበጣ ስፍራ ይዞ የነበረው የጠላት እግረኛ ሠራዊት በድንገት ከተማው ውስጥ ገብቶ ሕዝቡንና ሠራዊቱን በማሸበር ለታንከኛው ሠራዊት ወሳኝ ጥቃት ለማመቻቸት ማጥቃት ጀመረ።

የወገን ጦር ምሽጉ ውስጥ ራሱን በሚገባ ከልሎና መክቶ ጠላት መግደያ መሬት ሊገባለት በታጠቀው ዘመናዊ አውቶማቲክ ጠመንጃና መትረየሶች አረገፈው። የእጥቂው ጠላት የመጀመሪያው ረድፍ በጠቅላላው ማለት ይቻላል ወገን ባዘጋጀለት እመግደያ መሬት ውስጥ ገብቶ ሲያልቅ ወዲያው ሁለተኛውን ረድፍ ወይም ደጀን ጦሩን ውጊያው ውስጥ በማስገባት ሁለተኛና ብርቱ የማጥቃት ጥረት አደረገ። ውጤቱ ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ ከመሆኑ በላይ የአየር ኃይል ተዋጊዎቻችን ሲነሱ የጠላት እግረኛ ሠራዊት መፈርጠጥ ሲጀምርና ሲከተሉ ነበር እያሌ የጠላት ታንኮች በሰፊ ረድፍና በጥልቀት በድሬዳዋ ከተማ ምዕራብ ሲገሰግሱ በራሪዎቻችን የተመለከቷቸው።

የድሬደዋ የጦር ግምባር አዛዥ ሌ/ኮሎኔል ተካልኝ ንጉሤ በቀጥታ ወደ ታላቁ የተመንግሥት ደውሎ ድስ ይበልህ ደስ ብሎናል የሶማሊያን ሠራዊት እንደ ገብስ አጭደን አስቀረነው ብሎ ሲያስደስተኝ የብሔራዊ ዘመቻ መምሪያችን የአስቸኳይ ምስጢር ቀይ ስልክ ረዳት ሌ/ኮሎኔል ገ/ክርስቶስ ቡሊ መነጋገሪያውን ሰጠኝ። የደወለው የአየር ኃይላችን አዛዥ ኮሎኔል ፋንታ በላይ ድሬዳዋ ከሚገኘው የአየር ኃይል መደብ የዘመቻ መምሪያ

ነው። ፋንታ በስልክ ሲያገኘኝ ሌላ ቃልና ንግግር ወይም ሰላምታ እንኳን ሳይጨምር "በጠላት ታንኮች ተጥለቅልቀናል" ነው ያለኝ።

ከዚያው ከድሬዳዋ ግምባር ሰው ደውሎ ሲያጠቃ የመጣውን የሶማሊያ እግረኛ ጦር ፈጅነው። ደስ ይበልህ ደስ ብሎናል ሲለኝ ነው ገብረክርስቶስ ያንተን ጥሪ የሰጠኝ ስለው "እውነት ነው የጠላት እግረኛ ከአንዴም ሁለቴ የሰነዘረውን ጥቃት ሚሊሺያው በሚገባ መክቶ እንደተነገርዎትም ፈጅቶ ስለአባረረውና ጨለማውም ስለከፈተ የኔ ሰዎች ተነስተው የሚሸሸውን እያሳደዱ በሚደበድቡበት ጊዜ ነው ታንኮቹን የተመለከቱት። እኛን ጨለማው ብቻ ሳይሆን የመድፍ ተኩስ አላነቃንቅ ብሎን በጣም ተቸግረን ነበር። ምናልባትም የእግረኛውን መሸሽ የተመለከተው መድፈኛም እብሮ ወይንም ሸሽቶ ተደናግጦ ሊሆን ይችላል የመድፍ ተኩስ ጋብ ስላለ ነው አውሮፕላኖቻችን መነሳት የቻሉት" አለኝ።

የጠላት ታንኮች ብዛት በግምት ምን ያህል ይሆናል? ማቆም ወይንም መግታት አይቻልም? የኛን ታንከኞችና እግረኞች እንዴት አገኘሃቸው፡ ብዬ ስጠይቀው፤ ታንኮቹ በሙሉ እኔ ያለሁበትን ግምባር ነው ከነባልባል ብርጌዱ ጋር የሚከላከሉት። በጣም ጥሩ ጦር ነው። ቢሆንም የመጣውን የጠላት ታንክ ማቆም አደጋች ይመስለኛል፤ ሲለኝ ያለንን የታንክ መጠን ታውቀዋለህ፤ ሕዝባዊ ሠራዊቱ በጠብመንጃ ታንኮችን መመለስ ስለማይችል ተስፋችን ሙሉ በሙሉ ባንተላይ ነው። ያሉንን አውሮፕላኖች አስነስተህ የጠላትን ታንኮች ማቆም አለብህ። የሞት ሽረት ጥያቄ ነው ብየው ተለያየን።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ጓድ ኮሎኔል ፋንታ ለጓድ ሌ/ኮሎኔል ገ/ክርስቶስ ደውሎ "ዛሬ ተፈጥሮም ጠላታችን ሆኗል። አይቼ የማላውቀው የዝናብ ዶፍና የጠላት መድፍ ተባብረው ሲወርዱብን ታንኮቹም ወደኛ እየቀረቡና አንዳንዶቹ ወደ አውሮፕላኑ ማረፊያ እየገቡ ስለሆነ አውሮፕላኖቹ መሬት ላይ እንዳሉ እንዳይጠፉ ወደ ደብረ ዘይት መላኩን ለሲቃመንበር ንገራቸው ይለዋል። ገ/ክርስቶስ የፋንታን መልዕክት ሲነግረኝ አጠገቤ የነበሩ የሲቪልና ወታደራዊ ባለሥልጣኖች በሙሉ አንገታቸውን ደፉ።

በዚህ ጊዜ ጅጅጋ የተፈጠረው ሁኔታ በድሬዳዋም ይደገማል። ታሪኩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው። የድሬዳዋን ከተማ ሁለት ላይ ከፍሎ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የሚወርድ ትልቅ ጅረት አለ። ይህ ጅረት በበጋ ደርቆ አሸዋ ብቻ ስለሚሆን የውሃ ችግር ያለባቸው አንዳንድ የከተማው ነዋሪዎች አሸዋውን እየጫሩ በሚያገኙት ውሀ ከብቶቻቸውን ያጠጣሉ ወይንም ለተለያዩ ተግባሮች ይገለገሉበታል። አሸዋው ሌሊት ሌሊት የከተማው ቤት አልባ ደሆችና መጠጥ ያሸነፋቸው ሰዎች መተኛ ፍራሽ ነው።

በክረምት ወቅት ከሐረርጌ ደጋማ አውራጃዎች ማለትም ከጋራ ጉራቻ፣ ከወበራ፣ ከጨርጨር ወዘተ የሚዘንበው ከባድ ዝናብ በዘነበ ጊዜ በአሸዋው ላይ ያለውን ሰውም ሆነ እንሰሳ ወይንም ሌላ ነገር ጠራርጎ በመውሰድና በመውረድ ከከተማው ጠርዝ ጀምሮ እስከ ሸንሌ አካባቢ ድረስ በተኛው ዘቅዛቃ፤ ጎድጓዳና እንዲሁም ሰፊ አሸዋማ ሜዳ ላይ በመተኛት ለጥቂት ወራት አንድ ሰፊና ጥልቅ ሐይቅ ከሠራ በኋላ ዝናብ ሲያባራ ወይንም በበጋው እፍላ ወቅት ውሃው ወደ ከርሰ ምድር ገብቶ ሳይደርቅ ይሠፍና ጥልቅ የጭቃ ማጥ በመሥራት ለተሽከርካሪዎች ብቻ ሳይሆን ለእንስሣትና ለሰውም አደገኛ ሁኔታ ይፈጥራል።

የአየር ኃይላችንን የጦር ሰፈር፤ የአውሮፕላን ሜዳውንና ከተማውን ግብቶ አድርገው ከከተማው በስተ ምዕራብና በስተ ሰሜን ምዕራብ ባለው መሬት ከከተማው ግራና ቀኝ ጠርዝ መሐል ለመሐል ሐምሌ 19 ቀን ከጥዋቱ በሁለት ሰዓት ገደማ ለጥቃት እየገፉ የመጡት የጠላት ታንኮች ከፊሉ ማለት ይቻላል እማጡ ውስጥ እየገቡ በመስመጣቸው



አሽከርካሪዎቹ ከታንኮቻቸው ውስጥ እየወጡ ሲሸሹ ለተመለከተው የጠላት ታንከኛ ጦር መካከል ድንጋጤና ሽብር ተፈጠረ።

ሆኖም በአየር ኃይሉ የጦር ሠፈርና በአውሮፕላን ሜዳው አቅጣጫ የመጡት የጠላት ታንኮች ምንም ሳንካ ስላልገጠማቸው የመድፍና የመትረየስ ጥይቶቻቸውን በወገን ጦር ላይ እየረጩ ለመጠጋት ሲሞክሩ የኛ ታንኮች ብቻ ሳይሆኑ እግረኛ ሠራዊታችን በእጻፍኔና በፀረ-ታንክ መሣሪያዎች አፀፋውን እየመለሰ ፍልሚያው በተጧጧፈበት ጊዜ ዝናቡ ቆም ብሎ ብቅ አለች።

ከጓድ ኮሎኔል ፋንታ በላይ ጋር በተነጋገርነው መሠረት በአገሪቱ ያሉንን ተዋጊ አውሮፕላኖች ሁሉ አስነስቶ የጠላትን ታንኮች አብዛኛውን ሲያጋያቸውና የኛም ታንኮች ከመከላከያ ምሽጋቸው እየወጡ በማጥቃታቸው ጠላት እያሌ ታንኮቹ ከውጊያ ውጭ ስለሆኑበት፤ ታንከኛው ጦር ብቻ ሳይሆን ሜካናይዝድ እግረኛው፤ እግረኛውና መድፈኛው ጭምር ወደ ጀልዴሳ አፈገፈጉ። ጠላት ያፈገፈገው ወዶ ሳይሆን በወገን መልሶ ማጥቃት ኃይል ተመትቶ ቢሆንም የለየለት ሽሽት ሳይሆን ሥልታዊ ማፈግፈግ ነው ያደረገው።

ጀልዴሳ የሚባለው ስፍራ በአካባቢው ገገር የሆነ መሬት፤ በዛፎችና በእፅዋት የተሸፈነ፤ ወንዝ ብቻ ሳይሆን የከርሰምድር ውሃም ያለው፤ ነፋሻና ለመከላከል ውጊያ አመቺ ስለሆነ ጠላት የሰውና የመሣሪያ ኃይሉን አሟልቶ ለእሱ ባመቸው ጊዜ ሁኔታ መልሶ ለማጥቃት ዓላማና እቅድ ነበረው።

በእኛም ወገን ጦር ላይ ከባድ ጉዳት የደረሰ ከመሆኑ ባሻገር ቀላል መሣሪያ የታጠቀ ሠራዊታችንን ከብረት ለበስ ጦር ጋር በማጋፈጥ ኃይላችን ሳይመናመን የገዛናቸው መሣሪያዎች ወደ ሃገር ገብተው የማያዳግም መልሶ ማጥቃት እስክናደርግ ድረስ የመሬት ይዞታችንን አጽንተን የመከላከሉን ውጊያ ስለመረጥን መከታተሉን አልፈለግነውምና ከዚያ በኋላ ያለው ጊዜ ተፋጦ መቀመጥ ሆነ። በጠላት ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተገኘውን ድል ለማመን ያዳገተን ጦራችንን ብናደንቀውና እጅግ ብንደሰትም የውጊያ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመለወጥ ባህሪ ስለአለው አዲስ አበባ በብሔራዊ የዘመቻ መምሪያ አዳራሽ አብረውን ለነበሩ ወታደሩም ሆነ ለሲቪል ባለሥልጣኖች ድላችንን ለማብሰር ስለአለቸኮልኩ ጭንቀቱና ውጥረቱ ቢያንስ እስከቀኑ አጋማሽ ጊዜ ድረስ እንደአለ ነበር።

በግምት ከጧቱ አራት ሰዓት ገደማ የማስታወቂያና መረሐብሔር ሚኒስትር ልጅ ሚካኤል እምሩ፤ የማዕድንና የኃይል ማመንጫ ሚኒስትር ጓድ ኃይሉ ይመኑና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም መሥሪያ ቤት የተወሰኑ እውቅ ሰዎች ተጠራርተው በመሰባሰብ ጽሕፈት ቤት መጥተው ብርቱ ሐዘንና ብስጭት በተመላው ስሜት "ለድሬዳዋ ምን መፍትሄ ነው ያዘጋጀኸው? የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ከድሬዳዋም አልፎ መሃል ሀገር ስለአለመምጣቱ ምን ዋስትና አለ" ወዘተ በተሰኘ ጥያቄ ነው የቀረቡኝ።

የሰዎቹን ሁኔታና የጥያቄያቸውንም ይዘት ሳመዛዝነው እኔ በግሌ ሃገር እንዳስወሰድኩና መፍትሄም መፈለግ ያለብኝ እኔ ብቻ እንደሆንኩ የሚገለፅ የክስ ዓይነት ጥያቄ ሁሉም በወል ቢሆንም በግል መፍትሄ ወይም አንድ ገንቢና ጠቃሚ ሀሳብ ሳይሰጡኝ ከሞቀ እልጋቸው ተነስተው በመምጣት ወንበር ላይ ለማድረው ግለሰብ ያንን የመሰለ ጥያቄ ማቅረባቸው ለማን ቢያፈላውም ራሴን ተቆጣጥሬም ከሃገር ፍቅር ስሜትና ቁጭት የመነጨ ነው ብዬ አለፍኳቸው፤ ከሁሉ በፊት ድሬዳዋን ከተማ አልተቆጣጠረም፤ በድሬዋም በኩል ሆነ በሌላው አቅጣጫ የመጣውንና የሚመጣውን ጠላት አይቀጡ ቅጣት ቀጥተን እንመልሰዋለን የሚል

መልስ ስለሰጣቸው የማሾፍ ያህል ስለተሰማቸው በተለይ የልጅ ሚካኤል ንግግር ብቻ ሳይሆን የተቆጡ መሆናቸው ከፊታቸው ይነበብ ነበር።

በእናንተ በኩል እኔ ምን እንዳደርግ ትመክሩኛላችሁ የሚል ጥያቄ ሳቀርብላቸው ሁሉም ቀደም ብለው የተማከሩበት ይመስላል። ለተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ ጠይቀን ወራሪው ሠራዊት ከድሬዳዋ አልፎ ሌላው የአገራችንን ክልል ከመያዙ በፊት የተኩስ ማቆም ውለታ ገብተን ባለበት እንዲቆም ማድረግ አለብን የሚል ሃሳብ አቀረቡልኝ። ሃሳባቸውን አልተቀበልኩም። ከሁሉ በፊት የድሬዳዋ ከተማ በጠላት ስላልተያዘ ጠላት ድሬዳዋን አልፎ ሌላ መሬት ወይም ክልል ይይዛል የሚያሰኝ ሁኔታ አልተፈጠረም።

የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ሦስት ክፍለ አገሮቻችንን በመውረር ከሞላ ጎደል ፍላጎቱን ወደሚያረካበት ሁኔታ ተቃርቧል ማለት ይቻላል። ይህንን ሁኔታ ተቀብለን በተኩስ ማቆም ውለታ ሳቢያ የሶማሊያ መንግሥት በወረራ የያዘውን የመሬት ይዞታ እንደያዘ እንዲቆይ መዋዋል ማለት በተዘዋዋሪ ወረራውን ሕጋዊ አድርጎ መቀበል ማለት ነው። ይህ ደግሞ የቀድሞ መሪዎቻችን በዚህ ዓይነት ተፅዕኖ ሲሰሩት የነበረውን ስህተት እኛ ልጆቻቸውም እንድንገመው ማለት ነው። በኔ በኩል የተባበሩት መንግሥታት ማህበር የሚባለው ዓለም አቀፍ አካል በተለይም የፀጥታው ምክር ቤት አባላት አብዛኞዎቹ ዓለምን ሲወሩ በቅኝ ግዛትነት ይዘው ሲረግጡ ሲዘርፉ ሲገፉ የኖሩ ኢምፔሪያሊስት መንግሥታት ስለሆኑ የእነሱን ድርጊትና ርዕዮት ለምትቃወመው አብዮታዊት ኢትዮጵያ ሃቀኛና ፍትኃዊ ፍርድ ይሰጣሉ የሚል እምነትም አልነበረኝም። የጥቂት ጊዜ ጉዳይ እንጅ ወራሪውን ሠራዊት ትጥቁን አስጥለንና የማያዳግም ትምህርት ሰጥተን ለመመለስ እንደምንችል እምነት ስለነበረኝ እንዲህ ያለ ችግር ውስጥ ራሳችንን መክተት አስፈላጊነቱ አልታዩኝም።

የድሬዳዋን ከተማ አጥቅቶ ለመቆጣጠር የመጣው ጠላት ያደረገው ብርቱ ሙከራ ሳይሳካለት ከፍ ያለ የሰውና የቁሳቁስ ዋጋ ከፍሎ ጂልዴሳ ላይ መልሶ መቋቋም በማድረግ በመከላከል ሥልት መሽጎ ተቀምጠ እንጅ ወዲያው ወይንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሌላ የማጥቃት ሙከራ ለማድረግ አላማረውም። በወገንም በኩል ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት በተሰውትና በቆሰሉት አባላት የሰው ኃይሉን በሚሟላት የመሬት ይዞታውን አሻሽሎ ወደ ጅልዴሳ በመቅረብ አመቺ ወታደራዊ መሬት በመያዝና ምሽጉን ከማጠናከር ሌላ እግረ ውስጥ ገብተው የተቀረቀሩትን በማውጣትና የተማረኩትን በማሰባሰብ የኛ ሁለት የታንክ ሻለቆች የጎደሏቸውን ታንኮች ከማሟላት ባሻገር አንድ ሌላ የታንክ ሻለቃ አቋቁመን ግንባር ላይ በማዋል አሽከርካሪና ተኳሽ ወታደሮችን ማሠልጠን ጀመርን።

ጠላት ከድሬዳዋ ከተማ ጠርዝ ፊቱን አዙሮ በማፈግፈግ 60 ኪ/ሜትር ያህል በመራቁና የመድፎች ድምፅ በመጥፋቱ የድሬዳዋ ሕዝብ ከየቤቱ ወጥቶ በደስታና ሆታ አብዮታዊ ሠራዊታችን ያገኘውን ድል ከማድነቅ ባሻገር በከተማው ማሕበራት የአመራር አካላት ውጊያው ወደተደረገበት ወረዳ ተሠማርቶ ጠላት የጣለውን አያሌ የቡድንና የነፍስወከፍ መሣሪያዎች እየለቀመ ለሠራዊቱ ከማስረከብ በላይ ለቁስለኞቹ ያደረገው ርዳታና እንክብካቤ ለዘላለም የማይረሳ ነው።

ከተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ጋር በሐረርጌ ደጋ በቆሬ፣ በአዳልና ኢሳ ቆላማ አውራጃ በጅልዴሳ አብዮታዊ ሠራዊታችን ተፋጦ ባለበት ጊዜ ጠላት ያልተጠበቀ ሌላ አደገኛ ጥቃት ለመሠንዘር አሁንም ሃርጌሣ ባለው በሦስተኛው





የሶቭየት ሕብረት ፕሬዝደንት እና እኔ የትብብር ስምምነት ውል ስንፈርም

እዝ የሚታዘዝና በተዋጊ መሐንዲስ፣ በኮማንዶ ጦርና በመድፎች ድጋፍ የተጠናከረ አንድ እግረኛ ክፍለጦር ከአላይበዴ የመሰብሰቢያ ሠፈሩ ተነስቶ ጅጅጋን ወደ ቀኝ በመተው በቱልቻና በቢቆ በኩል አድርጎ የቆሬን ግምባር ከሐረር ባቢሌ ላይ ከኋላ በመቁረጥ ወደ ባቢሌ መቅረቡ በመረጃ ተደረሰበት። በኮሎኔል ይርጋለም የሚመራ አንድ የሕዝባዊ ሠራዊት ክፍለጦር በአስቸኳይ ወደ ባቢሌ በመላክ ባቢሌንና ከቆሬ ወደ ሐረር የሚወስደውን አውራ መንገድ እንዳይቆጣጠር በማዳን በተደረገው ትግል ጠላት እይሎ የወገንን ጦር እየገፋ ወደ ባቢሌ ከተማና ወደ መንገዱ በመቃረቡ ከድሬዳዋ ግምባር አንድ የታንክ ሻለቃ አንስተን ለባቢሌ ግምባር በመደረብና መልሶ በማጥቃት የጠላትን ምኞት ብናከሽፍም ባቢሌ የቆሬን ግምባር ለመቁረጥ ቁልፍ ቦታ ከመሆኑ ሌላ ጠላት ወደተቀሩት የሐረርጌ ምሥራቅና ሰሜን ደጋማ አውራጃዎች መቃረቢያ በመሆኑ ከሐምሌ 23 ቀን ጀምሮ ትኩረትን የሚጠይቅ ሌላ ሦስተኛ ግምባር ሆነ። በዚህ ጊዜ ነበር ከሐምሌ 25 ጀምሮ ለሦስት ቀናት ጉብኝትና ለሁለተኛ ጊዜ የኢትዮጵያን ልዑካን መርቼ ወደ ሞስኮ የሔድኩት።

በመጀመሪያ ጉብኝቱ የሶቭየት ሕብረት መንግሥት የሸጠልንን መሣሪያዎች በአስቸኳይ እንዲልክልን በማስታወስ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ወዲህ በአፍሪካ ቀንድ ከተፈጠረው ሁኔታ አንፃርና ሰባትመቶ ኪ/ሜትር ጥልቀት የአገራችንን ድንበር ጥሶ የገባውን የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ለማስወጣት የሚያስችሉንን የመሣሪያዎች ዝርዝር ነው ይዘን የሔድነው።

በዚህ ጊዜ ለሶቭየት ሕብረት አመራር አካላት ስለአፍሪካ ቀንድ ማስረዳት ለቀባሪ አረዱት እንዲሉ ስለሆነ የምንፈልገውን እናገኝ ዘንድ ለማሳመን ብዙ መድከም አላስፈለገም። ጉብኝታችንና የጉብኝታችን ዓላማ በሶቭየቶች ዘንድ የታወቀና የተጠበቀ ከመሆኑ ባሻገር እኛ ከያዝነው የመሣሪያዎች ዓይነትና መጠን በላይ እነሱ ያስፈልጋቸዋል ያሉዋቸውን የገመቱትን በርካታ መሣሪያዎች ሊሰጡን ወስነው የተቀመጡ ብቻ ሳይሆን በሁለቱ አገሮቻችን መካከል የምንዋዋላቸውን የመከላከያ ተራድዖ ውሎች ተግባራዊ በማድረግ



ለሶቭየት ሕብረት ፕሬዝደንት ለጓድ ሊዮኒድ ብሬዥኔቭ ስለኢትዮጵያ ሁኔታ መግለጫ ሲሰጥ

ረገድ ኢትዮጵያ ተቀምጠው የሚረዱንና የሚያማክሩንንም የተለያዩ ወታደራዊ ጠበብቶች ለመላክ ተዘጋጅተዋል።

የሶቭየት ሕብረት መንግሥትና የኮሚኒስት ፓርቲው የአመራር አካላት በሙሉ የኢትዮጵያን አብዮት ከልብ ከመደገፍ ባሻገር የከዳቸውን የሶማሊያ መንግሥት በእኛ ላይ ሊበቀሉት እንደሚፈልጉ ብንረዳም ያዘጋጁልንን የመሣሪያዎች ዓይነትና መጠን ስለማናውቅ በክሬምሊን ቤተመንግሥት መላው የሶቭየት ሕብረት ኮሚኒስት ፓርቲ የፖለቲካ ቢሮ አባላት ባሉበት ስለአገሬ ወቅታዊ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ውስጣዊ ሁኔታ በአጭሩ ከገለጥኩ በኋላ የኢትዮጵያ አንድነት፣ አብዮትና የሕዝባችን ማህበራዊ ደህንነት ያንዣበበባቸውን የውስጥና የውጭ የወረራ አደጋ በመዘርዘር አገራችንንና አብዮታችንን ለማዳን የሚያስችለን አስቸኳይ የመከላከያ ድጋፍ ጠየቅሁ።

ካለንበት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ አንፃር የሚያስፈልገንን የመከላከያ ድጋፍ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ገለፃ ሳደርግ በኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊትና በተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት መካከል ስለተደረገው ውጊያና ብሎም በጊዜው ስላለው ወታደራዊ ፍጥጫ ብቻ ሳይሆን፤ የውስጥ ፀረ-አንድነትና ፀረ-አብዮት ኃያላት ኢሕአፓን ጨምሮ የሚያራምዱትን ሃገር የመገንጠልና ፀር-ሕዝብ ሽብር ለማሥረጻት ሁኔታውን



የሚገልፅ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ካርታ ላይ የሃገር ደህንነት ጓዶች ሥዕላዊ መግለጫ ሥለው እንዲሰጡኝ አድርጌ ነበር። በነበረብኝ የሥራ ጫናና የጊዜ እጥረት ምክንያት የሃገር ደህንነት ጓዶች ያዘጋጁትን ካርታ እስከዚያ ጊዜ ድረስ አልተመለከትኩትም ነበር።

በሶቭየት ጓዶች ፊት ካርታውን ስገልጠው እነ ጓድ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ወ/ሥላሴ፣ ፀረ-አንድነትና ፀረ-አብዮት ድርጅቶች በአጠቃላይ የሚቆጣጠሩትንና ሽብር የሚያካሂዱበትን ክልል ለማሳየት ብለው የኢትዮጵያን ቆዳ በሙሉ ማለት ይቻላል ለጠላት ማመልከቻ የመረጡት ቀለም ቀብተውት ስለነበር የሶቭየት ሕብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና ፀሃፊ ጓድ ብሬዥኔቭ በገለፃዩ መካከል ጣልቃ ገብተው “ጓድ መንግሥቱ ወደሌላው ገለፃዎ ከመሔድዎ በፊት ልጠይቅዎት የምፈልገው ነገር አለኝ” ካሉ በኋላ “ለመሆኑ አብዮቱ የመጣለት ሕዝብ፣ አብዮታዊው የመከላከያ ሠራዊትና አብዮታዊው መንግሥት ያሉት የት ነው?” ብለው ሲጠይቁኝ የሶቭየትና የኢትዮጵያ ጓዶች በሙሉ እኔም ጭምር በሳቅ አወካን።

“የጠላት ዓይነት፣ መጠንና ሽብር የሚያኪያሂዱባቸውን ቀበሌዎች በተመለከተ በመጽሐፍ የተሰጠው መዘርዘር ፍፁም እውነት ቢሆንም ስዕላዊው መግለጫ እጅግ የተጋነነ ነው። እኔም የተመለከትኩት አሁን ከእናንተ ጋር ነው” ስል ዳግም ሳቁ።

ገለፃዬን ሳጠቃልል፣ “አሜሪካዊያንና ግብረ አበሮቻቸው ምዕራብ አውሮፓዊያን ወገድ ድንጋይ ሦስቱንም አገሮች ማለትም፣ ሶቭየት ሕብረትን፣ ኢትዮጵያንና ሶማሊያንም ለመምታት ሲሉ የሶማሊያን ወረራ በፅኑ የሚደግፉ መሆናቸውን ከኛ ይልቅ እናንተ ታውቃላችሁ።

በእኛና በተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት መካከል በተደረጉ ውጊያዎች የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት የወደሙበትን መሣሪያዎች አሜሪካኖቹ ከሚተኩለት በፊት በመልሶ ማጥቃት ወራሪውን ሠራዊት ከአገራችን ረግጠን ማስወጣት አለብን። የምንዋጋው ከሰው ጋር ብቻ ሳይሆን ከጊዜም ጋር ስለሆነ ለጋሥ ድጋፋችሁ በአስቸኳይ እንዲደርስን ደግሜ አሳስባለሁ” ካልኩ በኋላ ገለጣዬን አበቃሁ።

የሶቭየት ሕብረት ኮሚኒስት ፓርቲ ዋና ፀሃፊ ጓድ ሊዮኒድ ብሬዥኔቭ አገሬንና ኢትዮጵያውያንን አስመልክቼ ስላቀረብኩት መግለጫ በራሳቸውና በፓርቲ ቢሮ አባላት ስም ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን በማለት ላቀረብኩት የመከላከያ ድጋፍ ጥያቄ ኢትዮጵያ ልውካን ከጠበቀው በላይ እርኪ፣ እጅግ ለጋሥና ታሪካዊ መልስ ሰጡን።

“ጓድ መንግሥቱ ባለፈው ጥቅምት በመጀመሪያ ጊዜ አገራችንን በጎበኙበት ጊዜ በወርዎ በኢትዮጵያ የሚካሄደውን ሕዝባዊ አብዮት አስመልክተው በሰጡን መግለጫ ያቀራረብዎ ብስለትና በእርቆ አስተዋይነትዎ በመደነቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ብሩህ አምሮ ባለው ሃቀኛ አብዮታዊ ወጣት የሚመራ ሃቀኛ ሕዝባዊ አብዮት ነው ብለን ከልብ መቀበል ሃቀኛ አቋም ስንይዝ አልተሳሳትንም።

በዚያን ጊዜ ከአደረጓቸው ፍሬያማ ንግግሮችዎ በተለይ የሶማሊያን ሕዝብ አብዮት አስመልክተው “በአፍሪካ ቀንድ ለፈነዳውና እናንተና የተቀሩትም ህብረተሰባዊ አገሮች ድጋፋችሁን ለሰጣችሁት የሶማሊያ ሕዝብ አብዮት የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ሌላ ማድረግ የሚቻልም በመንፈስ ስንደግፈው ቆይተናል። ዛሬ ደግሞ የታሪክ ፈቃድ ሆኖ በአፍሪካ ቀንድ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት መፈንዳት ለሁለቱ ኩታ ገጠምና ሰፊ የጋራ ድንበር ላላቸው እህትማማች ሕዝቦች ጥቅም ብቻ ሳይሆን የዓለምን አብዮት እድማስ ማስፋትና የማኅልበት አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ” በማለት ባደረጉት ንግግር እና እዚያ የተገኙ ጓዶቼ በሙሉ ተመስጠን ነበር።

በሶማሊያ መንግሥት የአመራር አካላት ክህደትና አብዮት ቅልበሳ የአፍሪካ ቀንድ ዛሬ የምናየው ሁኔታ ላይ መገኘቱ በእጅጉ የሚያሳዝን ነው። እርስዎ ቅድም በትክክል እንዳስቀመጡ የሶማሊያ መንግሥት አመራር፣ አብዮት በመቀልበስ ከኢምፔሪያሊዝም ወግና የኢትዮጵያን ሕዝብ አብዮት መውጋት የሚጠቅመው ኢምፔሪያሊዝምንና የአካባቢውን አድሕሮት ኃይላትን እንጅ የሶማሊያን ሕዝብ እንዳልሆነ እውቅ ከመሆኑ ባሻገር የሶማሊያ መሪዎች ለመስፋፋት ብለው በጫሩት ጦርነት ያለጥርጥር የሚያሸንፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ነው። ይህ ደግሞ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ከመውሰዳችሁ በፊት እስከ አሁን በተኪያሄደው ውጊያ ብቻ እውን ወይንም ገሐድ ሆኗል።

በአድናቆት በምንመለከተው አብዮት እስከአሁን ከሰጣችሁት አመራር በተጨማሪ የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት ወረራ ለመመከት ያደረጋችሁት ሕዝባዊ ንቅናቄ የጦር አደረጃጀትና ብሎም የውጊያ አመካከታችሁ ደግሞ አስደቆናል። የሶቭየት ሕብረት አብዮታዊያን ከኢትዮጵያ አብዮት ጎን በመሰለፋችን ኩራትና ክብር ይሰማናል።

የተስፋፊውን የሶማሊያ መንግሥት ሠራዊት እርስዎ እንዳሉት ከኢትዮጵያ ሪግ ለማስወጣት ካለ አውቶሚክ በንብ በስተቀር የተቀረው የሶቭየት ሕብረት ወታደራዊ ቴክኖሎጂ በአስፈላጊው መጠንና በአጣዳፊ ይቀርብላችኋል። እኛ እናንተን የምንጠይቀው የአሰብ ወደብና ከአሰብ አዲስ አበባ መንገድ በሚገባ እንዲጠበቁ ብቻ ነው።”

ምስኮ በገባን ማግሥት ተቀብለውን ይህንን ከዚህ በላይ የገለጽኩትን መልስና ተስፋ ከሰጡን በኋላ በዚያው ቀን ምሽት ለእኛ ክብርና አቀባበል በተደረገው የራት ግብዣ ላይ ስለቀጣዩ ሥራ ብዙ ከአነጋገሩኝ በኋላ ያሰናበቱን ነገውን ወደ ሃገርዎ በመሔድ በእናንተ በኩል ያለውን መሰናዶ ቀጥሉ፤ የኛ ሰዎችና መሣሪያዎች ይከተሏችኋል በማለት ነበር።

## ምዕራፍ ሠላሳ አምስት

# ከሞስኮ ስንመለስ በአገራችን የጠበቁን ሁኔታዎች

በኔ የተመራው ልዑካን ከሞስኮ ሲመለስ ራሱን የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ብሎ ማለት የሚጠራው አምስተኛ ረድፍ እኛን በነጭ ሽብር ለመቀበል በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ፋት ድግስ ደግሶልን ነበር። የኤርትራ ገንጣዮች የአስመራን፣ የምፅዋንና የባሬንቱን፣ ራሱን የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ህብረት ብሎ የሚጠራው ተስፋ ለዘውድ የፊውዳል ታጣቂ የጎንደርን ከተማ ከብበው በነበረበት ጊዜ፤ የሐረርጌ፣ የባሌና የሲዳሞ፣ ጠረፍ አውራጃዎች በተስፋፊው የሱማሊያ ወራሪ ሠራዊት በመያዛቸው ባዕዳን የሰላማችን፣ የእድገታችንና የአንድነታችን ፀሮች ብቻ ሳይሆኑ የውስጥ አድሀሮትም ኢትዮጵያ አለቀላት ብለው ሲያሟርቱ፤ የኢሕአፓ አመራር አካላትና ጠቅላላ አባላቱ ግድየለም የሱማሊያ ሠራዊት አዲስ አበባ ከተማ መሿለኪያ ሲደርስ እንከላከላለን በማለት ከማፌዝ ባሻገር በአገር ላይ የደረሰውን ጥቃትና ውርድት የደርግ ውድቀትና የእነሱ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ማማ ላይ መውጣት አድርገው ስለሚመለከቱ በደስታ መፈንጠዝ ብቻ ሳይሆን ለወራሪዎቹና ለገንጣዩቹ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ያልሰጧቸው ድጋፍ አልነበረም።

የኤርትራ ገንጣዮች ከነገ ዛሬ በአሥመራ መንግሥት እናውጃለን ሲሉና የሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት የድሬዳዋን ከተማ እስከመያዝ ድረስ ሲጥር አብዮታዊ ሠራዊታችን በጠላቶቹን ህልምና ምኞች እያመከነ በመጠናከር ብሎም የመልሶ ማጥቃት መሰናዶውን ሲጀምር የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ነኝ የሚለው ድርጅት መሪዎች ከኃዘንና ከብስጭት አልፈው ወደ እብደት ተሸጋግረው ነበር ማለት ይቻላል።

ሐምሌ 27 ቀን 1969 ዓ.ም ከሞስኮ ጠዋት ተነስተን በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ የምንገባ ስለመሆናችን ደርግ ውስጥ ባሏቸው ወኪሎቻቸው አማካኝነት መረጃ ደርሷቸዋል። በእኔ ላይ ብቻ ሳይሆን አብረውኝ ባሉ የልዑካኑ አባላት ላይና እንዲሁም አውሮፕላን ማረፊያ ሊቀበሉን በሚመጡ የደርግ አባላት፣ በመከላከያ ሠራዊቱ የአመራር አካላትና ሚኒስትሮቻችንም ላይ የሞት ቅጣት በይነዋል።

ለግድያው አፈፃፀም ያዘጋጁት እቅድ ሻምበል አምሐ በተባለ የፖሊስ ሠራዊት መኮንን የሚመራ የነፍስ ገዳዮች ቡድን በቦሌ መንገድ ግራ ቀኝ መንገዱ ዳር ባሉ ደሳሳ ጎጆዎች ውስጥ ተከልለው በማድፈጥ እኛን የያዙ ተሽከርካሪዎች ዒላማ ሲገቡላቸው ባዙቃ በተባሉ የአሜሪካ ስሪት ፀረ-ታንክ መሣሪያዎች መትተው ተሽከርካሪዎቹ ሲጋዩ በሚፈጠረው ሽብር የሞት ፍርድ የፈረዱባቸውን ሰዎች በመትረየስ ለመልቀም ነው። ሁልጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ ይህንን ውሳኔ የሰጡት ወጥመዱንም ያዘጋጁት የኢሕአፓ ከፍተኛ የአመራር አካላት




ከፊሉ እንጅ ሁሉም የተስማሙበት ውሳኔ አልነበረም። እነ ብርሃን መስቀል ረዳ፣ ጌታቸው ማሩና ይህንን ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት በኔ ላይ የተሞከረውን ግድያም በፅኑ ተቃውመዋል።

ይህንንና ሌላም መረጃዎችን ማግኘት የተቻለው ፓርቲው በፀረ-አብዮት ተግባሩ ከሕዝብ ተተፍቶና ተመትቶ ህልውናው ከከሰመ በኋላ የእርምት እርምጃ በተሰኘ ውሳኔያቸውና በፍቃዳቸው ወደ አብዮቱ ሰፈር የተመለሱ አባላት ከሰጡት የምስክርነት ቃል ነው።

በፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካላት መካከል ከፍተኛና ብዙ የመርህ ልዩነት ከመኖሩ ሌላ አብዮተኞችን በግፍ መግደል ያሳዘናቸው ግለሰቦች ግድያው ከመፈፀሙ በፊት ለመንግሥት በሰጡት መረጃ መሠረት ልዑካኑ ቦሌ ከመድረሱ ከአንድ ሰዓት በፊት ለግድያ ያደፈጡት ነፍሰ ገዳዮች በወታደር ተከብበው እጃቸውን እንዲሰጡ ቢጠየቁ ተኩስ በመክፈታቸው ከአንድ ሰዓት ባላነሰ ጊዜ የቦሌ ከፍተኛ ቀበሌ የቀውጢ ተኩስ አውድማ ከሆነ ባኋላ የነፍሰ ገዳዩ ቡድን አባላት አንድም ሳይቀሩ ከነመሪው ተደመሰሱ።

የአባዲና ፖሊስ ኮሌጅ ምሩቅ የሆነው የቡድኑ መሪ፣ ብልህ፣ ፈጣንና እንደበተ ርቱዕ የሆነ አስመሳይ መኮንን በአብዮታችን ፍንዳታ ማግሥት መለዮ ለባሽ ካድሬ ለማፍራት ብለን ከመለዮ ለባሹ መካከል ወጣት መኮንኖችን እየመለመልን ወደ ታላቋ ሶቭየት ሕብረትና ወደ ተቀሩትም ህብረተሰባዊ አገሮች ለትምህርት ስንልክ ከመጀመሪያዎቹ ጋር ከከፋ ክፍለ ሃገር ፖሊስ የተላከ መኮንን ነው።

ለአስር ወራት ያህል የፖለቲካ ትምህርት ተልእኮአቸውን በሚገባ ፈፅመው ከተመለሱት አንዱ በመሆኑ አብዮታዊ ሰደድ የተባለው ድርጅት አባል ከመሆኑ ሌላ በሃገር ውስጥ ላቋቋምነው የፖለቲካ ትምህርት ቤት መምህርነትም ተመርጦ በሚያስተምርበት ጊዜ በፖለቲካ ትምህርት ቤቱ ቤተመጻህፍት ውስጥ እያደሩ ማርክሲዝም ሌኒንዝምን የሚያጠኑ በርካታ ወጣት ምሁራንን ሌሊት ከነቤተመጻህፍቱ በፈንጂ ያጋየ ግለሰብ ነው።

እኔ ለፖለቲካ ተማሪዎች፣ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ምረቃና በሌሎችም ምክንያቶች በአራት ኪሎና በስድስት ኪሎ ጎዳና ሳልፍና ሳገድም ከመንገዱ ዳርቻ ባሉ ከፍተኛ ሕንፃዎች ላይ በማድፈጥ በባዙቃ ለማጋየት ከአንዴም ሁለቴ ሙከራ አድርጎ ያልተሳካለት ሠርጎ ገብ የኢሕአፓ ነፍሰገዳይ ቡድን የአመራር አካላት አባል ነበር።

## ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

# የኢሕአፓ አደገኛ ሴራ በቆሬ የጦር ግምባር

ከሐረርጌ ቆላማ የጠረፍ አውራጃዎች አንዱ የሆነው የጅጅጋ አውራጃ በጠላት እጅ ወድቆ የወገን ጦር ጨለማን ከለላው አድርጎ በሚያፈገፍግበት ጊዜ የጠላት መድፈኞች እየተከታተሉ በሚያደርጉት ድብደባ መበሳጨቱን እንደ በጎ ነገር የሚመለከቱት የኢሕአፓ ሰርጎ ገቦች ባደረጉት ቅስቀሳና ግፊት የተፈጠረውን ሥርዓተ አልበኝነት በመጠቀም ዝርዝሩን በሌላ የመጽሐፉ ክፍል ለማብራራት ቃል መግባቴ ይታወሳል።

"ኢትዮጵያ አለቀላት" እያሉ ፀሮቿ ሲያሟርቱ ትግሉ እንደነሱ ምኞትና ፍላጎት ባለመስመሩ የኢሕአፓ መሪዎች በተለይ ክፋኛ ከመበሳጨት አልፈው ወደማበዱ አምርተው ነበር ለማለት ያስደፈረኝ አዲስ አበባ በቦሌ መንገድ ላይ ካቀዱት ግድያ ይበልጥ በቆሬ አብዮታዊ ሠራዊታችንን ከጠንካራ ምሽጉ አስወጥተው በመበተን ለወራሪው ጠላት ድልን በሰሀን ለማቅረብ ያደረጉት ጥረት ነው።

ወራሪው የሶማሊያ ሠራዊት የድሬዳዋን ከተማ አጥቅቶ ለመያዝ ሞክሮ በአብዮታዊ ሠራዊታችን ተጋድሎ መክሸፉንና ከዚያም የቆሬን መከላከያ ከኋላ ለመቁረጥ በባቢሌ በኩል ያደረገውን ሌላውን ያልተሳካ የጠላት ሙከራ እንደተሳካና እንዳለቀለት የጠላት ድል አድርጎ በቆሬ ግምባር ምሽግ ውስጥ ለሚዋጋው ጦር "ድሬዳዋ በሶማሊያ ጦር ተይዟል፣ የቆሬም ምሽግና በባቢሌ በኩል በመጣ ጠላት ከኋላ ተቆርጧል፣ ኢትዮጵያ አልቆላታል። ጉድጓድ ውስጥ ተቀምጠን ቀናችንን የምንቆጥረው ከፊታችን ወይም ከኋላችን ወይም ከሁለቱም አቅጣጫ እስከንመታ ድረስ ነው። ሐረርጌ፣ ባሌና ሲዳሞ በሶማሊያ ሠራዊት ተይዞ ሲሆን፣ ኤርትራ በገንጣዮች፣ ጎንደር በኢዲዩ ተይዟል። የተቀሩት የኢትዮጵያ ክፍሎች በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ሠራዊት ቁጥጥር ስር ናቸው" ወዘተ እያሉ እያባረና በታኝ ቅስቀሳ በማድረግ ሠራዊቱን ማስኮብለል ጀመሩ።

የመከላከያ ምሽጋችን በመጠናከሩ የጠላት የመድፍ ድብደባ ጉዳት በማያደርስብን ሁኔታ ላይ ነን ባንልም የእኛም መድፈኞች አፀፋውን እየመለሱ ጠላትን መገሠጽ የጀመሩበት፣ የስንቅ አቅርቦትና የሕክምና አገልግሎት በጣም በተሻሻለበት ጊዜ ፍፁም ተረጋግቶ የነበረው ሠራዊት፣ አንዳንዱ መሣሪያውን ምሽጉ ውስጥ ጥሎ ወታደራዊ ልብሱን በማውለቅ ከደት ማዘወተሩ ከፍ ያለ ሥጋት ላይ ጣለን።

የዚህን ምክንያት ለማወቅና ብሎም መፍትሄ ለመሻት እያሌ ጠንካራ የአብዮቱ ካድሬዎች ከሲቪሊና ከመለዮ ለባሽ ውስጥ እየመረጥን ወደ ቆሬ ግምባር ላክን። በተጨማሪም ሌሊት ከምሽግ እየወጡ የሚጠፉትን የሠራዊት አባላት አድፍጠው የሚጠብቁ ዘቦችም ከምሽጉ ኋላ እንዲያደፍጡ አደረግን።

በጥቂት ቀናት ውስጥ አምስት የሕዝባዊ ሠራዊት አባላት ጓደኞቻችና የአንድ ክልል ሰዎች ሌሊት ከምሽጋቸው ወጥተውና ወታደራዊ ልብሳቸውን ለውጠው ሊኮበልሉ ሲሞክሩ ተይዘው ሲመረመሩ በሰጡት ቃል፣ ሠራዊቱ ውስጥ ሰርገው የገቡ የኢሕአፓ ወኪሎች በብዛት እንዳሉ ሠራዊቱን የሚያሸብሩና የማያስኮበልሉ ሌሎች በየጦር ክፍሉ በህቡዕ ተቋቁመው እንደሚሠሩ ብቻ ሳይሆን ባመቻቸውና በተለይም ጠላት የመድፍ ተኩስ በሚከፍትበትና በሚያጠቃበት ጊዜ ከኋላ ጠንካራና ጀግና የሠራዊቱን መሪዎችና ወታደራዊ ካድሬዎች እንደሚገድሉ ማወቅ ተቻለ።

አዲስ የተላኩት የፖለቲካ ካድሬዎች ከኢሕአፓ ወኪሎች ጋር በቀጥታ ሳይጋጩ ራሳቸውን ሠርጎ ገብ የኢሕአፓ ወኪል አስመስለው በመቅረብና በረቀቀ ዘዴ የኢሕአፓን ሌሎችም በሙሉ ከነአመራራቸው ማወቅ ከቻሉ በኋላ ልቅም አድርገው በማውጣትና ሠራዊቱን በመሰብሰብ በሠራዊቱ ፊት አቆሙዋቸው።

ሠራዊቱም ማንነታቸውን ከሚያከናውኑት ተግባራቸው ጭምር ሲያጋልጣቸው፣ ተስፋ በመቁረጥ ማንነታቸውን ሳይክዱና ሳይከልሉ "ኢሕአፓ ያሸንፋል! ኢሕአፓ ለዘለዓለም ይኑር!" በማለት ራሳቸውን ስላጋለጡ በጦር ሜዳ ሕግ መሠረት በሠራዊቱ ፊት በጥይት ከተመቱ በኋላ የሠራዊቱ ሥነሥርዓት አክባሪነትና የተዋጊነት ሞራል በሠራዊቱ ውስጥ በነበረው አንድነትና መተሳሰብ፣ መፈታቀር ከነበረበት ተመለሰ።

ከቆሬ ግምባር በተገኘው ትምህርት በመላው አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊታችን ውስጥ ሠርገው የተሰገሠጉትን ብቻ ሳይሆን ከመላው የአገሪቱ ክልሎች፣ ከተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች፣ ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ከማምረቻና ከልዩ ልዩ አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች፣ ከከነማትና ከገበሬዎች ማህበራት ወዘተ የኢሕአፓ ወኪሎችን ሕዝቡ እያጋለጠ ከመሀሉ መንጥሮ ማውጣት የቻለው ከቆሬ የጦር ግምባር በተገኘው ልምድ ነው ማለት ይቻላል።

ይህ ሲሆንና ሲደረግ ግን ወያኔ አብዮቱን ሲወንጅል ብዙ ያልሆኑና ያልተሠሩ ወንጀሎች ፈጥሮ ባቀረባቸው የክስ ዶሴዎች ላይ እንደቀላመደው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተጋለጡ አምስተኛ ረድፎችን እንቅቶና አቃንቶ የአብዮቱ ወገን አደረጋቸው እንጅ አልገደላቸውም። የሞቱት የገደሉት ብቻ ናቸው።

## ምዕራፍ ሠላሳ ሰባት

# ለመልሶ ማጥቃት ውጊያ የተደረጉ መሰናዶዎች

አገራችንንና አብዮታችንን ለማዳን የሚያስፈልጉንን የመከላከያ ድጋፎች የሶቭየት ሕብረት መንግሥት በሚያስተማምንና በአፋጣኝ እንደሚያቀርብልን ቃል ከመግባት ባሻገር በሁለቱ አገሮቻችን መካከል ለ12 ዓመታት ፀንቶ የሚቆይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ በአጠቃላይ ሁለገብ የሆነ ውለታ ተዋውለን ተመለስን።

የሶቭየት ሕብረት ልዑካን ወደ አዲስ አበባ ከመምጣታቸው በፊት ለመልሶ ማጥቃቱ ዘኬታማነት ከአማካሪ ልዑካን ጋር በጋራ የምንሠራቸውንና በእኛ ብቻ መሠራት ያለባቸውን የመሰናዶ ዝርዝሮች ከዚህ በተመለከተው ሁኔታ በዓይነት፣ በመጠንና በጊዜ ሠንጠረዥ አዘጋጀን።

ከሶቭየት ሕብረት ጓዶች ጋር በጋራ የሚደረጉ መሰናዶዎች

ሀ. ወደ ሶቭየት ሕብረት ሔደው አስቸኳይ ሥልጠና የሚሰጣቸውና ከተለያዩ መሣሪያዎች ጋር ትውውቅ የሚያደርጉ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አባላት፣

1ኛ/ ተዋጊና የመጓጓዣ አውሮፕላኖችን የሚያበሩ የአየር ኃይል አባላት ዝርዝር

2ኛ/ ተዋጊና መጓጓዣ ሄሊኮፕተሮችን የሚያበሩ የምድር ጦር አቪየሽን አባላትን ዝርዝር

3ኛ/ ተዋጊዎች፣ ፈንጂ ጠራጊዎች፣ መጓጓዣ መርከቦችንና ጀልባዎችን የሚያንቀሳቅሱ የባሕር ኃይል አባላት ዝርዝር

ለ. በሃገር ውስጥ አስቸኳይ ሥልጠና ማግኘት አዲስ መደራጀትና ከተለያዩ መሣሪያዎች ጋር ትውውቅ ማድረግ ያለባቸውን የምድር ጦር ልዩ ልዩ ተዋጊ ክፍሎችን ማለትም፤

1ኛ/ የታንክ ብርጌዶችን
2ኛ/ የመድፍ ብርጌዶችን
3ኛ/ አየር መቃወሚያ ሻለቆች
4ኛ/ ፓራኮማንዶ ብርጌዶችን
5ኛ/ መደበኛ እግረኛ ክፍለ ጦሮችን
6ኛ/ ባለጎማ ተሽከርካሪዎች አሽከርካሪዎች ሥልጠና
7ኛ/ የመገናኛ ባለሙያዎች ሥልጠና
8ኛ/ የተዋጊ መሐንዲሶች ሥልጠና
9ኛ/ ከቃሬዛ እንሺ ጀምሮ የአምቡላንስ ነርሶች የተለያዩ ዓይነትና ደረጃ ያላቸው ድሬሰሮች ሥልጠና
10ኛ/ ሁለተኛ ዙር የሕዝባዊ ሠራዊት ሥልጠና
11ኛ/ በተለያዩ ሞያ ለተለያየ አመራር የሚሰጡ የበታች ሹማምንት ሥልጠና
12ኛ/ መሰመራዊ ወጣት መኮንኖች ሥልጠና

13ኛ/ ከሻለቃ እስከ ክፍለ ጦር ደረጃ አመራር የሚሰጡ ከፍተኛ መኮንኖች ሥልጠና። እነዚህ ከላይ የተገለፁት የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊትን መልሶ ለማጥቃት የሚደረጉ መሰናዶዎች ናቸው ቢባሉም ለሶቭየት ሕብረት መንግሥት ያቀረብነው የመሣሪያ ዓይነትና የመጠን ዝርዝር፣ ከዚህ ጋር የሚሄደው የሠራዊቱ ስልጠናና አደረጃጀት በስሜንም የምናደርገውን የመልሶ ማጥቃት ውጊያ መሰናዶ ያካተተ ነበር።

**መ. ለመልሶ ማጥቃቱ መሰናዶ በኛ በኢትዮጵያዊያን ብቻ የሚደረጉ ዝግጅቶችና የሚመቻቹ ቅደመ ሁኔታዎች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ።**

1ኛ/ የመልሶ ማጥቃቱ ተቃዋሚና ለስኬታማነቱ ፀር የሆኑትን ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ኃይላት በአጠቃላይ፣ አምስተኛውን ረድፍ በተለይ ቢያንስ ከሸዋ፣ ከሐረርጌ፣ ከሲዳሞና ከባሌ ወዘተ ክፍለአገራት በተቻለ መጠን ለቃቅሞ በማረሚያ ቤት ማቆየት፣

2ኛ/ የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት በጦር ግምባሮች ላይ ሲያተኩር፣ ፀረ-አንድነት፣ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-አብዮት ኃይላት ከኋላ የሚያካሂዱትን ሻጥርና በሕዝቡ ላይ የሚነዙትን ሽብር የሚከላከሉ የአብዮት ጥበቃ ሠራዊትን በየከልሉና በተለይም በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባ ማቋቋም።

3ኛ/ የሶማሊያ መንግሥትና ወራሪ ሠራዊቱ የእኛን መልሶ ማጥቃት የመከላከል አቅም እንዳይኖረው አየር ኃይላችን የሶማሊያን መንግሥት የአየር ክልል ጥሶ በመግባት የመከላከያ ሠራዊቱ መገልገያ የሆኑ የመገናኛ ማዕከሎች ድሮችን፣ የመሣሪያ፣ የጥይትና፣ የነዳጅ፣ የስንቅና ትጥቅ ግምጃ ቤቶችን፣ የአውሮፕላን ሜዳዎችን፣ ልዩ ልዩ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋሞችን በማውደም የማዳከም ተግባር ማከናወን ነበር።

4ኛ/ ለመልሶ ማጥቃቱ ተሳትፎ የሚዘጋጁበትን የተለያዩ የጦር ክፍሎች ማሰልጠኛ ተቋማት በተመለከተ የምድር ጦር ልዩ ልዩ የቴክኒክ አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ማለትም፣ የምድር ጦር ህክምና የመገናኛ መሀንዲስ ማመላለሻ ወዘተ በየሞያቸው በየከፍላቸው የቴክኒክ ሞያተኞችን እንዲያሰለጥኑ

5ኛ/ ተዋጊ ክፍሎችን ማለትም፣ መደበኛ ክፍለ ጦሮችን በትግራይ ክፍለ ሃገር ከዊሃ የጦር ሰፈር፣ በጎንደር ክፍለ ሃገር በአዘዞ የጦር ሰፈር በሸዋ ክፍለ ሃገር በደብረ ዘይት ወረዳ በለምለም የጦር ሰፈር በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በአዋሳ የጦር ሰፈር ሦስቱን ፓራኮማንዶ ብርጌዶች በሸዋ ክፍለ ሃገር በለገዳዲ ወረዳና በአርባ አዋሽ እንዲሁም በሲዳሞ ክፍለ ሃገር በዝዋይ የታንክና የመድፍ ብርጌዶችን በአዋሽ አርባ ወዘተ ማሠልጠኛ ተዘጋጅቶ ነበር።

የሶቭየት ሕብረት አማካሪ ልዑካን እንደመጡ በኛ በኩል በተደረገው የመሰናዶ ዝርዝርና የአፈጻፀም ፕሮግራም ላይ በጋራ አስፈላጊው ውይይት ተደረገ።

ከቀረበው ዝግጅት ዘጠና በመቶ የሚሆነውን በአድናቆት ደግፈው በቀሩት በጥቂቶቹ ላይ የማሻሻያ ሃሳብ ሰጥተው በአስቸኳይ ወደተግባር እንድናመራ የጋራ ስምምነት ከተደረገ በኋላ በኛ የአቅርቦት ጥያቄና ፕሮግራም መሠረት የጦር መሣሪያዎቹን በአሰብ ወደብ ማቅረብ ተጀመረ።

ለመሰናዶው ተግባራዊነት በወጣው ፕሮግራም መሠረት ሁሉም ነገር በሚያስደስት ፍጥነትና ሕብረት እየተካሄደ እያለ እክል የገጠማቸው ጉዳዮች ከዚህ የሚከተሉት ብቻ ነበሩ። እነሱም፤

1ኛ/ እጅግ ውስብስብና ዘመናዊ የሆኑትን መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ያውሉ ዘንድ እንዲሠለጥኑ ከምንፈልጋቸው ሰዎች በተራ ወታደርነት ደረጃ የተማረ የሰው ኃይል በሚያስፈልገው ዓይነትና መጠን ለማግኘት ያለመቻላችን

2ኛ/ ለመኮንኖች ማሠልጠኛ የተወሰነው ጊዜ እጅግ ማጠር፤

3ኛ/ ታንከኛውን ሠራዊት በማሠልጠን የገጠሙ የተለያዩ ችግሮች ነበሩ።



ታንከኛውን በተመለከት የገጠሙን ችግሮች:-

ሀ. በሌሎች የከባድ መሣሪያዎች ሥልጠና እንደተከሰተው ሁሉ በታንኮች ላይ ለመሠልጠን የሚያስችል የትምህርት መሠናዶ ያላቸውን ወጣቶች ለማግኘት ያለመቻሉ፤

ለ. እያንዳንዱ ዘመናዊ የሶቭየት ሕብረት ሥሪት ታንክ ክብደቱ 50 ቶን ሲሆን እንዲህ ያለ ክብደት ያላቸውን በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ታንኮች ከአሰብ ወደብ እንስቶ ወደሚፈለጉበት ሥፍራ ማጓጓዣ ሲያስፈልግ በሶቭየት ጓዶች በኩል ይህ ታስቦ ከታንኮቹ ጋር የታንክ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ሳይታከሉ መቅረታቸው ነው።

ሐ. ታንኮች ከባድ ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው በልዩ የታንክ መጓጓዣ ተጭነው ወደ ውጊያ ወረዳ በመቅረብ ጥቅም ላይ የሚውሉ የጨበጣ መሣሪያ እንጅ ከጦር ሜዳ ውጭ ረዥም ርቀት መንዳት የሌለባቸው ተሽከርካሪዎች ሆነው ሳለ የመልሶ ማጥቃቱ ውጊያ የሚካሄድበት የምሥራቅ የጦር ግምባር ከአሰብ የሚርቀው ከ1800 ኪ/ሜትር በላይ መሆኑ፤

መ. ታንኮቹ እንዳሻቸው ይሁኑ ብለን ብንወስንና እስከ ጦር ግምባር ቢነዱ በቅርቡ ዘሪያው ጊዜ በብዙ ሚሊዮን ብር ከአሰብ እስከ አዲስ አበባ የተነጠፈው የአስፋልት መንገድ ፍፁም የሚፈርስ ብቻ ሳይሆን ከሁሉም በላይ ጊዜ ያለመኖሩ።

ጊዜ ሳናባክን ታንከኛውን ሠራዊት በማሰልጠን ረገድ የገጠመን ችግር ለማስወገድ ታንኮቹን ከአሰብ ወደ መሃል ሃገር ለመንዳት ከመሞከር ይልቅ የሚሰለጥነው የሰው ኃይል ታንኮቹ ወደ አሉበት ወደ አሰብ ወደብ እንዲሄድና በአካባቢው ሥልጠና እንዲከናወን አደረግን።

ይህ ዘዴ ለሥልጠናው የወሰነውን አጭር ጊዜ ሳናባክን ሥልጠናውን እያኪያሄድን ምናገኘው ጊዜ የታንክ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ከሶቭየት ሕብረት እንዲመጡልን ማድረግ ብችልም ሥልጠናው የተካሄደው በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ነበር።

ሥልጠናው በሚካሄድበት ወቅት የአሰብ አካባቢ ከ40 ዲግሪ በላይ ይሞቅ ስለነበረ ዚህ የሙቀት ኃይል በጋለው ብረት ውስጥ ገብተው ማሽከርከርና ተኩስ የሚማሩት ወታደሮች በእሳት እየተጠበሱ ወይም እየተቀቀሉ ነበር ማለት ይቻላል።

እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቶ ሰማኒያው በላይ ማሀይም ስለነበረ መደበኛ የቀለም ትምህርት ያላቸውን ወጣቶች በማግኘት የገጠመንን ችግር ማቃለል የተቻለው በቅድመ አብዮት የነበሩትን የቀለም ትምህርትና ልዩ ልዩ ወታደራዊ እውቀት የነበራቸውን የመከላከያ ሠራዊት አባላት አዲስ በሚደራጀው ሠራዊት ውስጥ በማስገባት እንደ እርሾ በመጠቀምና ድህረ መሠረተ ትምህርት ያላቸው ወጣት ገበሬዎች መደበኛ ውትድርና በገፍ በመመልመል ነበር።

የመሰናዶው ፕሮግራም ከአቀፋቸው የሥልጠና ዝርዝሮች ውስጥ በጊዜ እጥረት ምክንያት ያልተሳካልን ነገር ቢኖር፤ ከሻለቃ እስከ ክፍለ ጦር ደረጃ ድረስ አመራር የሚሰጡ ነባር መኮንኖች ተሀድሶና እውቀት ማዳበሪያ ትምህርት ለመስጠት ያለመቻላችን ነበር።

ይሄ ሁሉ ጥረት ተደርጎ የሶቭየት ሕብረት መንግሥት ካቀረበልን ታንኮችና ልዩ ልዩ ከባድ መሣሪያዎች በሙሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሠራዊታችን ማስታጠቅ ባለመቻላችን ሶቭየት አመራር ጓዶች ከፊሉን መሣሪያዎቻችን የሚያንቀሳቅሱልን ጦር ከኩባ መንግሥት እንዲጠይቅ አማክረውን የኩባን አመራር ስንጠይቅ ፍፁም ፈቃደኞች ሆነው ስለተገኙ ኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት በመልሶ ማጥቃት ...



እንዲያስወጣ በታቀደው ፕሮግራምና የጊዜ ገደብ ለውጊያ ዝግጁ መሆን ተቻለ። በኛ በኩል ምስጢራችንን ለማንም ሳንገልፅ የመልሶ ማጥቃቱ ውጊያ እንዲጀመር ያቀድነው በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ 1970 ዓ.ም ነበር።

## ምዕራፍ ሠላሳ ስምንት

# ወራሪው የሶማሊያ መንግሥት የጦር ኃይል ሐረርጌን ለመያዝ ያደረገው የመጨረሻ ጥረት

ከሰኔ ወር መጀመሪያ 1969 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት ወረራ የጀመረው የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት እስከ ህዳር ወር 1970 ዓ.ም ድረስ ለስድስት ወራት ባደረገው በየአቅጣጫው የተደጋገመ የማጥቃት ሙከራና በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ፅኑ የመከላከል ተጋድሎ እያሌ ወታደሮች በመስዋታቸውና በመቁሰላቸው በርካታ ታንኮቹና የተለያዩ መሣሪያዎቹ በመውደማቸውና በመማረካቸው የአየር ኃይሉ ፍፁም ከጥቅም ውጭ ከመሆኑ በላይ የኛ አየር ኃይል ከሶማሊያ መንግሥት ግዛት የአየር ክልል ውስጥ እየገባ ባደረገው ድብደባ ጠላት ለማጥቃት የሚያደርገው ጥረት እብቅቷል የሚል የተሳሳተ ግምት ነበረን።

ጠላት የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት በአጭር ጊዜ ውስጥ ያደረገውን የኃይል ግምባታና የሶቭየት ሕብረት መንግሥት የሰጠውን የመሣሪያ ርዳታ ያለማወቅ ይሁን ወይም አውቆ የኛን የመልሶ ማጥቃት መሰናዶ በመረዳት ሳይቀደም የእኛን መሰናዶ ለማሰናከል ብሎ ያደረገው ይሁን በውል ባልተረዳነው ሁኔታና ባልጠበቅነው ጊዜ በህዳር ወር መጀመሪያ በ1970 ዓ.ም በደቡብና በምሥራቅ የጦር ግምባሮች ብቻ ሳይሆን በሰሜን ከሚወጉን ገንጣዮች ጋር የተቀናጀ ማጥቃት ጀመረ።

ከሰሜኖቹ ከሃዲ የሃገር ጠላቶች ጋር በቅንጅት በሁሉም የጦር ግምባሮች ማጥቃት የጀመረው በሁሉም ግምባሮች በእርግጠኝነት እጨብጠዋለሁ የሚለው ወታደራዊ ግብ የሮት ሳይሆን ሐረርጌን ብቻ ለመቆጣጠር ያቀድነው እቅድ ለመሸፈን የወገንን ኃይል ለመበታተንና ለዘመቻው አመራር ያለንን ትኩረት ለማዛባት ብሎ ያደረገው እንደሆነ በኛ በኩል የታወቀ ነበር።

የሚገርመውና የሶማሊያን መንግሥት ወራሪ ሠራዊትና የሰሜኖቹን ሃገር ገንጣዮች ውጊያ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም በአንድ የዘመቻ መምሪያ ክፍል ውስጥ እያስተባበረ ነው ብለን እንድናምን ያስገደደን ሁኔታ በዚህ ጊዜ ውስጥ ጅብሃና ሻዕቢያ ለሁለተኛ ጊዜ አሥመራን ለመያዝ ያደረጉት ከዚያ በፊት ያልታዩና ያላቋረጠ ከፍተኛ የማጥቃት ጥረት ነው።

የዚህ ተቃራኒ መልካሙ ነገር ጠቅላላው የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት በዚህ ወቅት ያለው ኃይሉ ብዛትና በታጠቀው የመሣሪያ ጥራት እጅግ የጎለበት ብቻ ሳይሆን በሞራሉም የዳበረና የማጥቃት ስሜት የተላበሰ ስለነበረ በሁሉም ግምባሮች የተቃጡበትን ጥቃቶች አክሽፈ ለመመለስ የተዘጋጀ መሆኑ ነው።

ጠላት የማጥቃት ችሎታውን የጨረሰ በመምሰል በመከላከያ ምሽጉ ውስጥ ለብዙ ወራት አድፍጦ ከከረመ በኋላ ባላሰብነውና ባልጠበቅነው ጊዜ ሐረርጌን ለመያዝ የነበረው እቅድና አፈፃፀም ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራር ሠራዊት በኢትዮጵያ ላይ የመስፋፋት ጥቃቱን ሲጀምር የጥቃቱ ዒላማ ያደረጋቸው ክልሎች ከአጠቃላይ የክልሎቹ አካል የሆኑትን የጠረፍ አውራጃዎች በተለይም የተጠቀመበትን ወታደራዊ ስልት ለአንባብያን በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በሥዕላዊ መግለጫም ማሳየቴ ይታወሳል።

በመጨረሻም ሐረርጌን ለመያዝ ለሚደረገው ዘመቻ ስኬታማነት በማዕከላዊና በደቡባዊ የኦጋዴን ክልሎች ላይ ያሰማራውን በሁለት እዞች ማለትም በባይዶዋና በገልካዩ እዞች ስር የነበሩትን ጦሮች በሙሉ አጠቃሎና በተጨማሪም ውጊያ ውስጥ ያልገባ አዲስ ኃይል ከመሃል ሶማሊያ አምጥቶ በማጠናከር ጅጅጋና ደገሀቡር ላይ ካከበተ በኋላ በአምስት ግብረኃይል ከፈለው።

አንደኛውን መጠነ ሰፊ ኃይል በመከፋፈል በሦስት ግብረኃይል አደራጅቶ ሦስቱንም ግብረኃይሎች በአንድ ላይ በጅጅጋ በስተምዕራብ በጭናክሰንና በጉርሱም አድርጎ በመንቀሳቀስ ኤጀርሳጎሮን ከተቆጣጠረ በኋላ ከኤጀርሳ ጎሮ እየተንደረደረ፣ በአንደኛው ግብረኃይል ኮምቦልቻን፣ በሁለተኛው ግብረኃይል ሐረርንና ድሬደዋን በመቁረጥ ዓለማያን ከያዘ በኋላ በመጨረሻውና በሦስተኛው ግብረኃይል ትልቁን የጀልዴሳን ግብረኃይል ከማጠናከር በላይ በዚሁ ግብረኃይል ከፊል ኃይል መሀል አገሩን ከድሬደዋ በመቁረጥ ሐረርን ያዘ።

በሌላ አነጋገር የድሬዳዋን ከተማ ከሐረርና ከመሃል ሃገር ቆርጦ በሦስት አቅጣጫ ሲከፍል የሐረርን ከተማ ቆሬን፣ ባቢሌን፣ ሐኪምጋራን፣ ፊዲስን፣ ዓለምማያን፣ ኮምቦልቻንና አቦከሪን በመያዝ ከሰባት አቅጣጫ ከበበን ማለትነው።

እዚህ ላይ የሐረርን ከተማ እጅግ ከፉ አደጋ ላይ የጣለው በሰባት አቅጣጫ መከበብ ብቻ አይደለም። ሁኔታውን ይበልጥ አደገኛ ያደረገው ከእነዚህ ጠላት ከተቆጣጠራቸው ስፍራዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ከሐረር ከተማ እምብርት የሚርቁት እስከ 15 ኪ/ሜትር መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሐኪምጋራንና አቦከር የሚባሉት ስፍራዎች ከተማውን የሚገዙ ከፍተኛ መሬቶች መሆናቸው ነው።

በአጭር ጊዜ ውስጥና ለኛ ባልተከሰተ ሁኔታ ጠላት ሐረርን ለመከበብ የቻለው የሐረርንና የአካባቢው ነዋሪ የሆኑ የእስልምና እምነት ተከታይ ኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ራሱን "ኦሮሞ እስላማዊ" ብሎ የሚጠራው የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ምንደኛ የሆነ ድርጅት መሪነትና አስተባባሪነት ለወራሪው ሠራዊት ወግነው ለወገን ምንም ዓይነት መረጃ ለመስጠት አለመፈለግ ብቻ ሳይሆን የወረራውም ተካፋይ በመሆናቸው ነው።

ጠላት ከተቆጣጠራቸው ስልታዊና ስትራቴጂያዊ ከሆኑ ቁልፍ መሬቶች አንዱ የሆነው ሐኪምጋራ የሚባለው ገገር መሬት የሐረር ከተማ አካል ከከተማው በስተምሥራቅ የሚገኘው የአንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት መምሪያ ጽሕፈት ቤት የሚገኝበት ነው።

እንዲሁም የከተማው አካልና ከከተማው በስተሰሜን ምዕራብ የሚገኘው አቦከር የሚባለውና ከተማውን የሚገዛው ሌላው ከፍተኛ መሬት ግርጌ የሚገኘው ቀላድአምባ በመባል የሚጠራው የከተማው ትልቁ አካልና የሐረር ከተማ ነዋሪ አብዛኛው ሕዝብ የሚኖርበት ችምችም ያለ ከተማ ነው።



የጠላት ሰላዮችና የፊት ተመልካች መድፍ አስተኳሾች ከእነኝህ ከዚህ በላይ በገለፅኳቸው የከተማው አካልና የከተማው ገገር በሆኑ መሬቶች ላይ ሆነው በከተማው ውስጥ የሚደረጉ ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች ለመመልከትና ለማስመታት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ደርሰው ነበር።

የደቡብንና የሰሜኑን የጦር ግምባሮች ሁኔታ ለጊዜው ወደ ጎን ትተን የጠላት ዋና ዒላማ የሆነውን ሐረርጌን ብቻ ብንመለከት በአንድ ጊዜ፣ በድሬዳዋ አካባቢ በኤረርና በጀልዴሳ ግምባር፣ በሐረርና አካባቢዋ፣ በዓለምማያና በደንገጎ፣ በአቦከርና በኮምቦልቻ፣ በፊደስና በሐኪምጋራ፣ በባቢሌና በቆሬ በጠቅላላ በዘጠኝ ግምባር እንዋጋ ነበር።

የሐረር ከተማ በመድፍና በሮኬት ትደበደብ ስለነበረ ለከተማው ነዋሪ ሕዝብ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከመከላከል ውጊያ ወደ ማጥቃት ለመሸጋገር የተዘጋጀ ስለሆነ ሁሉም ሠራዊቱ በያዘው የመከላከያ ምሽግ ውስጥ እየገባና በየደጃፉ ምሽግ እየቆፈረ ጠላቱን በቆራጥነት እንዲከላከልና ቁስለኛ እያገለለ እንዲንከባከብ፣ የተቻለውን ለተዋጊው ምግብና ውሃ እንዲያቀርብ ወዘተ ማስተባበሪያ ትዕዛዝና መመሪያ ይሰጥ የነበረው አዲስ አበባ ከሚገኘው ብሔራዊ አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ማዕከል በሃገር አቀፍ ሬዲዮ ነበር።

ይህንን በመሰለ እጅግ ፈታኝና ቀውጢ በሆነ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እያለን በሁኔታው የተሸበሩ ወዳጆቻችን አንድ ያልተጠበቀ አደገኛ ሁኔታ ፈጠሩ ።በምሥራቅ የጦር ግምባር ተሰማርተው ሐረር ከተማ ውስጥ ባሉ አራት ሆስፒታሎች በህክምና ሙያቸው ሠራዊቱን ሲረዱልን የነበሩ የሶቭየት ሕብረትና የኩባ ዶክተሮች እንዲሁም ነርሶች የሠራዊቱን አመራር አካላት ሳያማክሩና ወይም ሳይገልፁ ቁስለኛውን ትተው ወደ አዲስ አበባ ሊመጡ መነሳታቸው ከአንደኛ አብዮታዊ ሠራዊት እዝ ተነገረኝ።

ፍልሚያው ተጧጡፎ በነበረበት ጊዜ ቁስለኞችን ሆስፒታል ውስጥ ጥለው ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት የወሰኑት ውሳኔ አደገኝነቱ ቁስለኞቻችን ሕክምና ማጣታቸው ብቻ ሳይሆን ምን ተስፋ አስቆራጭ ነገር ቢፈጠር ነው በማለት መላው የከተማው ነዋሪ ሕዝብ በመደናገጥ ቤቱን ጠቅለሎ ቢሸሽ ወይንም ቢሰደድ ሠራዊቱንም የሚፈታ ወይንም የሚበትን አደጋ ይፈጠርና ወራሪው ሠራዊት ያለውጊያ የሐረርን ከተማ የሚረከብበት ድል በሰሀን የመስጠት ያህል እጅግ አደገኛና አፍራሽ እርእያንቱ ነው።

አዲስ አበባ በሚገኘው ብሔራዊና አብዮታዊ የዘመቻ መምሪያ ውስጥ ያለነው ጓዶች በእጅጉ አገዘንና ተበሳጭተንም ስለነበረ የሁለቱን አገራት ማለትም፣ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙትን የሶቭየት ሕብረትና የኩባን አምባሳደሮች ከነወታደራዊ አታሼዎቻቸው ጠራሁ። ሳታማክሩን ወይንም በቅድሚያ ሳታስታውቁን በምሥራቅ የጦር ግምባር ያለውን ሠራዊት በሕክምና ሞያቸው ሲያገለግሉ የነበሩ የሕክምና እርዳታ የሚሰጡ ባለሞያዎች በሙሉ ቁስለኛውን ጥለው መሸሽ በሕክምና ሥነ-ምግባር የማይገባና ቁስለኞቻችን የሕክምና ርዳታ የሚያጡ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን እኛ ያላወቅነውና እነሱ ያወቁት ምን አደጋ መጣ ብሎ የከተማውም ሕዝብ እንዲሸሽና ብሎም ተዋጊው ሠራዊት እንዲበተን በማድረግ ወራሪው ሠራዊት ያለውጊያ ሐረርን እንዲረከብ የሚያደርግ እጅግ አፍራሽና አስፈሪ ተግባር ስለሆነ የመሐል አገሩን የሕክምና አገልግሎት አቁመን በየሆስፒታሉ ያሉትን ኢትዮጵያዊ ሐኪሞችና ነርሶች ከመላካችን በፊት ከሥራቸው እንዳይንቀሳቀሱ ማዘዜን አሳወቅኋቸው። የኛ የሕክምና ባለሞያዎች ሐረር ከደረሱ በኋላ የእናንተ ሐኪሞችና ነርሶች ወዘተ ወደ አዲስ አበባ ከመምጣት ይልቅ ከድሬዳዋ አውሮፕላን ማረፊያ ወደየአገራቸው ነው መሔድ ያለባቸው።

ምክንያቱም ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሐኪም የሚያከብራቸው ካለመሆኑ ሌላ እናንተም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ በአፍላና በሥርነቀል ሕዝባዊ አብዮት ውስጥ ያለች ሃገር እንደመሆኗ መጠን የአዲስ አበባ ከተማም ሆነ የተቀሩት የአገሪቱ ክልሎችና ከተሞች ሁሉ የትግልና የውጊያ ሜዳ ወይንም መድረክ ስለሆኑ ለሕክምና ባለሞያዎቻችሁ ዘላቂ ደህንነት የሚበጀው ይሔው መሆኑን ልነግራችሁ ነው የጠራኋችሁ በማለት አሰናበትኳቸው።

የሁለቱም አገራት አምባሳደሮችና ወታደራዊ አታሼዎች በየበኩላቸው በየመንግሥታቸው አመራር አካላት በኢትዮጵያ የተፈጠረውን ሁኔታ አስረድተው የሕክምና ባለሞያዎች ከድሬዳዋ ወደየአገራቸው ይመለሱ እንጅ  አዲስ አበባ አትቀበላቸውም ብሏል የሚል መልዕክት በማስተላለፋቸው በሞስኮና በሐቫና ሌላ ያልተጠበቀ ትልቅና አስደንጋጭ የፖለቲካ አቧራ አስነሳ።

በኔ በኩል የሁለቱን አገራት አምባሳደሮችን ወታደራዊ አታሼዎችን ካሰናበትኩ በኋላ በወቅቱ የጤናጥበቃ ሚኒስትራችን የነበረውን ጓድ ዶክተር ተፈራ ወንዴን ጠርቼ በአዲስ አበባ ሆስፒታሎች ውስጥ የሚያገለግሉ ኢትዮጵያዊያን ሐኪሞችና ነርሶች በሙሉ ከአሁን ጀምሮ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአየር መጓጓዣ ወደ ሐረር እንዲላኩ የሰጠሁትን ትእዛዝ ያስፈፀመበት ሁኔታና የኢትዮጵያዊያኑ የሕክምና ባለሞያዎች ፍፁም ፈቃደኝነትና ትብብር እጅግ የሚያስደንቅ ነበር።

አዲስ አበባ፣ ሞስኮና ሐቫና ያሉት ሩሲያዊያንና ኩባዊያን ተማክረው የሐረር ከተማ በማንኛውም ሰዓት በጠላት እጅ የሚወድቅ ስለሆን በአስቸኳይ ከሐረር ውጡ ብለው የሕክምና ባለሞያዎችን ያዘዙት ሰዎች ውሳኔያቸውን ሽረው አዲስ አበባ ላሉ ኢምባሲዎቻቸው "ሐረር የሚገኙት የህክምና ባለሞያዎቹ እሥራቸው ላይ ሆነው ማናቸውንም መስዋዕትነት ከኢትዮጵያዊያኑ ጋር እንዲከፍሉ ይሁን" ብለው ሁለቱም አገሮች በአንድ ቋንቋ የላኩላቸውን መልዕክቶች ከተለዩኝ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አምጥተው ሰጡኝና ወደ ሐረር የተላኩት የኢትዮጵያዊያን ሐኪሞችና ነርሶች በሔዱበት አውሮፕላን ወደ አዲስአበባ ተመለሱ።

በወቅቱ አዲስ አበባ የነበሩት የሶቭየት ሕብረት የምድር ጦር ምክትል አዛዥ ሌ/ጄነራል ፔትሾና የኩባ የመከላከያ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር ሜ/ጄነራል እቻዎ እንዳነጋግራቸው ስለጠየቁኝ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ጽሕፈት ቤት ተቀበልኳቸው።

በሶቭየት ሕብረት የሳተላይት መረጃ አማካኝነት እንደተረዱት የሐረርና የድሬዳዋ ከተማዎች በወራሪው የሶማሊያ ሠራዊት በብዙ አቅጣጫ ከ10 እስከ 20 ኪ/ሜትር ርቀት ተስፋ በሌለው ሁኔታ መከበባቸውን ካስረዱኝ በኋላ ሊያገኙኝ የፈለጉት ይህንን መረጃ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ስለህክምና ባለሞያዎቹ የሰጠሁትን ውሳኔ አስመልክተው ፈሪና ፈርጣጮች ብለህ ስለሰደብከን አዝነናል በማለት ቅሬታቸውን ገለጹልኝ።

እነሱ ስለአነሷቸው ጉዳዮች መልስና አስተያየት ከመስጠቴ በፊት በኢትዮጵያ ወቅቱ ክረምት በመሆኑ ታላቁ የምኒልክ ቤተመንግሥት በከፍተኛ ቦታ ላይ የተሠራ ግቢው በዛፎችና በተለያዩ እፅዋቶች የተሞላ በመሆኑ በበጋው ወቅት በጣም ነፋሻ ሲሆን በክረምቱ ወቅት በጣም ስለሚቀዘቅዝ በርዷችኋል ብዬ ከቤቴ ሻይና ኮኛክ እንዲመጣ አዝዤ ሻይ በኮኛክ ጋብዣቸው ሁላችንም እየጠጣን እነሱም በሳተላይት መረጃ እንደተረዱት የሐረርና የድሬዳዋ ከተሞች መከበባቸው እውነት መሆኑን አምኜ ይህንን ሁኔታ በሚቀጥለው 24 ሰዓት ውስጥ ፍፁም እንደምንለውጠው ቃል በመግባት ስጋት እንዳይሰማቸው ነገርኳቸው።





ከኦጋዴን የሞቃዲሾን ወራሪዎች እየደመሰሰ የጠረገውን አብዮታዊ ጦር ስጎበኝ

ንግግሬን በመቀጠል ተሰድበናል በማለት ወደእነሱት ስሞታ አምርቼ ከሁሉ በፊት በተፈጠረው ታላቅ ስህተት እንተማመን። እናንተን ቅር ያሰኛችሁ ምናልባት ለራሳችሁ ያላችሁ ግምትና የልብ ኩራት ጉዳይ ሲሆን በታዘዙት መሠረት ሐኪሞቹ ቁስለኞቻቸውን ጥለው ቢመጡ ኖሮ ያለትግል ያለውጊያ አገሬን ለጠላቴ ማስረከብ ነበር፤ ማለቴ ነው ብላችሁ በመተረጎም ካልሆነ በስተቀር ፈሪና ፈርጣጭ የተባሉ ቃላቶች ከኔ እንደበት ሊወጡ አይችሉም። ደግሞስ እናንተን የመሰለ በብዙ የጦር ሜዳ የተፈተናችሁና ታላላቅ ጀብዱ የፈፀማችው ጀግኖችን እንዴት ፈሪና ፈርጣጭ ማለት እችላለሁ? በማለት አግባብቼና አረጋግቼ፤ ከኮኛክም ደጋግመው በቀልድና በሳቅ ተለያየን።

## ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

# የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ከመከላከል ወደ ማጥቃት መሸጋገር

ለመልሶ ማጥቃቱ መሰናዶ በወጣው ፕሮግራም መሠረት የውጊያ ዝግጅታችንን አጠናቅቀን በሚያስመካ ሁኔታ ሠራዊታችን መልሶ ለማጥቃት የሚችለው በየካቲት ወር መጨረሻ 1970 ዓ.ም ነበር።

የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት እጅግ አደገኛ በሆነ ሁኔታ የመጨረሻ ማጥቃት ሰንዝሮ የሐረርንና የድሬዳዋን ከተሞች ከ5 እስከ 15 ኪ/ሜትር በሆነ ርቀት ከብዙ አቅጣጫ መክበብ ብቻ ሳይሆን ሐኪምጋራና አቦከር የምንላቸውን የሐረር ከተማ አካል የሆኑ ወሳኝ ከፍ መሬቶችን ተቆጣጥሮ እግረኛውን ሠራዊት ወደከተማው ለጨበጣ ውጊያ ለማስገባት ከተማውን በመድፍና በሮኬት መደብደብ ስለጀመረ ለመልሶ ማጥቃት የምናደርገውን መሰናዶ አቋርጠን ከህዳር 15 ቀን 1970 ዓ.ም ጀምሮ ወደ መልሶ ማጥቃት እንድንሸጋገር ሁኔታው አስገደደን።

ወደ መልሶ ማጥቃቱ ታሪክ ከመግባቴ በፊት ወራሪው የሶማሊያ መንግሥት ሳይቀድሙኝ ልቅደም ብሎ መላ የጦር ኃይሉን በማሰባሰብ ሐረርን ለመያዝ በህዳር ወር መጀመሪያ ማጥቃት ባይሠነዝርና የኛ የመልሶ ማጥቃት መሠናዶ ቢጠናቀቅ ኖሮ የማጥቃት ውጊያ ዕቅዳችን ምን ይመስል እንደነበረ ለአንባቢ ማስረዳት አስፈላጊ ይመስለኛል።

ተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት አንድ አምስተኛው የኢትዮጵያ መንግሥት የአስተዳደር ክልል አለኝታዬ ነው ቢልም በብዙ ምክንያቶች በጠቅላላው የጦርኃይሉ ከብዛት መቶ በላይ በማሠማራት የወረራ ዋና አላማው ያደረገው ሐረርን በመሆኑ የኛ ጠቅላላ የውጊያ ስትራቴጂ በሰሜን መከላከልና በምሥራቅ ማጥቃት ቢሆንም የኃይል ክምችት፣ ስምሪትና አቢይ የውጊያ ትኩረታችን ሐረርጌ ነበር።

በዚህ የኃይል አሠላለፍ አንጻር የውጊያ ስትራቴጂያችንም በሐረርጌ ደጋማ ሥራጃዎችና በድሬዳዋ ከተማ አካባቢ የተሰባሰበውን ጠላት ከኋላው በመዞር መቁረጥና ከዚም በአፈና ውጊያ መላውን የጠላት ሠራዊት ከነመሣሪያው ወደአገሩ ሳይመለስ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ለማስቀረት ነበር።

ይህንን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የነደፍነው ሥልት:

1ኛ/ ሦስት ብርጌድ ፓራኮማንዶዎችን በጃንጥላ ወይንም በሄሊኮፕተር ከጠላት ጀርባ ጅጅጋ ላይ በማውረድ የጠላት ማፈግፈጊያ የሆነውን ማርዳፓስንና የጭናክስን በር ማዘጋት፤

2ኛ/ በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት ብርጌድ ታንክ፣ ከአንድ ብርጌድ ከባድ መድፍና ሮኬት የተቃመረ መጠን ሰፊ ሜካናይዝድ ሠራዊት ከአሠብ ተንሥቶ ወደ መሃል ሃገር ሳያመራና በማንም ሳይታይ፣ በኢትዮጵያ በጅቡቲ ሪፐብሊክ ጠረፍ፣ በአውሳ፣ በኢሳና ጉርጉራ የድሬዳዋንና የሐረርን ከተማ ወደቀኝ በመተው በጎግቲና በተፈሪ በር በኩል ወደ ጅጅጋ በመታጠፍ ከሦስቱ ፓራኮማንዶ ብርጌዶች ጋር በአንድ እዝ በተቀናጀ ውጊያ ቆሬ ያለውን ዋናውን የሶማሊያ ጦርና እንዲሁም ጉርሱምና ኤጀርሳጎሮ፣ ኮምቦልቻና ሐረር ከተማ የገቡትን ከሁለት አቅጣጫ ማለትም ከጅጅጋ ከቆሬ በአፈና ጥቃት መደምሰስ፣



3ኛ/ በሁለት የታንክ ብርጌድና በአንድ የመድፍ ብርጌድ የተቃመረ ሌላ ወይንም ሁለተኛ ሜካናይዝድ ግብረኃይል ጅጅጋ ከደረሰ በኋላ በስድስት ሰዓት ልዩነት ውስጥ የቆሬውና የጀልዴሳው የጠላት ጦሮች ሳይነቁ ከአሰብ ተነስቶ በአውሳ በኩል በመንደርደር ኢሳና ጉርጉራ ወደ ቀኝ ታጥፎ ከአየር ኃይል ጋር በተቀናጀ ድንገተኛ ውጊያ ከጀርባ ገብቶ ጀልዴሳ ያለውን የጠላት ሜካናይዝድ ጦር ከደመሰሰ በኋላ ወደ ጅጅጋ በመሄድ ጅጅጋ ያለውን የወገን ሜካናይዝድና የፓራኮማንዶ ቅምር ጦር ማጠናከር።

4ኛ/ ጅጅጋ ተይዞ የማርዳፓስና የጭናክስን በሮች ከተዘጉና ሁለተኛው ከባዱ ጀልዴሳ ያለው የጠላት ጦር ከተደመሰሰ በኋላ በሐኪምጋራና በፌዲስ፣ በአቦከርና በኮምቦልቻ ማለትም በሁለት ግምባር የሚዋጋውን ሕዝባዊ ሠራዊትና የአባት ጦሮች በአዲስ ሁለት መደበኛ እግረኛ ክፍለጦሮች፣ በመድፍና በአየር ድጋፍ አጠናክሮ በአንድ ጊዜና በተመሳሳይ ሰዓት ሐኪምጋራን፣ ፌዲስን፣ አቦከር፣ ኮምቦልቻን፣ ባቢሌንና ቆሬን ማጥቃት፣

5ኛ/ አቦከረንና ኮምቦልቻን ያጠቃው የወገን ጦር ከአየርኃይል ጋር በተቀናጀው ውጊያ ከኮምቦልቻ ተነስቶ ጀልዴሳ ያለውን ጦር ደምስሶ ወደ ጅጅጋ ለሚያመራው ሁለተኛ ሜካናይዝድ ግብረኃይል የቀኝ ክንፍ በመሆን ተንቀሳቅሶ ኤጀርሳጎሮና ጉርሱም ላይ ያለውን የጠላት ጦር በመደምሰስ ተራምዶ የጅጅጋውን አፋኝ የወገን ጦር አጠናክሮ በቆሬ ያለውን የጠላት ጦር ከጀርባ በመደምሰስ ለሚደረገው የአፈና ውጊያ ድጋፍ መስጠት፣

6ኛ/ ሐኪምጋራና ፌዲስ ላይ ያለውን የጠላት ጦር የደመሰሰው የወገን ጦር ባቢሌ ያለውን የጠላት ጦር ከደመሰሰው የወገን ጦር ጋር ተቀናጅቶ ጠላትን እያሳደደና እየቃመረ ወደ ደገሀቡር በመሄድ መልሶ መቋቋም አድርጎ ለሚቀጥለው ግዳጅ የበላይ አካልን ትዕዛዝ መጠበቅ። የጅጅጋው ቅምር የወገን ጦርም የተሰጠው የጠላትን ማፈግፈግያ መንገድ



መዝጋትና ብሎም ከጀርባ በአፈና ውጊያ ጠላትን የመደምሰስ ተግባሩን ከፈፀመ በኋላ መልሶ መቋቋም አድርጎ ለሚቀጥለው ግዳጅ የበላይ አካል ትዕዛዝ መጠበቅ።

7ኛ/ በተመሳሳይ ጊዜ በሁለተኛው ዙር ከሰለጠነው ሕዝባዊ ሠራዊቱ በተቀነሱ ሁለት ክፍለ ጦሮች በቦረናና በባሌ ሲከላከል የነበረውን የወገን ጦር አጠናክሮ ከአየር ኃይል ጋር በተቀናጀ ውጊያ ማጥቃት ነበር።

ቀደም ብሎ ማለትም ከሰኔ ወር 1969 ዓ.ም ጀምሮ አገሩንና አብዮቱን ለማዳን በግምባር በመከላከል ውጊያ ከተሠለፈው ጦር ሌላ የመልሶ ማጥቃቱን ውጊያ ስኬታማ ለማድረግ ከጦር ግንባሮቹ ኋላ በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎችና የጦር ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ በመሰልጠንና በመደራጀት ላይ የነበሩት የጦር ክፍሎች ከዚህ የሚከተሉት ነበሩ።

በጀንጥላ ወይንም በሄሊኮፕተር ጅጅጋ ላይ ወርደው ለጠላት ማፈግፈጊያ የሚሆኑትን የማርዳፓስና የጭናክስን በሮች የሚዘጉት ሦስት ፓራኮማንዶ ብርጌዶች ለማቋቋም በሁለተኛው ዙር ሕዝባዊ ሠራዊት ውስጥ ከ18 እስከ 25 ዓመት እድሜ ያላቸው፣ ፍፁም ጤናማና ከድህረ መሠረት ትምህርት ጀምሮና ከዚያ በላይ የቀለም ትምህርት ያላቸውን ወጣቶች፣

1ኛ/ ሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ ኃብተማርያም በኋላ ብ/ጄነራልና የህብረተሰባዊ ኢትዮጵያ ጀግና፣

2ኛ/ ሻለቃ ሽባባው ዘለቀ የላቀ ጀግና ግን በማዕረግ ሳያድግ በሰሜን ውጊያ የተሰዋ፣

3ኛ/ ሻለቃ ሽፈራው ወርቁ እያንዳንዳቸው ለሚመሯቸው ፓራኮማንዶ ብርጌዶች በጋራ መልምለው ከነሐሴ ወር 1969 ዓ.ም ጀምሮ በሌ/ኮሎኔል ተስፋዬ የሚመራው ብርጌድ በሲዳሞ ክፍለሃገር በአዋሳ ሐይቅ አካባቢ፣ በሻለቃ ሽባባው የሚመራው ብርጌድ በሸዋ ክፍለ ሃገር በአዋሽ አርባ አካባቢና በሻለቃ ሽፈራው የሚመራው እንዲሁ በሸዋ ክፍለሃገር በለገዳዲ አካባቢ የኮማንዶ ሥልጠና ጀምረው ነበር።

ለመልሶ ማጥቃቱ ዋና ኃይል ወይንም የጀርባ አጥንት ይሆናሉ ብለን ያመንባቸው የታንክ ብርጌዶች የታንክ ማጓጓዣ እጦት በፈጠረው ችግር ምክንያት ሠራዊቱ እንዲሰለጥን እንዲደራጅ የተደረገው በአሰብ ወደብ አካባቢ ስለነበር ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ጊዜ ለመቆጠብና በጠላት ላይ ድንገተኛነትን ለማግኘት ብቻ ሳይሆን ከሦስቱ ፓራኮማንዶ ብርጌዶች ጋር በተቀናጀ ውጊያ ጠላትን ጅጅጋ ላይ ለማፈን ያዘጋጀነው አራት የታንክ ብርጌዶችን፣ አራት የመድፍና የቢኤም 23 ሮኬት ብርጌዳችን ነበር።

ሁለት የታንክና የመድፍ ኢትዮጵያዊ ብርጌዶች ቀደም ብለው በቀረቡልን ታንኮች፣ መድፎችና ሮኬቶች ላይ ሲሠለጥኑ የተቀሩትን ሁለት ብርጌዶች ታንኮች፣ መድፎችና ሮኬቶችን የሚያንቀሳቅስልን የኩባ ጦር ከመምጣቱ በፊት ለመሰናዶ ቀድሞ በመጣው የጦሩ አዛዥ ሜ/ጄነራል ኦቾዋ እኛ ቀደም ብለን ያቀድነውን የመልሶ ማጥቃት ውጊያ ዕቅድ አማክሬው ጦሩ በመርከብ አሰብ በሚገባበት ጊዜ በዚያው በአሰብ አካባቢ በመሥፈር ትጥቁን ተረክቦ ከኢትዮጵያ ብርጌዶች ጋር የጦር ልምምድ ካደረጉ በኋላ አራቱም የታንክና የመድፍ ብርጌዶች በአውሳና በኢሳ በኩል በቀጥታ ወደ ጅጅጋ ይሄዱ ዘንድ ተስማምተን ነበር።

ሊቀመንበር መንግሥቱ የመልሶ ማጥቃቱን ፍልሚያ ዕቅድ ገለጠልኝ ብሎ የኛን ዕቅድ ለሶቭየት ጓዶች ሲያሥረዳቸው፣ "መንግሥቱ ይህንን ዕቅድ ያዘጋጀው ያለጥርጥር ሶማሊያን ለመውረር ስለሆነ መስማማት የለብንም" ይሉታል።

"ይህንን ባለማወቁና ባለመጠራጠሬ ዕቅዱን በማድነቅ ተስማምቼ በጠየቀኝ መሠረት የኩባም ጦር እዚያው አሰብ ሠፍሮ ከኢትዮጵያ ብርጌዶች ጋር በጋራ የውጊያ ልምምድ ለማድረግ ጭምር ስላቀድን ቃሌን ለማጠፍ እንዴት ይቻለኛል?" ብሎ ሲጠይቃቸው ከሶቭየት መላክ የነበረባቸውን የተለያዩ የጦር መሣሪያዎች፣ ጥይቶች ተሽከርካሪዎችና በጠቅላላው ለውጊያው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን አዲስ አበባ ሆኖ ያዝ የነበረው የሶቭየት ሕብረት የምድር ጦር ምክትል አዛዥ ሌ/ጄኔራል በኋላ ማርሻል ፔትሮቭ ግዴለም እኛም እናንተም በዚህ ምክንያት ከኢትዮጵያዊያኑ ጋር እንዳንጋጭ እኔ ዘዴ አለኝ ይልና ኩባዎቹ መታጠቅ የነበረባቸውን ታንኮችና የተለያዩ መሣሪያዎች በመርከብ አሰብ ላይ ከማውረድ ፋንታ በአውሮፕላን ቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ በማቅረብ አሰብ የሰፈረው የኩባ ጦር ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ በማድረግ የኛ ዕቅድ እንዳይሠራ ተደረገ።

ሁለቱም ይህንን ተንኮላቸውን የገለፁልኝ የመልሶ ማጥቃቱ ውጊያ በተሳካ ሁኔታ ተከናውኖ በኛ ድል አድራጊነት የምሥራቁ ውጊያ አክትሞ አማካሪዎቻችንን እንደሞያቸውና አገልግሎታቸው በኒሻን ሸልማት አስደስተን ወደ አገራቸው ሲመለሱ ባዘጋጀንላቸው ግብዣ ላይ ነው። ማርሻል ፔትሮቭ ሶማሊያን ትወራለህ ብለን ስለፈራንህ እንዲህ ያለ ሻጥር ሠርተናል። ዛሬ የምንነግርህ የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት ድል አድርገህ ያባረርክ ስለሆነ ሳትቀየመን ይቅርታ እንደምታደርግልን ስላመንን ነው ሲለኝ የኩባውም ጄኔራል አቻዎ ከጎኔ ተቀምጦ ነበር። "ጥርጣሬያቸው የተሳሳተ፣ ሻጥሩም የማይገባ ቢሆንም ሳትደብቁኝ በመናገራችሁ አመስግናችኋለሁ" የሚል መልስ ሰጥቼ ተለያየን።

ለመልሶ ማጥቃቱ እየሰለጠኑና እየተደራጁ ነበር በማለት ከዚህ በላይ ከገለፅኳቸው የጦር ክፍሎች በተጨማሪ ከሁለተኛው ሕዝባዊ ሠራዊት ሥልጠና ሌላ፣ በትግራይ ክፍለሃገር ከዊሃ የጦር ሠፈር፣ በጎንደር ክፍለ ሃገር በአዘዞ የጦር ሠፍር፣ በሸዋ ክፍለሃገር በደብረ ዘይት አካባቢ ለምለም እየተባለ በሚጠራው የጦር ሠፈርና በሲዳሞ ክፍለሃገር በአዋሳ ሐይቅ አካባቢ አራት መደበኛ እግረኛ ክፍለጦሮች በሥልጠና ላይ ይገኙ የነበረ ሲሆን ከዚህ በላይ ቀድም ብዬ በሌላ አጋጣሚ እንደገለፅኩት ተዋጊ የሰው ኃይል ዝግጅቱ የስሜኑንም የመልሶ ማጥቃት መሰናዶ ያካተተ ነበር።

ወደ ርዕሴ ወደ መልሶ ማጥቃቱ ልመለስና ወራሪውን ሠራዊት ከኢትዮጵያ ምድር በአጠቃላይ ከሐረርጌ ክፍለሃገር በተለይ ለጠላት በተሠወረ ሁኔታ በድንገት ከጀርባው በመዞር ቆርጠን በአፈና ውጊያ ከነመሣሪያው በኢትዮጵያ ምድር ለማስቀረት በየካቲት ወር 1970 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲሆን የታቀደው የመልሶ ማጥቃት ስትራቴጂና ሥልት ከዚህ በሚከተሉት ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። ይኸውም፡-

1ኛ/ የውጊያ መሰናዶችንን አጠናቅቀን ጥቃት ለመሠንዘር ያሰብነው ከየካቲት ወር መግባደጃ ጀምሮ ሲሆን ጠላት ቀድሞ በህዳር ወር ውስጥ ጠቅላላ የመጨረሻ አደገኛ ጥቃት በመሠንዘሩና መሰናዶውን አቋርጠን ማጥቃት ለመሠንዘር ተገደድን።

2ኛ/ በዚህም ምክንያት አሰብ በመሠልጠንና በመደራጀት ላይ የነበሩት የታንክና የመድፍ ብርጌዶች ውጊያውን መካፈል አልቻሉም፤

3ኛ/ ሦስቱ ፓራኮማንዶ ብርጌዶች ሥልጠና ስለአልተጠናቀቀ እንደ ፓራኮማንዶ ጦር ጅጅጋ ላይ ከጠላት ጀርባ ልናወርዳቸው ባለመቻላችን፣ ለሐኪምጋራ፣ ለፈዲስ፣ በአቦከርና ለኮምቦልቻ ውጊያ እንደተራ እግረኛ ጦር ነው የተጠቀምንባቸው።

4ኛ/ አራት የታንክ ብርጌዶችን ከአሰብ በቀጥታ በአዳልና ኢሳ በኩል ወደ ጅጅጋ ለመወሰድ የታቀደው ዕቅድ ከፍ ብየ በጠቀስኩት ምክንያት ተሠርዞ ሁለት የኩባ ታንክች





ከወራሪው ሶማሊያ የተማረኩ የጦር መሳሪያዎች

ብርጌድ ከኢትዮጵያ መደበኛና ሕዝባዊ እግረኛ ክፍለጦሮች ጋር ከአሰብ የታሰበውን ከድሬዳዋ በማስነሳት በቅድሚያ ጀልዴሳ ላይ ያለውን ሁለተኛውን የጠላት ከምችት በመደምሰስ በመጀመሪያው ዕቅድ መሠረት ወደ ጅጅጋ በመሔድ የአፈናውን ውጊያ ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞከር በድሬዳዋ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ እጅግ ከባድና ያላቋረጠ ዝናብ ከአንድ ሳምንት በላይ ዘንቦ የተሽከርካሪዎቹን ንቅናቄ ፍፁም በማወኩ በሰውርና በፍጥነት እንዲከናወን የታቀደው በጅጅጋ በኩል ከጠላት ጀርባ የመግባቱን ሥልት ጠላት ቀድሞ ስላወቀው የወገን ጦር ድንገተኝነትን ለማግኘት አልቻለም።

በእነኝህ አራት ምክንያቶችና በከፊል ተሳኩ በምንላቸው መልሶ ማጥቃቶች በሐረርጌ ክፍለሃገር ሐኪምጋራና አቦከር ላይ፤ ኮምቦልቻና ፈዲስ ላይ በድሬዳዋ ግምባር ጅልዴሳ ላይ፤ በባሌ ክፍለሃገር ጎባ ላይ፤ በሲዳሞ ክፍለ ሃገር ነገሌ ላይ በአብዮታዊ ሠራዊታችን በመጀመሪያው የመልሶ ማጥቃት ወራሪው ሠራዊት በሚገባ ስለተመታ የተቀረው ጦር በሙሉ ከያለበት አጥቂው የኛ ታንኮች ጦር ጂጅጋ ከመግባቱ በፊት ጓዙን ጠቅልሎ በመሸሹ ከባቢሌና ከቆሬ ግምባር ጀምሮ በሐረርጌ፣ ጅጅጋ፣ ደገሐቡር፣ አይሻ፣ ዋርዴር፣ ገላዲን፣ ቀብሪደሐር፣ ፊርፊር፣ ብሩኩር፣ ሙስተሂልና ጎዴን፣ በባሌ ክፍለሃገር ገናሌን፣ ወንዶዩን፣ ዋቢን፣ ኤልከሬን፣ ዶሎን፣ ከሲዳሞ ክፍለሃገር አሬሮንና ጠቅላላ ቦረናን ወዘተ መልሰን የተቆጣጠርነው ያለውጊያ ነው።

በመጨረሻ ለአንባቢ ሳልገልጽ የማላልፋቸውና ሊሰመርባቸው የሚገቡ የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ወራዳ ተግባሮች፡-

1ኛ/ ከሐበሻ ኢምፔሪያሊዝም ቅኝነት ነፃ ላወጣህ መጣሁ ያለውን ሶማሊኛ ተናጋሪና የኦጋዴን ክልል ነዋሪ ኢትዮጵያዊ ሕዝብ መካከል ቤቱን ከመፈንገልና ወንድን ከማዋረድ ጋር ብቸኛ ሀብትና መተዳደሪያ የሆኑ የቀንድ የዳልጋ ከብትና ግመሎች እያረደ ሲበላ ከርሞ ሲሸሽ ጠራርጎ ወደ አገሩ በመንዳት መላውን የኦጋዴን ሕዝብ ለአስቃቂ ድህነት መዳረጉ፤

2ኛ/ በጎዴ የሚገኘው በዓለም አቀፍ ደረጃ የተገነባ ታላቅና ዘመናዊ የአውሮፕላን ግዳ በትራክተር ማረሱና ታላቁን የዋቢ የብረት ድልድይ ማፈራረሱ፤



3ኛ/ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት በበላይ አካል ታዞ በስልታዊ ማፈግፈግ የኦጋዴንን ክልል ለቆ ከወጣ በኋላ በሕክምና አገልግሎት፣ በመምህርነት፣ በርዳታ አስተባባሪነት፣ በመንገድ ሥራ፣ በባንክ በተለያዩ የመንግሥት ሥራዎችና በንግድ የተሰማሩትን ሶማሊኛ ተናጋሪ ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን ወንድና ሴት፣ ከሁለቱም ፆታ የደከሙ አዛውንቶችና ሕፃናት በግዴታ አግዞ ወደ ሞቃዲሾ ወስዶ ለመንግሥት ሲያስረክብ፣ የሶማሊያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ከታች እስከ ላይ ኢትዮጵያዊያኑን ተከፋፍለው ከአስር ዓመታት በላይ በባርነት በግብርና በድንጋይና እንጨት ፈለጣ፣ በመንገድ ሠራተኝነትና በሕንፃ ግምባታ ኩሊነት፣ በአትክልተኛነትና በቤት አገልጋይነትና ያለክፍያ፣ ያለአልባሳት፣ እርቃናቸውን በርሃብ እየቆሉ ድል አድራጊው ሠራዊታችን ሐበሻን ለባርነት ሳከልን በማለት ይመፃደቁ የነበረ መሆኑን ነው።

ጦርነቱ ያደረሰው የጉዳት መዘርዘር፣

| | የሞተ | የቆሰለ | የተማረከ |
|---|---|---|---|
| ከሶማሊያ ወራሪ ሠራዊት | 15,900 | 26,000 | 1,785 |
| ከኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት | 18,200 | 29,100 | 7 |

ልዩ መግለጫ

1. ወራሪው የሶማሊያ ሠራዊት የኦጋዴንን ክልል በተቆጣጠረ ጊዜ ውጊያ በሌለበት በክልሉ ከተሞች በንግድ፣ በመምህርነት፣ በጤና አገልገሎት ወዘተ የተሰማሩ 4,000 ኢትዮጵያዊ ሰላማዊ ዜጎችን አግዘው በመውሰድ በመሃል ሶማሊያ ከ10 ዓመታት በላይ በባርነት ሲገለገሉባቸው ቆይተው የምርኮኛ ለውጥ በተደረገ ጊዜ 2,600 ብቻ ወደ አገራቸው ሲመለሱ የቀሩት በተለያዩ ምክንያቶች ሞተዋል።

2. ወራሪው የሐረርን ከተማ በከበበት ጊዜ አራት የሶቭየት ሕብረት ወንዶ ሐኪሞችና አንድ ኩባዊ የምድር ጦር ወጣት መኮንን ታፍነው ወደ ሞቃዲሾ ከተወሰዱ በኋላ የሶቭየት ሕብረት መንግሥት ዜጎች ሆነትን መንግሥታቸው ለኛ ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ ከሶማሊያ መንግሥት ጋር በመደራደር በጥቂት ወራት ውስጥ አስለቅቆ ሲወስድ የኩባው መኮንን የአእምሮ በሽተኛ ከሆነ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰው ያለውጊያ የተጋዙት ኢትዮጵያዊያንን በምርኮኛ ለውጥ ባስመለስንበት ጊዜ ነው።

# ክፍል ፲

## ማጠቃለያ

# ምዕራፍ አርባ

## ያሸነፈው አብዮት ነው!

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሰሜን አፍሪካ የእንግሊዝና የጀርመን ሜካናይዝድ ጦሮች ካደረጉት ውጊያ በስተቀር በአፍሪካ ያልታየ ዘመናዊ የሜካናይዝድ ጦሮች ውጊያ በሶማሊያና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የተደረገበትን ምክንያት ለምሥራቁ ግምባር ውጊያ ታሪክ መግቢያ አድርጌ ለመግለፅ ሞክሬያለሁ። የምሥራቁን ግምባር ውጊያ ታሪክ መደምደሚያ ማድረግ የሚገባ የሚመስለኝ ውጊያው በምን ምክንያት ተደረገ በማለት ሳይሆን ሶማሊያ እንዴት ኢትዮጵያን ልትደፍር ቻለች በሚል ነው።

በአፍሪካ ታሪክ ብቻ ሳይሆን በዓለም ታሪክ ጥንታዊ ከሚባሉት አገሮች አንዷና የጥንታዊው የሰው ልጅ ሥልጣኔ ተጋሪ የሆነችውን ሊደፍሯት የሞከሩ፣ በየጊዜው ኃይል የተሰማቸውን፣ እብሪት የወጠራቸውንና መስፋፋት፣ ዘረፋና ገፈፋ ያማራቸውን የቅኝ ግዛት ኃይሎች እያሳፈረች በመመለስ ከጥቁር ሕዝብ ብቻዋን የነፃነት ደሴት ሆና የኖረችውን ኢትዮጵያ አገራችንን ሶማሊያ እንዴት ልትደፍራትና ልትወራት በቃች?

ለዚህ ጥያቄ እያሌ ሰዎች የተለያዩ የየበኩላቸውን መልሶች እንደሚሰጡ እያጠያይቅም። ከሶቭየት ሕብረት መንግሥት ባገኘችው ሊጋስ የጦር መሣሪያ አቅርቦት የገነባችው የጦር ኃይል ስለአስመካት ለሰው ሕይወት በጣም ተስማሚ የሆነው ነፋሻው የኢትዮጵያ የአየር ንብረት፣ በአፍሪካ ወደር የሌለው የውሃ ሀብትና የለም መሬት ቅናትና ምኞት መሪዎቿን ስለአስከራቸው፣ ኢምፔሪያሊዝምና የአካባቢው ታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች በሶማሊያ እጅ አንድነቷን በማፍረስና አብዮቷን በመቀልበስ ሊበቀሏት፣ እኛም ከጎንሽ አለን በማለት ስለገፏፏት ነው’ የሚል መልስ የሚሰጡ ብዙዎች እንደሆኑ ይገመታል። ጠቅለል ባለሁኔታ የሶማሊያ መሪዎች ጭፍን ግብዝነት ብቻ ሳይሆን ኋላቀርነትና የንቃተ ህሊና ጉድለት ነው የሚሉም ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል። እነዚህ ግምቶችና አስተያየቶች እውነታነት ያላቸው ቢሆንም ከሶማሊያ ወገን ባሉ ሁኔታዎችና ምክንያቶች ለጥያቄው የተሟላ መልስ ተሰጠ ብሎ መደምደም የሚቻል አይመስለኝም። ኢትዮጵያዊያን አበው ሀሳባቸውን በነገር ምሳሌ ለመግለፅ ብለው የሚጠቀሙበት የቆየ ዘይቤ፣ “አሽካከሙን አይተው ጭብጦውን ቀሙት” ይላሉ።

ከዚህ በላይ የተለያዩ ሰዎች ግምትና አስተያየት ናቸው ብዬ የገለፅኳቸው ትክክልና አሳማኝ ምክንያቶች እንደተጠበቀ ሆነው የሶማሊያ መንግሥት በ1969 ዓ.ም ኢትዮጵያን ለመውረር ያስደፈረው ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል የሚያስችላት ትጥቅና በቂ መከላከያ ሠራዊት የላትም፣ ሕዝቧ አንድነት የሌለው እርስ በእርሱ የሚዋጋና የሚገዳደል፣ የሚመራበት ማህበራዊ ሥርዓት ኋላቀር አገሪቱን የሚመራው ገዥ መደብ በሰፊው ሕዝብ

የተጠሳና የተወገዘ ከመሆን አልፎ በሕዝብ አመፅ የኃይለሥላሴ ዘውዳዊ አገዛዝ ስለተገረሰሰ አገሪቱ አመራር አልባ ሆና ሕዝቡ በሥርዓተ አልበኝነት እየታመሰ ስለሆነ በኢትዮጵያ ላይ ለመስፋፋት ያለንን ምኞት ተግባራዊ ለማድረግ ከዚህ የተሻለ ጊዜ የለም ብለው እንደሆነ የወረሩን እነሱ እራሳቸው ይህንን ሳይክዱና ሳይሰውሩ በተለያዩ አጋጣሚዎችና ጊዜዎች የገለፁት ጉዳይ ነው።

የሶማሊያ መሪዎች ወረራውን ለመሰንዘር ያስደፈራቸው የጦር መሣሪያቸው ጥራት፣ የሠራዊታቸው ብዛትና ከሌሎችም ከጠቃቀስናቸው የተለያዩ ምክንያቶች ይልቅ በእነሱ የፖለቲካ አመለካከትና በወታደራዊ መረጃቸው መነፅር የታያቸው ተራ ሽብርና ሥርዓት አልበኝነት ነው ብለው የገመቱት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ነው።

ሶማሊያዎች የረሷቸው፣ ያላስተዋሏቸው፣ ያላመዛዘኗቸው ምናልባትም ያላወቋቸው የኢትዮጵያ ብርቱ ጎኖችን ነው። እነዚህም፡-

1ኛ/ ከታላላቆቹ ወይም ግምባር ቀደሞቹ ስህተቶቻቸው አንዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድክመቱ ወጥቶ ለማንሰራራትና ለረጅም ጊዜ ለመዋጋት የሚያስችለው የሰው ኃይልና የኢኮኖሚ አቅምና ሁኔታ ጋር ያመዛዘኑ አይመስልም።

2ኛ/ እነሱን ቀርቶ እጅግ ገናና እና ኃይለኛ የነበሩ የአካባቢውን ኃይሎችና የአውሮፓ ቅኝ ገገርዎችን የወረራ ሙከራ እየመከተ አሳፍሮ በመመለስ በታሪኩ ለዘለቄታው ተሸንፎ ክብርና ነፃነቱን ያላስገፈፈ ብቸኛ ጥቁር ሕዝብ ለመሆን ያስቻለውን የታሪክ፣ የመንፈስና የሥነ ልቦና አቋሙን ለማስተዋል አልሞከሩም።

3ኛ/ ከሁሉም በላይ የወቅቱን የሕዝብ አብዮት መንስዔ፣ ባህሪ፣ ዓላማ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያከናወኗቸው ሕዝባዊ ተግባሮችና የተቀዳጃቸው ድሎች የአብዮቱን ሕዝባዊነትና ሕዝባዊ መሰረቱን ፈጽሞ አላጤኑትም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ተከፋፍሎ የሚዋጋበት፣ ሕዝብ እርስ በእርሱ እየተገዛዘ የተዳከመበት፣ የአመራር አልባ ቀውስና ሥርዓተ አልበኝነት የሰፈነበት ሃገር አድርገው በመመልከት ከዚህ የተሻለ ጊዜ አናገኝም ብለው ማሰባቸው ከስህተቶቻቸው ሁሉ ከባዱ ነበር። ያሸነፋቸው እነሱ በትክክል ያልተረዱት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ነው።

እንዴ በጥቁር ባሕር ዳርቻ የምትገኘዋን ሴባስቶፖል የምትባለውን ታሪካዊ ከተማ በጎበኘሁበት ጊዜ በፋሽስት ጀርመንና በሶቭየት ሕብረት ቀዩ አብዮታዊ ሠራዊት መካከል ለረጅም ወራት የተደረገውን ከባድና መሪር ውጊያ የሚያሳየውን የአስደናቂ ሥዕላዊ የታሪክ መግለጫ ያስጎበኙኝ የታሪክ መዘክሩ ሥራ መሪ የሆኑ የ80 ዓመት አብዮታዊ አዛውንት ስለጦርነቱ ሲገልፁልኝ ጀርመኖች ከተሰማቸው እብሪትና ከተነሱበት የመስፋፋት ዓላማ ባሻገር የሶቭየት ሕብረትን ሁኔታ የገመቱት አሜሪካዊያን ከሚያሰራጩት ፀረ-አብዮት ፕሮፖጋንዳ አንፃር ብቻ ነበር። የአብዮቱ መንስኤ የአብዮቱን ዓላማ፣ አብዮቱ የተቀዳጀውን ሕዝባዊ ድሎችና ሕዝባዊ መሰረቱን አልተረዱም። ሕዝቡን ከእንቅልፍ የቀሰቀሰው፣ ያነቃው፣ ያደራጀውና ያንቀሳቀሰው አብዮት ነው። የጀርመን መንግሥት የተመካበትን ወራሪ ሠራዊትና የመሣሪያ ኢንዱስትሪ የደመሰሰው አብዮታችን ነው።

የሩሲያ ሕዝብ በአጠቃላይ ወዛደሩ፣ ገበሬው፣ አብዮታዊ ምሁሩና ወታደሩ ወዘተ ከዛሩ መንግሥትና ሥርዓት ጋር ዓይንና በርበሬ በነበሩበት ጊዜ ጀርመኖች ወርረውን ቢሆን ኖሮ ሩሲያ ናፖሊዮ በናፓርት ካደረሰባት ውርደትና እጅግ የከፋ ውድቀት በደረሰባት ነበር ሲሉ የሰጡን ገለፃ ሲታወሰኝ ይኖራል። የኛም አብዮት ፍፁም ሕዝብዊ ነበር። ሕዝቡን





ያሰባሰበ ነበር። ከዘውዱ መገርሰስ ከመሬት አዋጅ፣ ከብሔረሰቦች፣ ከሃይማኖት፣ ከፆታ እኩልነት አዋጁ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት እንደ አንድ ሰው የሚንቀሳቀስ ሕዝብ ነበር።

ለአብዮቱና ለአንድነቱ ለመስዋዕት በቁርጥ የተዘጋጀ ሕዝብ ነበር። የሶማሊያ መሪዎች እንደገመቱት ሳይሆን በተቃራኒው በተደረገለት የእናት ሃገር ጥሪ የሰጠው መልስና ብሎም በፍልሚያው የተቀዳጀው ድል ያልጥርጥር የሚያስረዳን የሶማሊያን ወራሪ ሠራዊት ድባቅ የመታው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት መሆኑን ነው።

እነዚህ ጠቅለል አድርጌ በአጭር የጠቃቀስኳቸው መሰረታዊ የሆኑ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ አመለካከትና አጠቃላይ የንቃተ ህሊና ፋይዳዎች ናቸው። በስህተትም ይሁን በግብዝነት የጀመሩት ወረራ ከወታደራዊው ስትራቴጂ አኳያ ስንመለከተው ደግሞ የሶማሊያ መሪዎች ስህተቶች ግዙፎች ናቸው።

ምንም ዓይነት የኢካኖሚ ምንጭ የሌለው፣ ምድረ በዳ ላይ የተቀመጠና በዓለም የመጨረሻው ደሃ ሃገር ብዛትና ጥራት ያለው መሣሪያ ስለተሸከመ ብቻ ተብቶ ከእሱ በብዙ ረገድ የሚልቀውን ጎረቤት ሃገር ቢወር ለጊዜው በውጊያው ያሸንፍ እንደሆን እንጅ ጦርነቱን አያሸንፍም።

ሌላው መታወቅ ያለበት ጉዳይ የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት የተሸከመውን ዘመናዊ የጦር መሣሪያ የመጠቀም፣ የመጠገን፣ የመለዋወጫ እቃ የነዳጅና ቅባት አቅርቦት ብቃትና እንዲሁም ፍጆቱን ደህና አድርጎ የማወቅ፣ የማቀድና የማዘጋጀት ችሎታ አልነበረውም።

የጦር መኮንኖቹ እያንዳንዳቸው 50 ቶን የሚከብዱና በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ታንኮቻቸውን ከሞቃዲሾ እስከ ድሬዳዋ ከሺህ ኪ/ሜትር በላይ እያንከባለሉ ሲመጡ ውሃ እየጠጡ እንደሚነዷቸው ግመሎቻቸው የተመለከቷቸው ይመስላል።

ለታንኮቻቸውና እንዲሁም ለተቀሩት ልዩ ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎቻቸው ነዳጅ ተሸክመው ለዳግም እደላ የሚከተሉትን ቦቴዎች እየመረጠ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ለጋየባቸው ውጊያውን ሳይሳተፉ በየመንገዱ በነዳጅና ቅብት

ታንኮች የአየር ኃይላችን የኢላማ መለማመጃ ሆነዋል። ሠራዊቱ ተሸንፎ ሲሸሽም በጥገና ጉድለትና በመለዋወጫ እቃ እጦት አብዛኞዎቹ ታንኮችና ልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎች ከጦሩ ጋር ወደ አገራቸው አልተመለሱም።

ከዚህ በላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የሶማሊያ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ለረጅም ጊዜ የሚያዋጋው አቅም ስለሌለው ለጊዜው በነበረው ከፍ ያለ የመሣሪያ የበላይነት ውጊያውን ያሸንፍ እንደሆን እንጅ  ጦርነቱን እንደማያሸንፍ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው ብያለሁ። በተለያዩ አቅጣጫዎች ሠራዊቱ 700 ኪ/ሜትር ያህል ጠልቆ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ይግባ እንጅ  በስትራቴጂ ጉድለት ምክንያት ውጊያውንም ቢሆን አላሸነፉም።

በአፍሪካ ደረጃ እጅግ ዘመናዊና መጠነ ሰፊ ሜካናይዝድ ሠራዊት በኢትዮጵያ ምስራ ክፍለ አገሮችና በተለይም በሐረር ክፍለ ሃገር ደግሞ፣ በጎዴ፣ በቀብሪደሐር፣ በዋርዴር፣ በደገሐቡር፣ በጅጅጋና ብሎም በቆሬ ሸለቆና በኋላም በድሬዳዋ አቅጣጫ ከመበታተን ፋንታ በአንድ አቅጣጫ ማለትም በጅጅጋ ወይንም በድሬዳዋ ብቻ በጥልቀት ቢያሰልፈው ኖሮ አዲስ አበባ ለመግባት የሚያውከው ነገር የነበረ አይመስለኝም።

በሶማሊያ የመሣሪያ አጠቃቀም ጉድለትና የስትራቴጂ ስህተት በኛ በኩል የነበረው የጦር መሣሪያ ድህነት ወይንም ከፍ ያለ እጥረት መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ ለመከላከል በሚያመቹና የአገራችን ደጋማ አውራጃዎች ከፍታማ መሬቶች ላይ መሽገን ከስምንት ባልበለጡ ተዋጊ አውሮፕላኖችና ቀላል መሣሪያዎች በታጠቀ እግረኛ ሠራዊት የጠላትን ጥቃት መከተን ጊዜ ለመግዛት ቻልን።

የሶማሊያ መኮንኖች አብዛኞዎቹ ታንኮቻቸውና ከባድ መሣሪያዎቻቸው ከጥቅም ውጪ ከሆነባቸው በኋላ ከስህተታቸው የተማሩ ይመስላል ሐረርጌን ለመያዝ የመጨረሻ ጥረት ባደረጉበት ጊዜ የተጠቀሙበት የከበባ ውጊያ ሥልት፤ የመሬትና የመድፍ አጠቃቀማቸው ግሩም በጣም ግሩም ነበር።

ከስድስት ወራት በላይ ደሞዝ ሳይከፍለው፤ በቂ ቀለብ ሳይቀርብለት፤ በቂ የህክምና አገልግሎት ሳይሰጠው፤ በባዕድ ሃገር፤ በማያውቀው ምድርና ቀዝቃዛ የአየር ንብረት በኢትዮጵያ አብዮታዊ ሠራዊት ጥይት እየተጠዘጠዘና አየር ኃይላችን ያለማቋረጥ በቦምብና በሮኬት እየደበደበው የሶማሊያ ሠራዊት ፀንቶ መዋጋቱ የሠራዊቱን ሥነ ሥርዓት አክባሪነትና የመኮንኖቹን ጥብቅነት የሚያስረዳ ነው።

በጀግንነትም ቢሆን የሚናቁ አይደሉም። አብዮታዊ ሠራዊታችን ፈዲስ ላይ የነበረውን ኃይላቸውን በታንክ እየተረዳ ባጠቃበት ጊዜ በጽኑ ተከላክለው ብዙ ጉዳት ከማድረሳቸው ሌላ ብዙ ወታደሮች ታንኮቻችን ላይ እየዘለሉ በመውጣት በታንኩ ቱሬት የእጅ ቦምብ ለመክተት ሲሞክሩ ታይተዋል።

በመጨረሻም እኛ መልሰን በማጥቃት ብቻ ሳይሆን አንድ የሶማሊያ ወታደርና መሣሪያ ወደ ሶማሊያ ግዛት ሳይመለስ በኢትዮጵያ ምድር ለማስቀረት ያዘጋጀንላቸውን ወጥመድ ተገንዝበውና ኢትዮጵያን መውረራቸው ታላቅ ስህተት መሆኑን ከጦር ሜዳ ተምረውና ታርመው መሸሻቸው ብልህነት ነው።

# መዘርዝር

ይህ ትግላችን ቅፅ አንድ ከሚያተኩርባቸው የጊዜ ክልሎች ማለትም ከየካቲት ወር 1966 እስከ ሰኔ ወር 1970 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአብዮቱ የተቀዳጃቸው ድሎችና አበይት አብዮታዊ ክንውኖች ዝርዝር፣

## ከየካቲት ወር 1966 ዓ.ም እስከ መስከረም 1967 ዓ. ም

1ኛ/ በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም በነገሌ ቦረና ሰፍሮ የነበረው የአራተኛ እግረኛ ብርጌድ ጦር ሲገበኙት የሄዱትን የምድር ጦር አዛዥ ሌ/ጄኔራል ድረሴ ዱባለን ከነተከታዮቻቸው በቁጥጥሩ ስር በማዋል ለመላው የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት አብዮቱ መጀመሩን አበሰረ፤

2ኛ/ በሰሜን ኢትዮጵያ ማለትም በኤርትራ ሰፍሮ የነበረው ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር የአራተኛ እግረኛ ብርጌድን የአብዮት ፋና ወጊነት በመደገፍ በክፍለ ጦሩ ውስጥ የነበሩትን ከሻለቃ ማዕረግ በላይ ያሉ መኮንኖች፣ የክፍለ ጦሩን አዛዥ ጄኔራል መኮንንና ምክትል አዛዡን፣ የክፍለ አገሩን አስተዳዳሪ፣ ምክትል አስተዳዳሪና ሌሎች የክልሉን ከፍተኛ የሲቪል ባለሥልጣኖች በቁጥጥሩ ስር በማድረግ በአስመራ ራዲዮ አማካኝነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት መቀጣጠሉን ለመላው የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት አበሰረ።

3ኛ/ መንግሥት አማፅያኑን አግባብተው የታሰሩትን ከፍተኛ ወታደራዊና የሲቪል ባለሥልጣኖች በማስፈታት አመፁን እንዲገቱ የላከቸውን ከፍተኛ ጄኔራል መኮንኖች በቁጥጥሩ ስር አውሎ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ ከሥልጣናቸው እንዲነሱ ጠየቀ።

4ኛ/ ሁለተኛው ዋሊያ እግረኛ ክፍለ ጦር የወሰደውን አብዮታዊ እርምጃ መላው የአገሪቱ የጦር ኃይሎች መደገፋቸውን ከመግለጣቸው ሌላ በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መሪነት የምድር ጦር አየር ክፍል፣ በአዲስ አበባ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች የሁለተኛ እግረኛ ዋሊያ ክፍለ ጦርን ጥያቄ ተግባራዊ ለማድረግ በአዲስ አበባ ከተማ አብዮታዊ ንቅናቄ አድርገው ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድን ከሥልጣናቸው በማስነሳት ልጅ እንዳልካቸው መኮንን እንዲተኩ አደረጉ።

5ኛ/ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው እንደተሾሙ፣ በአወጡት የፖለቲካ ፕሮግራም አማካኝነት ለሕዝቡ በገቡት ቃል መሰረት በጠቅላይ ምኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ አመራር ጊዜ ሕዝብ የበደሉና ያለአግባብ የበለፀጉ ባለሥልጣኖች ለፍርድ ይቀርቡ ዘንድ በወታደር እያሳደኑ እንዲታሰሩ አደረጉ።

6ኛ/ የፊውዳሉ ሥርዓት አራማጅ ገዥ መደቦች ጋሻና መከታ ብቻ ሳይሆን የሥርዓቱ አይነተኛ መሳሪያ የሆኑት የአገሪቱ የጦር ኃይሎች በገሀድ በሥርዓቱ ላይ አምፀው መነሳታቸውን ያስተዋለው ሕዝብ ከእንግዲህ ማን ሊፈራ በማለት ያለማቋረጥ፣ በየፈርጁ በፈረቃና በህብረት በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ መንግሥትን በመቃወም ሠላማዊ ሰልፍና የስራ ማቆም አድማ አደረገ።

7ኛ/ የአገሪቱ የጦር ኃይሎች የእዝ ሰንሰለታቸውን በየክልሉና በየጦር ክፍላቸው ሰብረው ወይም ቆርጠው የመከ ላከያ ሠራዊቱ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላው መለዮ ለባሽ የሚመራው በጊዜያዊ ሀቡዕ ኮሚቴ ሆነ።

8ኛ/ በመላ አገሪቱ ያሉ የተለያዩ የማምረቻ፣ የማከፋፈያ፣ ልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጪና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችም እንደመለዮ ለባሹ ከአሰሪዎቻቸውና ከበላይ አመራራቸው ጋር የነበራቸውን ሕጋዊና መደበኛ የስራ ግንኙነት አቋርጠው የየራሳቸውን ሕዝባዊ የአመራር ኮሚቴዎችን አቋቋሙ።

9ኛ/ የአገሪቱ መላው የትምህርት ቤቶች፣ በየትኛውም ደረጃ ያሉ መምህራን፣ የአዲስ አበባን ዩኒቨርስቲ ጨምሮ የመለዮ ለባሹንና የሕዝቡን አመፅ በመደገፍ የመማርና የማስተማር ተግባራቸውን አቆሙ።

10ኛ/ የአገሪቱ ሠራተኞች ማህበር ማዕከላዊ አመራር በየክልሉ ያሉትን የማህበሩን ቅርንጫፎችና ዘርፎች የአመራር አካላት ከየአሉበት ወደ አዲስ አበባ ጠርቶ በማህበሩ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከየካቲት 16 እስከ 22 ሲመክር ቆይቶ 16ተራ የያዙ ጥያቄዎችን ለአዲሱ የልጅ እንዳልካቸው መንግሥት በማቅረብ ለጥያቄያቸው ተገቢው መልስ እስከ የካቲት 28 ድረስ ባይሰጠው አገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ እንደሚያደርግ አስታውቆ ስብሰባውን በተነ።

11ኛ/ ግንቦት 11 ቀን 1966 ዓ.ም አዲሱ መንግሥት የምሥራቁን ክልል መለዮ ለባሾች እንዲያነጋግሩ በጄኔራል ወ/ሥላሴ በረካ መሪነት ወደ ሐረር የላካቸውን የከፍተኛ ጄኔራል መኮንኖች ልዑካን ሦስተኛ እንበሳው እግረኛ ክፍለ ጦር ሠራዊት በቁጥጥሩ ስር አድርጎ የአብዮቱ ሂደት መቀጠሉን ለመላው የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት አበሰረ።

12ኛ/ ግንቦት 17 ቀን 1966 ዓ.ም በሐረር ከጄኔራሎቹ መታሰር ጋር በተያያዘ ሁኔታ የክፍለ ጦሩ ሠራዊት ለክፍለ አገሩ ነዋሪ ሕዝብ በአደረገው ቅስቀሳ መሰረት በሐረር ከተማ ግንቦት 26 ቀን 1966 ዓ.ም በድሬደዋ ከተማ ከአዲስ አበባ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሰላማዊ ሰልፍ በተደረገ ማግሥት በተቀሩትም የአገሪቱ ክፍለ ሃገራት ከተሞች በተከታታይ በአገሪቱ ታሪክ ላይ ታይተው የማይታወቁ ሕዝባዊ ሰልፎች ተደረጉ።

13ኛ/ ሰኔ 17 ቀን 1966 ዓ.ም በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር መሪነት በአዲስ አበባ ከተማና በዙሪያዋ የሚኖሩ ልዩ ልዩ የጦር ክፍሎች በህብረት ለሦስተኛ ጊዜ ከጦር ሰፈራቸው በትጥቅ ወተው የአገሪቱን ማዕከላዊ የዜና ማሰራጫ፣ ባንኮችና መጠበቅ ያለባቸውን ተቋማት በሙሉ በቁጥጥራቸው ስሩ አደረጉ።

14ኛ/ ሰኔ 18 ቀን 1966 ዓ.ም ሦስተኛውንና የመጨረሻውን የጦር ኃይሎች አብዮታዊ ንቅናቄ ለማብሰርና ለንቅናቄውም መላውን መለዮ ለባሽ አቀፍ የአመራር ማዕከል ለመፍጠር በታቀደው መሰረት ከሦስቱ የጦር ኃይሎች ማለትም ከምድር ጦር፣ ከአየር ኃይል ከባሕር ኃይልና እንዲሁም ከፖሊስ ሠራዊት፣ በምድር ጦር ዕዝ ስር ያሉት እግረኛ ክፍለጦሮችና ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች ሁሉ እንዲወክሏቸው የሚፈልጓቸውን ተወካዮች መጠንና የማዕረግ ደረጃ በመግለፅ አዲስ አበባ አራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ጠቅላይ ሰፈር ድረስ ይልኩ ዘንድ ጥሪ ተደረገ።

15ኛ/ በጥሪው መሰረት አዲስ አበባ በአራተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር ግቢ የተሰበሰቡት የሠራዊቱ ተወካዮች ሰኔ 21 ቀን 19 66 ዓ.ም አብዮታዊውን ደርግ አቋቋሙ።

16ኛ/ ሰኔ 22 ቀን 1966ዓ.ም ደርግ ህልውናውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አበሠረ።

17ኛ/ ሰኔ 23 ቀን 1966ዓ.ም ደርግ በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው ትዕዛዝ በኮሎኔል የየዓለምዘውድ ይመራ የነበረው ወታደራዊ ኮሚቴ ያሰራቸውን የመከላከያ ሠራዊት አባሎች በመፍታት ወደየጦር ክፍላቸው መለሳቸው።

18ኛ/ በዚሁ ቀን ለንጉሡና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያን ለማስቀደም የተነሳበትን ዓላማና ስለአገሪቱም ሰላም የአለበትን ሃላፊነት ከመግለፅ ጋር ለሰላምና ለመረጋጋት የሚያደርገውን አስተዋፆ የሚገልፅ ቤተመንግሥቱንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ውጥረት በማርገብ የሚያዝናኑ ደብዳቤዎች ከደርጉ ተላከላቸው።



19ኛ/ በዚሁ ቀን በደርጉ ጥያቄና በንጉሡ ፈቃድ ሜ/ጄኔራል አማን ሚካኤል አምዶም በሌ/ጄኔራልነት ማዕረግ የአገሪቱ የጦርኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ሆነው ተሾሙ።

20ኛ/ በዚሁ ቀን ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው አቋቁመውት የነበረው ብሔራዊ የፀጥታ ኮሚሽንን ደርግ አፈረሰው።

21ኛ/ በዚሁ ቀን በአገሪቱ ርዕሰ ከተማ በአዲስ አበባና በየክፍለ አገሩ ወህኒቤቶች ታስረው ሲሰቃዩ የነበሩ የፖለቲካ እስረኞችን በሙሉ ደርጉ ፈትቶ በነፃ ለቀቃቸው።

22ኛ/ ሐምሌ 26 ቀን 1966 ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው ጥያቄ ደርግንና የሚኒስትሮች ምክር ቤትን የሚያገናኝ ኮሚቴ ከሁለቱ ተቋሞች በተወጣጡ ስድስት ሰዎች ተቋቋመ።

23ኛ/ በአገናኝ ኮሚቴው አማካኝነት ከደርግ አመራር አካላትና ከሚኒስትሮች ምክር ቤት እኩል በእኩል በተመረጡና በተውጣጡ ግለሰቦች የሚኒስትሮች ምክር ቤቱን በውክ ሥልጣን እንጋራ በማለት ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው ያቀረቡትን ጥያቄ አብዮታዊው ደርግ የተቋቋመው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት ለማድረግ እንጂ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ዘውዳዊ መንግሥት ተክቶ ራሱን ሥልጣን ማማ ላይ ለማውጣት ስላልሆነ የቀረበለትን ሥልጣን የመጋራት ጥያቄ እንደማይቀበል አስታወቀ።

24ኛ/ ሐምሌ 27 ቀን 1966 ዓ.ም የፖለቲካ ስደተኛ ሆነው በተለያዩ ባዕዳን አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ወደ አገራቸው ተመልሰው የሕዝባዊው አብዮት ተባታፊ ይሆኑ ዘንድ ለደህንነታቸው አስተማማኝ ዋስትና ከመስጠት ጋር በደርጉ ጥሪ ተደረገላቸው።

25ኛ/ ከሰኔ 22 እስከ 30 1966 ዓ.ም ድረስ በነበሩት ቀናቶች ውስጥ የአፄ ኃይለሥላሴ መለኮታዊ ሥልጣን መጠበቂያ አይነተኛ መሳሪያ የነበሩትን የአገሪቱን፣ የደህንነት አመራር ማዕከል፣ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የነበሩትን ቅርንጫፎቹን፣ የንጉሠ ነገሥቱን ልዩ ኤታማዦር ጽህፈት ቤትና በስሩ የነበሩትን የኤሌክትሮኒክ የስለላ መሳሪያዎች፣ የንጉሠ ነገሥቱን የዘውድ ምክርቤትና የዙፋን ችሎት ወዘተ ስናፈራርስ የተቀሩትን በቁጥጥር ስር አውለን ለአብዮቱ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደረገ።

26ኛ/ በእነዚሁ ቀናቶች ውስጥ ሕዝቡን የበደሉና ያለአግባብ የበለፀጉ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖቹን ወንጀል መርምሮ ለፍርድ የሚያቀርብ መርማሪ ኮሚሽንና ጊዜያዊ ሕዝባዊ የመማክርት ሸንጎ ተቋቋመ።

27ኛ/ ሐምሌ 30 ቀን 1966 ዓ.ም ኢትዮጵያ ምን አይነት መንግሥት ያስፈልጋታል የሚል ጥያቄ በደርግ ለሕዝቡ ቀርቦ፣ ሕዝቡም በቀረቡለት የሃሳብ መስጫ ሳጥኖች አማካኝነት ሃሳቡንና የሚፈልገውን የመንግሥት አይነት ምርጫውን ሰጠ።

28ኛ/ በነሐሴ ወር ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን በስዊዝ ባንክ ያስቀመጡትን ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ መልሰው ከድህነት ወለል በታች መቆሙ አንሶ በርሀብ ለሚሞተው ሕዝብ እንዲለግሱት ተጠየቁ።

29ኛ/ ነሐሴ 15 ቀን 1966 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንን ከሥልጣናቸው ወረዱ።

30ኛ/ በዚሁ ቀን ልጅ ሚካኤል እምሩ በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው ምትክ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው በደርግ ተሾሙ።

31ኛ/ ለ1967 ዓ.ም አጥቢያ ምሽት ደርግ የወሎንና የትግራይን ሕዝብ የተደበቀ እጅግ አሰቃቂ ሁኔታ የሚያሳየውን በርሀብ እልቂት ፊልም ንጉሡና የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያስተውሉ ጋበዘ።

## ከመስከረም 1967 ዓ.ም እስከ መስከረም 1968 ዓ.ም

32ኛ/ መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም በጉልታዊ ሥርዓት ማህበር የሚመራው ፊላዴ ቀራጭ፤ መለኮታዊ የዘውድ አገዛዝ ተገረሰሰ።

33ኛ/ መስከረም 3 ቀን 1967 ዓ.ም በቤተመንግሥቱ አመራር ስር ሆኖ የበጎ አድራጎት እየተባለ ይጠራ የነበረው ድርጅት በመንግሥት ቁጥጥር ስር የሕዝብ ይዞታ ሆነ።

34ኛ/ መስከረም 24 ቀን 1967 ዓ.ም የቅንጦት የቤት ተሽከርካሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ ሃገር ውስጥ እንዳይገቡ ታገዱ።

35ኛ/ መስከረም 24 ቀን 1967 ዓ.ም በቅድመ አብዮት ባለሥልጣን የነበሩ ግለሰቦች፤ ንጉሣዊያን ቤተሰቦች፤ መሣፍንትና መኳንንት ወዘተ አብዛኛው በገጠር የሚጠቀሙበት የእርሻ መሬት፤ በከተማ የሚገለገሉበትን የህንፃ፤ የንግድና ሌሎችም ግብሮች ሳይከፍሉ ይኖሩ ስለነበረ ይህንን ለረጅም ዓመታት የተከበተ ውዝፍ የመንግሥት ግብር በሕግ ተገደው በአንዴ እንዲከፍሉ ተደረገ።

36ኛ/ ጥቅምት 8 ቀን 1967 ዓ.ም የእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ መምሪያ በአዋጅ ተቋቋመ።

37ኛ/ ጥቅምት 25 ቀን 1967 ዓ.ም ከወራሪ ፋሽስት የኢጣሊያ መንግሥት በሕዝቡ ደምና ሕይወት የኢትዮጵያ መንግሥት የተረከባቸውን የተለያየ መጠንና አገልግሎት ያላቸውን መሥሪያ እና መኖሪያ የሆኑ ዘመናዊ ህንፃዎች፤ ንጉሡ ለተለያዩ ሀብታም መሣፍንትና መኳንንት በስጦታ አድለዋቸው ስለነበረ እነዚሀ የሕዝብ ሀብትና ንብረቶች በመንግሥት ቁጥጥር ስር የሕዝብ ይዞታ እንዲሆኑ ተደረገ።

38ኛ/ ታህሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም ኅብረተሰባዊነት ወይም ሶሻሊዝም የኢትዮጵያ ሕዝብ የእድገት አቅጣጫ መመሪያ እንዲሆን ታወጀ።

39ኛ/ በዚሁ ቀን የአብዮቱን ባህርይና አቅጣጫ እንዲሁም ግብ የሚያስረዳና ስለ ሕዝባዊ ድርጅቶች፤ ስለፖለቲካ ፓርቲዎችና ስለሕዝባዊ መንግሥት አመሰራረት የሚገልፅ የፖለቲካ ፕሮግራም ወጣ።

40ኛ/ ታህሳስ 12 ቀን 1967 ዓ.ም የእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ የከተት በዓል በአዲስ አበባ ከተማ በታላቅ ስልፍና ሥርዓት ተከበረ።

41ኛ/ ታህሳስ 14 ቀን 1967 ዓ.ም በኢትዮጵያ ያሉ መንፈሳዊ እምነቶች ወይም ሃይማኖቶች እኩልነት፤ አንዱ ከሌላው ባነሰ የማይታይበት፤ የሃይማኖት መድሎ የማይደረግበትና የኢትዮጵያዊያን የሀሊና ነፃነት ታወጀ።

42ኛ/ ታህሳስ 15 ቀን 1967 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በአገሪቱ ራዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች የኦሮሞ ቋንቋ ፕሮግራም እንዲሰራጭ፤ ጋዜጦችና መጽሄቶች እንዲታተሙ ከማድረግ ጋር የብሔረሰቦች የቋንቋ፤ የባህል እኩልነትና ነፃነት ታወጀ።

43ኛ/ ታህሳስ 23 ቀን 1967 ዓ.ም የባዕዳን ድንበር ዘለል ከበርቴዎች የጥቅም ምንጭ የነበሩ የንግድ ባንኮች፤ የገንዘብ ድርጅቶችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በመንግሥት ቁጥጥር ስር የሕዝብ ይዞታ ሆኑ።

44ኛ/ ጥር 2 ቀን 1967 ዓ.ም የኢትዮጵያ አርሶ አደር በተለይና ጠቅላላውን ገጠሬ ሕዝብ በአጠቃላይ ከማህይምነት ጨለማ ለማውጣት፤ የፖለቲካ ንቃት ለመስጠት፤ የገጠሩን የእርሻ መሬት ለማከፋፈልና ገበሬውን በማህበር ለማደራጀት ከአብዮታዊ ሠራዊት፤ ከሁለተኛ ደረጃና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ከመምህራኖቻቸው ጋር በጠቅላላ 60,000 ዘማቾች በመላው ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት ዘመቱ።



45ኛ/ ጥር 26 ቀን 1967 ዓ.ም በአገሪቱ በተለያዩ ከተሞችና አውደ ከተሞች ያሉና አብዛኛው የድንበር ዘለል ከበርቴዎች የጥቅም ምንጭ የነበሩ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ የማምረቻ፤ የማከፋፈያና የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ ተቋሞች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሕዝብ ይዞታ ሆኑ።

46ኛ/ የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም በአፍሪካ ቀርቶ በዓለም ታላላቅ አብዮቶች ታሪክም ወደር የሌለው፤ የጉልተኞች ገባር፤ ጢሰኛና ሎሌ የነበሩትን ጭቁንና ምንዱብ አርሶ አደሮች ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያንን ከጉልተኞች መዳፍ ነፃ ያወጣው ታሪካዊው የመሬት አዋጅ ታወጀ።

47ኛ/ መጋቢት 28 ቀን 1967 ዓ.ም ሚያዝያ 27 ቀን እንዲከበር የሆነው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን የግል ዝና ለማጋነን እንጂ ከሳቸው ቀድመው የኢትዮጵያ አርበኞች ፋሽስትን ድል በመምታት የኢትዮጵያን ነፃነት ያበሰሩት መጋቢት 28 ቀን ስለሆነ የድል መታሰቢያ ቀን ድሉን ላበሰረው ታጋይ አርበኛ ይሰጥ ብለው የኢትዮጵያ አርበኞች ማህበር አመራር አካላት በአመለከቱት መሠረት በፋሽስት ኢጣሊያ ላይ የተቀዳጀነው የድል በዓል መጋቢት 28 ቀን እንዲሆን ተወሰነ።

48ኛ/ መጋቢት 29 ቀን 1967 ዓ.ም የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች በመንግሥት ቁጥጥር ስር የሕዝብ ይዞታ ሆኑ።

49ኛ/ ሚያዝያ 23 ቀን 1967 ዓ.ም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓለም ወዛደሮች ቀን በመላው ኢትዮጵያ ከፍ ባለ ሥርዓትና ድምቀት ተከበረ።

50ኛ/ ግንቦት 11 ቀን 1967 ዓ.ም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ኮሚሽን በሕግ ተቋቋመ።

## ከመስከረም 1968 ዓ.ም እስከ መስከረም 1969 ዓ.ም

51ኛ/ መስከረም 18 ቀን 1968 ዓ.ም የግል ትምህርት ቤቶችን በመንግሥት ቁጥጥር ስር የሕዝብ ይዞታ የሚያደርግ አዋጅ ታወጀ።

52ኛ/ ህዳር 26 ቀን 1968 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብ ሰብዓዊ፤ ዲሞክራሲያዊ፤ ኢኮኖሚያዊ መብትና ጥቅማጥቅሞቻቸውን በሚገባ የሚያስከብሩበትና አምራቹን ወዝ አደር የሚንከባከብ የሠራተኛ መተዳደሪያ ሕግ ታወጀ።

53ኛ/ ታህሳስ 19 ቀን 1968 ዓ.ም መሬት ለአራሹ አብዮታዊ አዋጅ ነፃ የወጡትን የኢትዮጵያ ነፃ ገበሬዎች የቀበሌ ማህበራት ወደ ከፍተኛ ንቃትና ድርጅት፤ ወደ ከፍተኛ ምርትና ማህበራዊ አመራረት የሚወስዳቸው ማጠናከሪያ አዋጅ ታወጀ።

54ኛ/ ሐምሌ 7 ቀን 1968 ዓ.ም በኢትዮጵያ ብዙሃን ሕዝባዊ ድርጅቶችን ከማደራጀት ባሻገር በአገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆኑትን የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደራጁበትን ሁኔታዎች በማመቻቸትና ብሉም በመርዳት ወደ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ምስረታ ለማምራት የሚያስችል ሰሙ የሕዝብ ማደራጃ በመባል የሚጠራ ተቋምና የፖለቲካ ትምህርት ቤት ማቋቋሚያ ሕግ ታወጀ።

## ከመስከረም 1969 ዓ.ም እስከ መስከረም 1970 ዓ.ም

55ኛ/ መስከረም 10 ቀን 1969 ዓ.ም የኢትዮጵያን አጠቃላይ ገንዘብ ነክ ጉዳይ አመራር ወይም አስተዳደር የገንዘቦች አሰራር በኢትዮጵያ አዲስ የገንዘብ መውጣት፣ አይነት ስርጭቱን ወዘተ አዋጅ ታወጀ።

56ኛ/ መስከረም 29 ቀን 1969 ዓ.ም የከተማ ቀበሌ ማህበራትን ማጠናከሪያ የአውደ ከተሞች የአጠቃላይ ምክር ቤትና የአመራር አካላት አደረጃጀትን የሚደነግግ አዋጅ ታወጀ።

57ኛ/ ሚያዝያ 4 ቀን 1969 ዓ.ም ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና አድሀሮት፣ የአካባቢው ተስፋፊዎች የውስጥ ፀረ-አንድነትና ፀረ-አብዮት በሕብረት ያወጁብንን ጦርነት ለመከላከል ለኢትዮጵያ ሕዝብ አገርንና አብዮትን የማዳን ታሪካዊ የእናት ሃገር ጥሪ ተደረገ።

58ኛ/ በእናት አገር ጥሪ መሰረት ታሪካዊው የታጠቅ የጦር ሰፈር ተገንብቶ ሦስት መቶ ሺህ ሠራዊት እዉ ምልምሎች በጦር ሰፈሩ ከተቱ።

59ኛ/ መስከረም 7 ቀን 1969 ዓ.ም የመላው ኢትዮጵያ ገበሬዎች ሃገር አቀፍ ማህበር መኢገማ ማቋቋሚያ አዋጅ ታወጀ።

60ኛ/ ሰኔ 19 ቀን 1969 ዓ.ም የኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት እናት አገሩንና አብዮቱን ከወረራ ለማዳን ወደ ጦር ሜዳ ከመሰማራቱ በፊት በአዲስ አበባ አብዮት አደባባይ ዓለም ያደነቀውን የጀግና ሰልፍ አሳየ።

61ኛ/ ከሰኔ 1969 ዓ.ም ጀምሮ ለሰባት ወራት የኢትዮጵያ አብዮታዊ አንደኛው ሠራዊት የተስፋፊውን የሱማሌን መንግ ሥት ሠራዊት ወረራ መክቶ በሚያኮራ ሁኔታ ተከላከለ።

62ኛ/ ከህዳር 15 ቀን 1970ዓ.ም ጀምሮ የኢትዮጵያ አንደኛው አብዮታዊ ሠራዊት ከመከላከል ወደ ማጥቃት ተግባር ተሸጋገረ።

63ኛ/ በዚሁ ዓመት በህዳር ወር መገባደጃ የኢትዮጵያ አብዮታዊ አንደኛው ሠራዊት በተስፋፊው የሱማሌ መንግሥት ወራሪ ሠራዊት ላይ የማያዳግም የጦር ሜዳ ድል ተቀዳጀ።

# የቃላቶች ትርጉም

**ሆርሻ፡-** ቴክኒካዊ የፈጠራ፣ የማምረቻ፣ የእደሳና የጥገና ወዘተ የሚከናወኑበት ህንፃ ወይም ስፍራ ማለት ነው።

**ሉባ፡-** ጥንታዊው የኦሮሞ ማህበረሰብ ይተዳደርበት የነበረው ገዳ በመባል የሚታወቀው የጎሳ ማህበር መዋቅር ውስጥ የመከላከያ፣ የፍርድና የአስተዳደሩን ስራ በበላይነትና በወል እንዲመሩ በጎሳው ማህበር ጠቅላላ አባላት ስብሰባ የሚመረጡ ከ40 እስከ 48 ዓመት እድሜ ያላቸው የጎልማሶች ቡድን የወል መጠሪያ ስም ነው።

**ላዕላይ መዋቅር፡-** የአንድ ድርጅት ወይም ተቋም በተለይም እኔ በተጠቀምኩበት አረገድ፣ የአንድ ፖለቲካ ሥርዓት-ማህበር የአንድ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ከፍተኛ የአመራር ማዕከል መዋቅር ሲሆን በጠቅላላ አነጋገር ፖለቲካው ማለት ነው።

**ሕቡዕ፡-** የቃሉ ምንጭ ግዕዝ ነው። ትርጉሙ የተደበቀ ወይም የተሰወረ ማለት ነው።

**ማህበረሰብ፡-** በጎብረተሰብ የእድገት ታሪክ ሂደትና ማህበራዊ አደረጃጀት፣ ከቤተሰብ፣ ከቤተዘመድ፣ ከመንደር ወይም ከጎጥ በላይ የሆነና በርካታ ጎጦችን ወይም መንደሮችን ያሰባሰበና በሦስተኛ ደረጃ የሚገኝ ማህበራዊ ድርጅት ነው።

**መስመራዊ መኮንኖች፡-** ከሻለቃ ማዕረግ በታች ላሉ የጦር መኮንኖች የተሰጠ መለያ ነው።

**ቅልፈት፡-** በኢትዮጵያ አብዮታዊ የመከላከያ ሠራዊት ውስጥ የበርካታ የጭነት ተሽከርካሪዎች ከትትል ወይም ጉዞ ወይም የተሽከርካሪዎች ጋተሎ ማለት ነው።

**ትምር፡-** ጥምር፣ ቅልቅል፣ ስብስብ ወይም ስብጥር ማለት ነው።

**ቡርዥዋ፡-** ቃሉ ከፈረንሳይ ቋንቋ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ የከበርቴ መደብ ማለት ነው።

**ብሔር፡-** በጎብረተሰብ የእድገት ሂደት ታሪክና ማህበራዊ አደረጃጀት ከፍተኛውና የመጨረሻው ሲሆን ፀሀ ቃል ከዘር፣ ከነገድና ከጎሳ መግለጫነት እጅግ የሰፋና የላቀ ትርጉም ያለው፣ የአንድ አገር ወይም ሕዝብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ወዘተ በጠቅላላው ሁለንተናዊ ማህበራዊ እርከንን የሚያሳይ የእድገት መግለጫና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ እያሌ ማህበረሰቦችን እና ብሄረሰቦችን ያካተተ ማህበራዊ ድርጅት ነው።

**ብሀርታዊ፡-** የተለያዩ ወይም በርካታ ማህበረሰቦች፣ ብሄረሰቦችና የቋንቃ ቤተሰቦች የተካተቱበት ወይም የተቃመሩበት የቋንቋ ቤተሰብ ወይም ኅብረተሰብ ማለት ነው።

**ባለሌላ ማዕረግተኞች፡-** ከመጀመሪያው የውትድርና ማዕረግ ማለትም፣ ከምክትል የአስር አልቃና ጀምሮ እስከ ሻለቃ ባሻ ድረስ ያሉትን በሌላ አነጋገር መኮንን ያልሆኑትን ወታደራዊ ሹማምንት መለያ ስም ነው።

**ታህታዊ መዋቅር፡-** አንድ አገር በሚመራበት ማህበራዊ ወይም የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ፖለቲካውን ወይም ላዕላይ መዋቅሩን የተሸከመው ወይም ለፖለቲካው መሰረት የሆነውን ኢኮኖሚውን ማለትም፣ የመሬቱ፣ የግብርናው፣ የማዕድኑ፣ የኢንዱስትሪው፣ የገንዘቡ ወዘተ አደረጃጀት መዋቅር ማለት ነው።

**የምርት ኃይሎች:-** እምራቹን ሠርቶ አደር ሕዝብና የሚያመርትባቸውን የማምረቻ መሳሪያዎችን ያጠቃለለ የወል ስም ነው።

**ጎጥ:-** ይህ ቃል በአብዛኛው የአገራችን ሰሜናዊ ክልል ነዋሪ ሕዝብ መንደር ለማለት የሚጠቀምበት ቃል ነው።

**እባወራ:-** ቃሉ የተገኘው ከኦሮሞ ብሄረሰብ ሲሆን ትርጉሙ የቤተሰብ ሃላፊ፣ የቤተሰብ አባት ወይም አውራ ማለት ነው።

**ጠገግ:-** የድርጅታዊ መዋቅር ተዋረድ፣ አስተዳደራዊ ተዋረድ ወይም የእዝ ሰንሰለት ማለት ነው።

**ካድሬ:-** በምሁራን ዘንድ የሚታወቀው ለአንድ ልዩና ምርጥ ስራ የተመረጠ አነስተኛ የሰው ቁጥር ወይም ቡድን ማለት ሲሆን በማርክሲያዊያን ትርጉም ግን መሪ፣ አስተማሪ፣ መልካም ምሳሌና አርአያ ማለት ሲሆን፣ የሰራተኛው መደብ ግንባር ቀደም መሪ የሆኑ ድርጅቶች ወይም ፓርቲዎች አባላት ሁሉ የሚጠሩበት ስም ነው።

**ግብረኃይል:-** ይህ ቃል በወታደራዊ ተቋሞች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሲቪሉም ኅብረተሰብ ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ለተለያዩ ተግባራት ሁለገብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በድህረ አብዮት በአብዮታዊ ሠራዊታችን ውስጥ በተለይ በሰሜኑ ውጊያ የተጠቀምንበት ወታደራዊ አደረጃጀት ነበር። ግብረኃይል የምንለው የጠላትን መጠንና አይነት፣ የሚዋጋበትን የመልክዓምድር አይነትና ባህሪ ካመዘገንና በኋላ ይህንን ጠላት ለመደምሰስ ይችላል ብለን በማደራጀት የምንወረውረው የጦር ክፍል ነው። አንድ ወጥ እግረኛ ጦር ወይም ሜካናይዝድ ወይም ታንከኛ ብቻ ወይም የነኝህ ሁሉ ቅምር ሊሆን ይችላል።

**ሜካናይዝድ ጦር:-** ቃሉ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን የዚህን ጦር አይነትና ባህሪ በትክክል የሚገልፅ ስም በአማርኛ ትርጉም ባለመገኘቱ በሠራዊታችን ውስጥ የእንግሊዝኛውን ቃል እንዳለ ስንጠቀምበት ኖረናል። አሁንም ትርጉም የተገኘለት አይመስለኝም። ሜካናይዝድ ጦር ማለት መቶ በመቶ በወታደራዊ የየብስ ተሽከርካሪዎች የሚጓዝ ሞተራይዝድ እግረኛ ጦርን፣ መቶ በመቶ በብረት ለበስ ተዋጊ ተሽከርካሪዎች የሚጓጓዝና የሚዋጋ ብረት ለበስ እግረኛና ታንከኛ ጦር ቅምር ማለት ነው። ሜካናይዝድ ጦር ከፍተኛ የመንቀሳቀስ ችሎታና ከፍተኛ የተኩስ ኃይል ያለው ፀረ-እግረኛ ጦር ነው።

# ዋቢ መጻሕፍት

በዚህ መጽሐፍ መቅድም ላይ እንደገለፅኩት፣ ታሪኩን ለመፃፍ ዋና መሰረት ያደረኩት ትዝታዎቼን ወይም ትውስታዎቼን ነው። ትውስታዎቼም ሁለት አይነት ናቸው። ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ዋዜማ ጀምሮ ከአብዮታዊ ሠራዊታችን፣ ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከኢትዮጵያ አብዮታዊያን ጋር ከአስተባባሪነት እስከ መሪነት የዋኘሁበት አብዮት በመሆኑ የተሰረፁብኝ የእየለቱ የተግባር ትውስታዎቼ ዋና መሰረቶች ናቸው።

ሌሎች ትውስታዎቼ፣ በቅድመ አብዮት ለረጅም ጊዜ፣ በድህረ አብዮት ለተወሰኑ ጊዜያቶች ያነበብኳቸው የተለያዩ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የፍልስፍና ወዘተ መጻሕፍትና ማርክሳዊ ሌኒናዊ የሆኑ አብዮታዊና ርዕዮተ ዓለማዊ መጻሕፍት ናቸው።

እነኝህ መጻሕፍት ከመበርከታቸውና ያነበብኩበትም ጊዜያቶች የዚያኑ ያህል ከመርዘማቸውም በላይ መጻሕፍቱ በእጄ ስለማይገኙ ያስታወስኳቸውን ጥቂቶቹንና በቅርቡ በስደት ላይ ሆኜ ያገላበጥኳቸውን ለዋቢነት ከዚህ እንደሚከተለው አቅርቢያቸዋለሁ።

## በአገር ውስጥ የተዘጋጁ


አለቃ ታዬ፣ *የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ* (አዲስ አበባ፣ 1964 ዓ.ም)

ላጲሶ ጌ. ደሌቦ፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የህዝብና የመንግስት ታሪክ* (አዲስ አበባ፣ 1982 ዓ.ም)

ላጲሶ ጌ. ደሌቦ፣ *የኢትዮጵያ የገባር ስርዓትና ጀምር ካፒታሊዝም* (አዲስ አበባ፣ 1983 ዓ.ም)

ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት* (አዲስ አበባ፣ 1980 ዓ.ም)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ይኩኖ አምላክ እስከ አፄ ልብነ ድንግል* (አዲስ አበባ፣ 1956 ዓ.ም)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ* (አዲስ አበባ፣ 1965 ዓ.ም)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ *አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት* (አዲስ አበባ፣ 1981 ዓ.ም)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ *አፄ ዮሃንስና የኢትዮጵያ አንድነት* (አዲስ አበባ፣ 1982 ዓ.ም)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ *አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት* (አዲስ አበባ፣ 1983 ዓ.ም)

ተክለፃዲቅ መኩሪያ፣ *የግራኝ አሕመድ ወረራ* (አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም)

ነጋድራስ አፈወርቅ፣ *ዳግማዊ ምኒልክ* (ሮማ፣ 1901 ዓ.ም)

ሐሊ ዝበናው፣ *አንድ ለናቱ* (አዲስ አበባ፣ 1983 ዓ.ም)

መንግስቱ ኃይለማርያም አርአያ እና መዝገቡ ምትኬ፣ *ጥርስ የገባች አገር* (በጆን ሃገዜብ የተጻፈ) (አዲስ አበባ፣ 1986 ዓ.ም)

ሚሊዮን ነቅንቅ፣ ትልቋ ኢትዮጵያ፣ የብዙሃን ነገዶች ማህረሰብ የረጅም ዘመናት እድገት (በዶናልድ ሌቪን የተጻፈ) (አዲስ አበባ፣ 1993 ዓ.ም)

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ህይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቅጽ 1 (አዲስ አበባ፣ 1965 ዓ.ም)

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ህይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ ቅጽ 2 (አዲስ አበባ፣ 1966 ዓ.ም)

ይልማ ደሬሳ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን (አዲስ አበባ፣ 1959 ዓ.ም)

## ከአገር ውጪ የተዘጋጁ

Badoglio, Pietro. *The War in Abyssinia* (London: Methuen, 1973)

Boca, Angelo Del. *The Ethiopian War, 1935-1941* (Chicago: The University of Chicago University Press, 1969).

Dye, William Mc E. *Moslem Egypt and Christian Ethiopia* (New York: Atkin & Prout Printers, 1880)

Hardie, Frank. *The Abyssinian Crisis* (London: B.T. Batsford, Ltd., 1974).

Makin, William J. *War Over Ethiopia* (London: Jarrolds Ltd., 1935)

Pankhurst, Sylvia. *Counsel for Ethiopia: A Biographical Essay on Ethiopian Anti-Fascist and Anti-Colonialist History 1934-1960* (Hollywood: Tsehai Publishers, 2003)

Pankhurst, Richard. "The Emperor Theodore and the Question of Foreign Artisans in Ethiopia," *Boston University Papers on Africa, V.2 African History*, J. Butler, ed. (Boston, 1966): 217-235

Skinner, Robert. *Abyssinia of Today: An Account of the First Mission Sent by the American Government to the Country of the King of Kings (1903-1904)* (London: E. Arnold; New York: Longmans, Green & Co. 1906)

# መጠቁም

...ሀ...

ሁሴን አብደላ ሻሂም፦ 331
ሆብስ ጋሎስ፦ 70
ሆሴን እስማኤል (አቶ)፦ 179
ሆጀ ኃይለሥላሴ (ሻለቃ)፦ 155
ሆጀ ጥበቡ (አቶ)፦ 179
ሆዴ ከራር (ፊታውራሪ)፦ 172

...ለ...

ለገሰ አስፋው (የሃምሳ አለቃ)፦ 135፣ 146፣ 156፣ 424፣ 444
ለገሰ አየለ (አቶ)፦ 181
ለገሰ ወ/ማርያም (ኮሎኔል)፦ 182
ሊንደን ጆንሰን (ፕሬዝዳንት)፦ 229
ሊዮኒድ ብሬዥኔቭ (ጓድ)፦ 347፣ 353፣ 359፣ 458-459
ሌሊሶ ጌ. ደሊቦ (ዶክተር)፦ 12፣ 327፣ 497
ልብነድንግል (አፄ)፦ 21፣ 23-24

...መ...

መለስ ማሩ (የመቶ አለቃ)፦ 155
መለስ ተክሌ (ዶክተር)፦ 246
መላኩ ተፈራ (የመቶ አለቃ)፦ 155
መሐመድ (ነቢዩ)፦ 19
መሐመድ ሳኒ (ሀጂ)፦ 172
መሐመድ አብዱራህማን (አቶ)፦ 183
መስፍን ወ/ማርያም (ዶክተር)፦ 179-180፣ 197
መስፍን ገብረቃል (ሌ/ኮሎኔል)፦ 444፣ 449
መስፍን ገብረቃል (ሻለቃ)፦ 126
መርሻ አድማሱ (ሻለቃ)፦ 179
መርዕድ ብሩ (ልጅ)፦ 177
መርዕድ ንጉሴ (ሌ/ኮሎኔል)፦ 127፣ 129
መርዕድ ግዛው (ሜ/ጀነራል)፦ 125፣ 129
መተል ጣሂር (ደጃዝማች)፦ 178
መነን (እቴጌ)፦ 89፣ 266-267
መንገሻ (ልዑል ራስ)፦ 42፣ 177፣ 368
መንግሥቱ ለማ (አቶ)፦ 182
መንግሥቱ ኃይለማርያም (ሻለቃ ፣ ኮሎኔል)፦ 145-146፣ 151፣ 153-154፣ 163፣ 171፣ 182፣ 196፣ 200፣ 212፣ 222፣ 235፣ 257፣ 344፣ 346፣ 354፣ 459
መንግሥቱ ነዋይ (ጀኔራል)፦ 82፣ 84-85፣ 87፣ 89፣ 113፣ 128፣ 130፣ 222
መንግሥቱ ገመቹ (የአሰር አለቃ)፦ 156
መኮሪያ (ሌ/ኮሎኔል)፦ 257
መኮንን (ልዑል ራስ)፦ 47፣ 59፣ 224
መኮንን ወ/ማርያም (ዶክተር)፦ 179
መዋዕለ መብራቱ (አቶ)፦ 179
ሙሉጌታ (ራስ)፦ 51
ሙሉጌታ ቡሊ (ጀኔራል)፦ 84
ሙሉጌታ አብርሃም (የአሰር አለቃ)፦ 156
ሙላቱ ነጋሽ (ኮሎኔል)፦ 415
ሙንሲንጀር ፓሻ፦ 37
ሚልዮን ነቅንቅ (አቶ)፦ 162
ሚካኤል አስገዶም (ፒ.ኦ)፦ 156
ሚካኤል እምሩ (ልጅ ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር)፦ 162፣ 177-179፣ 181፣ 183፣ 189-190፣ 194-195፣ 242፣ 245-246፣ 319፣ 455-456፣ 491
ሚካኤል ገብረንጉሥ (ሻምበል)፦ 153
ሚካኤል፦ (ራስ)፦ 384
ማልቲኮ (ማርሻል)፦ 54
ማሞ መዘምር (ሻምበል)፦ 130
ማሞ እጅጉ (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
ማርክስ፦ 3፣ 408
ማትያስ ሀብተወርቅ (ብላታ)፦ 172
ማንመክቶት ወንድማገኝ (ባሻ ፣ ሻለቃ)፦ 151፣ 155
ምህረተአብ ተድላ (ኮሎኔል)፦ 124
ምትኬ ደበሌ (ሻምበል)፦ 179
ምኒልክ (አፄ ፣ ንጉሥ ፣ እምዬ ፣ ዳግማዊ)፦ 10፣ 42-45፣ 47-51፣ 69፣ 77-78፣ 88፣ 190፣ 307፣

332-335፥ 337-338፥ 341፥ 366-368፥ 371፥ 412፥ 423፥ 474፥ 497
ምናሴ ኃይሌ (ዶክተር)፦ 162
ሞልቶት (የመቶ አለቃ)፦ 222
ሞገስ ወ/ሚካኤል (ጓድ ሻምበል)፦ 153-154፥ 350-351

...ሬ...

ረዳኢ (አቶ)፦ 182
ሩዝቬልት (ፕሬዝዳንት)፦ 58፥ 373
ራፋኤል ሮዛቲኒ (ሲኞር)፦ 331
ራፋዔል ካርሎስ (ጓድ)፦ 356
ሮሜል (ማርሻል)፦ 57

...ሰ...

ሱብለወንጌል (እቴጌ)፦ 25
ሰናይ ልኬ (ጓድ ዶክተር)፦ 246
ሰይፉ ይገዙ (አቶ)፦ 182
ሱሊማን (ሀጂ)፦ 182
ሱልጣን አሊ ሚራሁ፦ 177
ሲሳይ ሀብቴ (ሻምበል ፣ ሻለቃ)፦ 153-154፥ 171፥ 240፥ 245፥ 251
ሳህለ ሥላሴ (ንጉሥ)፦ 31፥ 330
ሳሙኤል (አቡነ ፣ አባ)፦ 98፥ 182
ሳሙኤል ገዛኸኝ (አቶ)፦ 182
ሳራ (ልዕልት)፦ 269
ሳንማርሳኖ (ጀኔራል)፦ 41-42
ሰለሺ መንገሻ (የአስር አለቃ)፦ 156
ሰለሺ በየነ (የመቶ አለቃ)፦ 155
ሰውል ሚካኤል (ራስ)፦ 30

...ሸ...

ሸዋንዳኝ በለጠ (ጓድ)፦ 246
ሻረው (አቶ)፦ 182
ሽመልስ አዱኛ (ጓድ)፦ 183
ሽባባው ዘለቀ (ሻለቃ)፦ 479
ሽፈራው በቀለ (አቶ)፦ 4
ሽፈራው ወርቁ (ሻለቃ)፦ 479

...ቀ...

ቃለክርስቶስ አባይ (ኮሎኔል)፦ 144
ቅጣው ይታጠቁ (አፈንጉሥ)፦ 172

...በ...

በለጠ አወቀ (አቶ)፦ 181
በለጠ ገብረጻዲቅ (አቶ)፦ 162፥ 183
በላቸው አሥራት (አቶ)፦ 162፥ 183
በላቸው ጀማነህ (ኮሎኔል)፦ 183
በላይ ቢተው (የመቶ አለቃ)፦ 155
በረከት ኃብተሥላሴ (ዶክተር)፦ 179፥ 196፥ 240
በቀለ ደጉ (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
በእውቀቱ ካሳ (የመቶ አለቃ)፦ 155
በዛብህ ማሩ (ጓድ ዶክተር)፦ 246
በዛብህ ደምሴ (አቶ)፦ 182
በዛብህ ገብሬ (አቶ)፦ 182
በየነ አብዲ (አቶ)፦ 182
በጋሻው አታላይ (የአስር አለቃ)፦ 156
በጋሻው ጉርሜሳ (የአስር አለቃ)፦ 156
ቡልቻ ደመቅሳ (አቶ)፦ 162
ባህሩ ቱፋን (ብ/ጀኔራል)፦ 193
ባህሩ ዘውዴ (ዶክተር)፦ 4
ባራቲየሪ (ጀኔራል)፦ 368
ባሮ ቱምሳ (አቶ ፣ ጓድ)፦ 179፥ 246
ባዩ ይርዳው (የመቶ አለቃ)፦ 222
ቤኒቶ ሙሶሎኒ፦ 53-55፥ 60፥ 73፥ 103፥ 328፥ 369፥ 372
ብሩ (ደጃዝማች ፣ ራስ)፦31፥ 177
ብርሃነመስቀል (ደጃዝማች)፦ 177
ብርሃኑ ባይህ (ጓድ ሻምበል)፦ 143፥ 146፥ 153-154፥ 171፥ 250፥ 319፥ 347፥ 350-352፥ 355
ብርሃኑ አበበ (ዶክተር)፦ 4
ብርሃኑ ዋቀዩ (አቶ ፣ ጓድ)፦ 163፥ 172፥ 183
ብርሃኑ ዲንቃ (ጓድ)፦ 350
ብርሃኔ ገብሬይ (አቶ)፦ 182

...ቨ...

ቪክቶር ኢማኑኤል፦ 52፥ 329
ቭላድሚር ኢሊች ሌኒን፦ 34፥ 65፥ 404፥ 406፥ 408-409፥ 462

...ተ...

ተሰማ በላይ (የመቶ አለቃ)፦ 155
ተሰፋ ደስታ (ኮሎኔል)፦ 195
ተሰፋ ዮሃንስ በርሄ (ደጃዝማች)፦ 162
ተስፋዬ ሕሩይ (ሻምበል)፦ 232
ተስፋዬ ተክሌ (የመቶ አለቃ)፦ 155
ተስፋዬ ኃብተማርያም (ሌ/ኮሎኔል)፦ 479
ተስፋዬ እንዳለ፦ 249
ተስፋዬ እንግዳ (ተራ ወታደር)፦ 384
ተስፋዬ ወ/ሥላሴ (ጓድ ሌ/ኮሎኔል)፦ 174፥ 209፥ 211-213፥ 459
ተስፋዬ ገብረኪዳን (ጓድ ሻለቃ ፣ ሌ/ኮሎኔል)፦ 123፥ 129፥ 152-154፥ 192፥ 210፥ 250፥ 256፥ 350፥ 383፥ 443፥ 447-449
ተናኘ ወርቅ ኃይለሥላሴ (ልዕልት)፦ 112 189
ተካ ቱሉ (ሻለቃ)፦ 146፥ 153-154፥ 250፥ 256
ተክልኝ ንጉሤ (ሌ/ኮሎኔል)፦ 453
ተክልኝ ገዳሙ (አቶ)፦ 162፥ 183
ተክለፃዲቅ መኩሪያ፦ 22፥ 162፥ 171፥ 190፥ 497
ተክለኃይማኖት፦ 17
ተክለብርሃን ወ/እየሱስ (ቄስ መላከሰላም)፦ 172
ተክለጊዮርጊስ (አፄ)፦ 332
ተገኘወርቅ ተሰፋ (ሻምበል ባሻ)፦ 156
ተፈሪ መኮንን (ደጃዝማች ፣ ራስ)፦ 48፥ 78፥ 263፥ 266፥ 340፥ 384 (አፄ ኃይለሥላሴን ይመልከቱ)
ተፈሪ ባንቲ (ብ/ጀኔራል)፦ 144፥ 146፥ 181፥ 219፥ 246-247፥ 249-250፥ 253፥ 255
ተፈራ ተክለዓብ (ም/የመቶ አለቃ ፣ የመቶ አለቃ ፣ ሻለቃ)፦ 111፥ 119-120፥ 123፥ 129-130፥ 143፥ 221-222፥ 224፥ 232፥ 234-235
ተፈራ ኃይለሥላሴ (አቶ)፦ 183
ተፈራ ወ/መስቀል (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
ተፈራ ወንዴ (ጓድ ዶክተር)፦ 474
ተፈራ ደንቀው (ሻምበል)፦ 155
ተፈራ ደገፌ (አቶ)፦ 172፥ 268
ተፈራ ጂፋር (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
ቲቶ (ማርሻል)፦ 351
ታምሩ ወንድምአገኘሁ (አቶ)፦ 182
ታምራት ፈረደ (ፒ.ኦ)፦ 156
ታምራት ፈዬ (ሻምበል ባሻ)፦ 156
ታዬ ገብረማርያም (አለቃ)፦ 327
ታደሰ መንገሻ (አፈንጉሥ)፦ 172
ታደሰ ብሩ (ብ/ጀኔራል)፦ 130፥ 178
ታደሰ ተፈራ (አቶ)፦ 162
ታደሰ አደራ (ሻምበል ባሻ)፦ 155
ቴዎድሮስ (አፄ ፣ ዳግማዊ)፦ 30፥ 32-33፥ 36፥ 43-45፥ 48፥ 69፥ 190፥ 277፥ 332፥ 365 (ካሳ ኃይሉን ይመልከቱ)
ቴዎፍሎስ (አቡነ)፦ 271
ትሩማን (ፕሬዝዳንት)፦ 66-67
ትርፌ ሹምዬ (ብላታ ፣ ፊታውራሪ)፦ 172፥ 177

...ኀ...

ኃ/ገብርኤል ዳኘው (ዶክተር)፦ 183፥ 245
ኃይለሥላሴ (አፄ ፣ ቀዳማዊ)፦ 43-44፥ 47-48፥ 51፥ 55፥ 57-63፥ 69፥ 73፥ 78-82፥ 101፥ 105፥ 107፥ 112፥ 118፥ 125፥ 130-131፥ 163፥ 167፥ 172፥ 177፥ 180፥ 207፥ 217፥ 222፥ 224-226፥ 237፥ 259-266፥ 271፥ 293፥ 309-310፥ 339-341፥ 343፥ 350፥ 363፥ 369፥ 371-376፥ 380፥ 390፥ 396፥ 403፥ 414፥ 419፥ 486፥ 491፥ 493 (ተፈሪ መኮንንን ይመልከቱ)
ኃይለሥላሴ ጉግሳ (ደጃዝማች)፦ 50
ኃይሉ ረጋሳ (ሻለቃ)፦ 178
ኃይሉ በላይ (የአስር አለቃ)፦ 156
ኃይሉ ወ/ጊዮርጊስ (አቶ)፦ 182
ኃይሉ ይመኑ (ጓድ)፦ 183፥ 395፥ 455
ኃይሌ ባይከዳኝ (ሜ/ጀኔራል)፦ 138፥ 232
ኃይሌ ወ/ሚካኤል (ዶክተር)፦ 172፥ 182
ኃይሌ ፊዳ (ጓድ)፦ 246

...ነ...

ነቢዩ ታዬ (ሻለቃ)፦ 129፥ 210-211
ነአኩቶለአብ፦ 19
ነገደ ጎበዜ (ጓድ ዶክተር)፦ 246፥ 350
ነጋ ተገኝ (ሜ/ጀኔራል)፦ 125-126፥ 129፥ 141፥ 177፥ 233
ነጋሽ ደስታ (አቶ)፦ 162
ነጋሽ ተስፋጽዮን (ሻምበል)፦ 155
ነጋሽ ወ/ማርያም (አቶ)፦ 172
ናደው ዘካሪያስ (ጓድ ሻለቃ)፦ 4፥ 152
ናፒየር (ጀኔራል)፦ 365
ንዋይ ወ/ዓዲቅ (አቶ)፦ 182
ንጉሴ ኃይሌ (ሻለቃ)፦ 169
ንጉሴ ነጋሳ (የአስር አለቃ)፦ 156
ንጉሴ ወልዴ (የአስር አለቃ)፦ 156
ንጉሴ ፋንታ (የሃምሳ አለቃ)፦ 137፥ 146፥ 155

...አ...

አሀዱ ሳቡሬ (አቶ)፦ 162
አህመድ ሰኢድ አሊ (አቶ)፦ 182
አህመድ ወልደ ኢብራሂም (ግራኝ ፣ ኢማም)፦ 3፥ 21-23፥ 25፥ 30፥ 35፥ 72
አለሙ አበበ (ጓድ ዶክተር)፦ 246፥ 347፥ 391
አለማሁ አየለ (የአስር አለቃ)፦ 156

አለማየሁ ኃይሌ (የመቶ አለቃ)፦ 153-154፣ 245
አለማየሁ ከልካይ (ተራ ወታደር)፦ 157
አሎላ (ራስ)፦ 40-41
አሊ (ራስ)፦ 31፣ 330
አሊ ሙሳ (የመቶ አለቃ ፣ ሻምበል)፦ 155፣ 212-213
አሊ ኑር፦ 29
አሊ ኩሉ፦ 331
አሌክሳንደር (ታላቁ)፦ 70
አማኑኤል አምደሚካኤል (አቶ)፦ 171፣ 199
አማን ሚካኤል አንዶም (ብ/ጀነራል ፣ ሌ/ጀነራል ፣ ሜ/ጀነራል)፦ 86-87፣ 111፣ 113፣ 119-125፣ 159፣ 180፣ 183፣ 186-187፣ 190-191፣ 193-213፣ 215-219፣ 222-224፣ 234፣ 240፣ 318፣ 321፣ 491
አምሐ (ሻምበል)፦ 461
አምባቸው ዓለሙ (የአስር አለቃ)፦ 156
አምቤርቶ (ንጉሥ)፦ 368
አምደጺዮን (አፄ)፦ 31
አሥራተ ካሳ (ልዑል)፦ 112
አሥራት ደስታ (ሻለቃ)፦ 153-154
አራቢኦም እንቶኖሬ፦ 331
አራቢና በዛብሁ፦ 452
አራጌ ይመር (የአስር አለቃ)፦ 157
አሰፋ ሊበን (አቶ)፦ 172፣ 182
አሰፋ መኮንን (ሻለቃ)፦ 155፣ 163፣ 166
አሰፋ መድሐኔ (ጓድ ዶክተር)፦ 246
አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ (ዶክተር)፦ 182
አሰፋ ደምሴ (ሌ/ጀነራል)፦ 175
አሰፋ ገብረማርያም (ብ/ጀነራል)፦ 125
አሳየ ብርሃኑ (የመቶ አለቃ ፣ ጓድ)፦ 136፣ 141
አሰፈሃ ወ/ሚካኤል (ቢትወደድ)፦ 171፣ 202
አስፋወሰን (ልዑል አልጋ ወራሽ)፦ 111፣ 112
አሸብር አማረ (የመቶ አለቃ)፦ 155
አሻግሬ በየነ (አቶ)፦ 181
አሻግሬ ይግለጡ (ዶክተር)፦ 181
አበራ አጋ (ሻምበል ባሻ)፦ 156
አበበ ረታ (ቢትወደድ)፦ 172
አበበ በላይነህ (ሻለቃ)፦ 155
አበበ ቢቂላ፦ 424
አበበ ወ/መስቀል (ጀነራል)፦ 124-125
አበበ ደጋጋ (ሌ/ኮሎኔል)፦ 126
አበበ ገመዳ (ጀነራል)፦ 120፣ 125፣ 224-226፣ 232
አበበ ጥላሁን (አቶ)፦ 181
አቢኑር (ሻምበል)፦ 142
አባተ መርሻ (ሻለቃ)፦ 154
አብርሃም ደሞዝ (ዶክተር)፦ 172
አብዩ አበበ (ሌ/ጀነራል)፦ 125፣ 162
አብደላ ኢብን፦ 331
አብዱ ረሺድ ሸርማርኬ (ዶክተር)፦ 226
አብዱላሂ (ጓድ)፦ 443
አብዱላዚዝ ሼክ መሃመድ (ቀኛዝማች)፦ 172
አብዱል ፈታህ (ጓድ)፦ 342-344፣ 354
አብዱራፊ፦ 36፣ 110
አንድሪያ ኮርዚኒ፦ 331
አንድሬ ግሮሚኮ (ጓድ)፦ 351፣ 356
አከሊሉ ሀብተወልድ (አቶ)፦ 61፣ 99፣ 106፣ 111-113፣ 115-116፣ 118፣ 130፣ 156፣ 168፣ 177፣ 489
አከሊሉ ሀብቴ (ዶክተር)፦ 172
አከሊሉ በላይነህ (ሻምበል ባሻ)፦ 156
አወል አደም አባዋሬ (አቶ)፦ 182
አውጋቸው ከፍያለው (አቶ)፦ 182
አየለ አድማሱ (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
አያሌው ማንደፍሮ (አቶ)፦ 344
አይዘንሃወር (ጀነራል)፦ 57
አደም ያሲን (ዶክተር)፦ 344
አዲስ ተድላ (ሻምበል ፣ ሻለቃ)፦ 155፣ 250፣ 347፣ 442-443
አዲስ አለማየሁ (ቢትወደድ)፦ 172
አዳነ (ቢትወደድ)፦ 261
አዳፍሬ አየሉ፦ 384
አጉስቶስ ቄሳር፦ 70
አጥናፉ አባተ (ሻለቃ ፣ ሌ/ኮሎኔል)፦ 122-123፣ 149፣ 151-153፣ 154፣ 160፣ 171፣ 173፣ 175፣ 178፣ 180፣ 188፣ 190፣ 196፣ 199፣ 200፣ 205፣ 212-213፣ 234-235፣ 237-239፣ 240-243፣ 246-248፣ 250-251፣ 253-258፣ 268-269፣ 270፣ 280፣ 427-429
አፈወርቅ ወንድሙ (አቶ)፦ 182
ኡመር ሰመተር፦ 421
ኢብራሂም ቢምአህመድ፦ 331
ኢብራሂም ኢጋል፦ 225-226፣ 378
ኢትዮጲስ፦ 11
ኢጋል (ጠቅላይ ሚኒስትር)፦ 225-226
ኤረንድሮፕ (ኮሎኔል)፦ 37
ኤሪክ ሆኔከር (ጓድ)፦ 352፣ 359
ኤንግልስ፦ 408
ኤፍሬም ገብረሃና (ም/የመቶ አለቃ)፦ 222
እምሩ (ልዑል ራስ)፦ 51፣ 84፣ 186፣ 189፣ 268-269
እስክንድር ደስታ (አድሚራል)፦ 112
እሸቱ አለሙ (ተራ ወታደር)፦ 157
እንዳለ ተሰማ (ሻምበል)፦ 155
እንዳልካቸው መኮንን (ልጅ)፦ 62፣ 99፣ 112፣ 114-115፣ 117-119፣ 121-123፣ 127፣ 130-132፣ 136፣ 140፣ 143፣ 153፣ 158-162፣ 168-170፣ 173፣ 175-179፣ 194፣ 235፣ 238፣ 242፣ 248፣ 264፣ 266፣ 278፣ 489-491
እዮአስን (አፄ)፦ 30
እያሱ (ልጅ)፦ 48፣ 59፣ 79፣ 340
እምብ ገ/ክርስቶስ (ዶክተር)፦ 182
ኦቻዎ (ሜ/ጀነራል)፦ 474፣ 479


...ከ...


ከበደ ተሰማ (ደጃዝማች)፦ 162፣ 183፣ 383
ከበደ አሊ (ሻምበል ባሻ)፦ 155
ከበደ አበጋዝ (የአስር አለቃ)፦ 156
ከበደ ኩብረት (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
ከበደ ደስታ (አቶ)፦ 182
ከበደ ገብሬ (ጀነራል)፦ 113
ከተማ አይቶንፍሱ (ሻለቃ)፦ 129፣ 155
ኩዱ ዳሌ (የመቶ አለቃ)፦ 217-218
ኩዊንተስ ኩራቲወስ፦ 70
ኪሮስ (ሻለቃ)፦ 247
ኪሮስ አለማየሁ (ሻለቃ)፦ 247
ካርል ማርክስ፦ 3፣ 408
ካሳ (ደጃዝማች)፦ 332፣ 365 (አፄ ዮሐንስን ይመልከቱ)
ካሳ (ራስ)፦ 51
ካሳ ኃይሉ፦ 32 (አፄ ቴዎድሮስን ይመልከቱ)
ካሳ አሥራት (አቶ)፦ 182
ካሳ ከበደ (ጓድ)፦ 383-384
ካሳ ወ/ማርያም (ልጅ)፦ 224
ካሳሁን ታፈሰ (ሻለቃ)፦ 155
ካሳዬ አራጋው (የመቶ አለቃ)፦ 153-154
ክሪስቶፎር (ኮሎኔል)፦ 41
ክፍሌ ወርቁ (አቶ)፦ 232
ኮሪ (አምባሳደር)፦ 84


...ወ...


ወ/ማርያም ወ/ሚካኤል (አቶ)፦ 182
ወ/ሥላሴ በረካ (ሌ/ጀነራል ፣ ሜ/ጀነራል)፦ 133፣ 125፣ 135
ወ/ጊዮርጊስ (ፀሃፊ ትዕዛዝ)፦ 61
ወሌ ቸኮል (አቶ)፦ 182
ወርቁ ሀ/ወልድ (አቶ)፦ 182
ወርቁ መኮንን (ብ/ጀነራል)፦ 126
ወርቁ ተፈራ (አቶ)፦ 172
ወርቁ ገብረማርያም (ብ/ጀነራል)፦ 125
ወሰንሰገድ መኮንን (ልዑል)፦ 112
ወንዳየሁ ምህረቴ (ሻለቃ)፦ 172፣ 186
ዊልያም ሄዊት (ሬር አድሚራል)፦ 39
ውቤ (ደጃዝማች)፦ 31፣ 330
ውብሸት ደሴ (ሻምበል)፦ 155


...ዘ...


ዘለቀ (ጓድ)፦ 449
ዘለቀ መንግሥቴ (ም/የመቶ አለቃ)፦ 222
ዘለቀ በየነ፦ (ሻለቃ ፣ ሌ/ኮሎኔል)፦ 155፣ 447
ዘራያዕቆብ (አፄ)፦ 49
ዘውዲቱ (ልዕልት ፣ ንግሥት)፦ 48፣ 59፣ 79፣ 266
ዘውዴ ገብረሥላሴ (ደጃዝማች)፦ 162፣ 183፣ 194-195
ዘየደ ድንበሩ (የመቶ አለቃ)፦ 222
ዘገየ አስፋው (ጓድ)፦ 245
ዚያድ ባሬ (ጀነራል)፦ 342፣ 378፣ 433
ዥኮቭ (ማርሻል)፦ 57


...የ...


የማን ገብረንጉሥ (ሻምበል)፦ 155
የኋላሸት ግርማ (ሌ/ኮማንደር)፦ 155
የወንደወሰን ኃይሉ (ጓድ)፦ 246
የግለምዘውድ ይመሬ (ኮሎኔል)፦ 119፣ 121-122፣ 131፣ 142-143
ያሲን አራፋት፦ 284
ይልማ ከበደ (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
ይልማ ደሬሳ (አቶ)፦ 27፣ 171
ይልማ ግዛው (ሻለቃ)፦ 443
ይርጋለም (ኮሎኔል)፦ 457
ይስሃቅ (አፄ)፦ 31
ይስፋሀ ደስታ (ሻለቃ)፦ 124
ይኩኖ አምላክ (አፄ)፦ 19፣ 23፣ 497
ይድነቃቸው ተሰማ (አቶ)፦ 183
ይገዙ (ኮሎኔል)፦ 234

ፀዋና አበበ (ቀኛዝማች)፦ 182
የሀንስ ፍታዊ (ጄ.ኤ.ከማን)፦ 157
ዮሐንስ (አፄ ፣ ዳግማዊ)፦ 36-44፣ 48፣ 248፣ 332-334፣ 365-366፣ 384፣ 423 (ደጃዝማች ካሳን ይመልከቱ)
ዮሐንስ አፈወርቅ (ተራ ወታደር)፦ 248፣ 384
ዮዲት እምሩ (ወይዘሪት)፦ 172
ዮዲት (ንግሥት)፦ 17-19፣ 22፣ 33፣ 172

...ደ...
ደመቀ ባንጃው (የሃምሳ አለቃ)፦ 135-136፣ 138፣ 146፣ 156
ደምሴ (ፊታውራሪ)፦ 163፣ 183፣ 198-199
ደምሴ ተፈራ (ፊታውራሪ)፦ 163፣ 183፣ 198-199
ደምሴ አብተው (ሻምበል ባሻ)፦ 156
ደምሴ ካሳዬ (ም.ቴ.ክ.)፦ 155
ደምሴ ደሬሳ (ሻለቃ)፦ 155
ደምስ አላምረው (ተራ ወታደር)፦ 157
ደርቤ ታፈሰወርቅ (አቶ)፦ 182
ደሳለኝ በላይ (ሻምበል ባሻ)፦ 156
ደስታ ታንቱ (አቶ)፦ 182
ደበላ ዲንሳ (ሻለቃ)፦ 155፣ 171፣ 189
ደጀኔ ሰሜ (የመቶ አለቃ)፦ 124
ደጀኔ ወንድምአገኘሁ (የአስር አለቃ)፦ 157
ደጎል (ጄኔራል)፦ 228
ዲሜጥሮስ (ንቡረዕድ)፦ 205
ዲሜጥሮስ ገብረማርያም (ንቡረዕድ መላከሰላም)፦ 202
ዳምጤ ገረመው (የአስር አለቃ)፦ 156
ዳንኤል አስፋው (ሌ/ኮሎኔል)፦ 247፣ 268
ዳንኤል ደስታ (ም/የመቶ አለቃ)፦ 222
ዳኛቸው ይርጉ (ዶክተር)፦ 183
ዳዊት አብዲ (ጄኔራል)፦ 130
ዳግላስ ማካርተር (ጄኔራል)፦ 58
ዳግማዊ ቪልሄልም (ንጉሥ)፦ 368
ዴቪድ ሊቪንግስተን (ዶክተር)፦ 55
ድልነዓድ፦ 17
ድረሴ ዱባለ፦ (ሌ/ጄኔራል ፣ ብ/ጄኔራል)፦ 86፣ 111፣ 222፣ 233፣ 489

...ጀ...
ጀማል አብድርቃድር (ዶክተር)፦ 183
ጀምስ ብሩስ፦ 55፣ 103
ጄሴፔ ሳፔቶ፦ 330-332፣ 366
ጂሚ ካርተር፦ 348፣ 379-380፣ 396
ጃጋማ ኬሎ (ጄኔራል)፦ 169
ጆርጅ ማርሻል (ጄኔራል)፦ 66
ጆርጅ ፓርለስ (ጄኔራል)፦ 39
ጆርጅ ፓርለስ ጎርደን (ጄኔራል)፦ 39
ጆርጅ ኦርዌል፦ 314
ጆናተን ዲንበልቢ፦ 186

...ገ...
ገ/ሕይወት ገ/እግዚአብሔር (ሻምበል ባሻ)፦ 156
ገ/ጊዮርጊስ ብርሃኔ (ተራ ወታደር)፦ 157
ገላውዴዎስ (አፄ)፦ 24-25፣ 29
ገመዳ ጎንፋ (አቶ)፦ 181
ገበሰ ወ/ኪዳን (ም.ቴ.ክ.)፦ 155
ገበያው ተመስገን (የመቶ አለቃ)፦ 155፣ 173-174
ገብረክርስቶስ፦ 454
ገዛሀኝ ወርቄ (የአስር አለቃ)፦ 156
ጉሊዬልም (አድሚራል)፦ 331
ጋማል አብዱል ናስር (ኮሎኔል)፦ 107፣ 308፣ 318
ጋዜሳ (ዶክተር)፦ 225
ጌታሁን ተ/ማርያም (ሻምበል ባሻ)፦ 156
ጌታሁን አቦዬ (ሻምበል ባሻ)፦ 156
ጌታቸው ሺበሺ (ሻለቃ)፦ 155፣ 194፣ 257
ጌታቸው በላቸው (አቶ)፦ 182
ጌታቸው በቀለ (አቶ)፦ 163
ጌታቸው ተቀባ (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
ጌታቸው ናደው (ብ/ጄኔራል)፦ 193
ጌታቸው አረጋ (የሃምሳ አለቃ)፦ 156
ግራዚያኒ (ጄኔራል)፦ 49፣ 54
ግርማ ሀብተገብረዬል (ሻለቃ)፦ 155
ግርማ ቡርቃ (የአስር አለቃ)፦ 156
ግርማ አየለ (የአስር አለቃ)፦ 157
ግርማ አድማሱ (የአስር አለቃ)፦ 156
ግርማ ወ/ጊዮርጊስ (የመቶ አለቃ)፦ 182
ግርማ ፈለቀ (ብ/ጄኔራል)፦ 144፣ 235
ግርማ ፍስሀ (የመቶ አለቃ)፦ 155
ግርማሜ (አቶ)፦ 83-85
ግርማቸው ተ/ኃዋርያት (ደጃዝማች)፦ 172
ግዛው በላይነህ (ሜ/ጄኔራል)፦ 193፣ 214፣ 217፣ 415፣ 443
ግዛው ወ/ሚካኤል (ሻምበል ባሻ)፦ 155
ጎርዶን (ጄኔራል)፦ 39
ጎሹ አለማየሁ (ሻምበል ባሻ)፦ 156
ጎይቶም (ብ/ጄኔራል)፦ 211
ጎይቶም ጴጥሮስ (አቶ)፦ 172

...ጠ...
ጣሰው ጥጆ (ሻለቃ)፦ 173-175
ጥላሁን ቢሻኔ (ብ/ጄኔራል)፦ 144
ጥላሁን አበበ (አቶ)፦ 182
ጥላሁን ገሠሠ፦ 188
ጥሩነህ ኃይለሥላሴ (የመቶ አለቃ)፦ 155
ጥቁሬር ኃይሉ (ዶክተር)፦ 182

...ጰ...
ጰውሎስ ቦጋለ (የመቶ አለቃ)፦ 181
ጰውሎስ ኞኞ (አቶ)፦ 123
ጴጥሮስ ገብሬ (የአስር አለቃ)፦ 153፣ 157፣ 174

...ፀ...
ፀጋዬ አበራ (አቶ)፦ 182
ፀጋዬ ጥሩነህ (የአስር አለቃ)፦ 156
ፀጌ ዲቡ (ጄኔራል)፦ 84፣ 86፣ 222
ፀጌ ፍስሀ (አቶ)፦ 182

...ፈ...
ፊደል ካስትሮ (ጓድ)፦ 352-354፣ 356-358፣ 360
ፋንታ በላይ (ኮሎኔል)፦ 453፣ 455
ፋንታዬ ይህደጎ (ሻለቃ)፦ 155
ፍሬደሪክ ኢንግልስ፦ 408
ፍስሀ ባየህ (አቶ)፦ 172
ፍስሀ አንደቶ (የአስር አለቃ)፦ 157
ፍስሀ ዘውዴ (ጓድ)፦ 4
ፍስሀ ደስታ (ሻለቃ)፦ 155፣ 424
ፍስሃጽዮን ቀከሌ (አቶ)፦ 172
ፍቅረሥላሴ ወግደረስ (ሻምበል)፦ 155፣ 185፣ 187፣ 424
ፍቅሩ ከበደ (ሻምበል)፦ 215
ፍቅሩ ወ/ተንሣይ (ሌ/ኮሎኔል)፦ 127
ፍቅሬ መርዕድ (ጓድ)፦ 246
ፍቅሬ ዘርጋብቸው (የሃምሳ አለቃ)፦ 156

...ፐ...
ፒሎን ግሬንዶኒ፦ 331
ፔትሮቭ (ማርሻል)፦ 480
ፔትሻ (ሌ/ጄኔራል)፦ 474
ፖዶጎርኒን (ጓድ)፦ 347

